መስከረም

STANFORD LIBRARIES

- ሕዝባዊ ድርጅቶች በሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ
- ስለ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት — አንዳንድ ነጥቦች
- ፕሮፓጋንዳ ለምንና እንዴት — አጭር ቅኝት
- የሶሻሊስት ፔዳጎጂ ሚና

DT
371
M469
No.24
1978

ሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 6 ቁጥር
ታኅሣሥ 1978

24

Digitized by Google

Digitized by Google

Meskerem

ET5089PP
9

መስከረም

ቅጽ 6 ቁጥር 24
ታኅሣሥ 1976

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

STANFORD LIBRARIES

ገጽ

- ለተጠናከረ አመራርና ተሳትፎ 3
- ሕዝባዊ ድርጅቶች በሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ 7
  —አብዱል ሐፊዝ ዩሱፍ
- ስለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት
  — አንዳንድ ነጥቦች 38
  —ጌታቸው ሆዴታ
- ፕሮፓጋንዳ ለምንና እንዴት
  —አጭር ቅኝት 50
  —ሰለሞን ለማ
- የሶሻሊስት ፔዳጎጂ ሚና 60
  —ወልደዮሐንስ ወርቅነህ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google



ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

ለተጠናከረ አመራርና ተሳትፎ

የሕዝባዊ አብዮት ዓላማ ብዝበዛንና ጭቆናን ማጥፋት እንደመሆኑ በተቀጣጠለ ማግሥት ብዙኃን ሠርቶ አደሮች ችግሮቻቸውን ሁሉ እንዲያስወግድላቸው ይሻሉ ። በእርግጥ የአብዮት አነሣሥ ለዚሁ በመሆኑ ጉጉታቸው አግባብ አለው ። ይሁን እንጂ በምትሃት ለችግሮች መፍትሔ የሚያስገኝ ሳይሆን ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ታግሎ ምኞቱን እውን እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርለትና የመብቱ ተጠቃሚ የሚያደርገው ነው። በሌላ አገላለጽ ሕዝቡ በነቃና በተደራጀ መልክ ታሪክ ሠሪነቱን በጉልህ ለማረጋገጥ የሚያስችለው ብቻ ነው ። የሕዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች ተቀነባብረውና ተደራጅተው ወደሚፈለገው ታሪካዊ ግብ ያመሩ ዘንድም የግንባር ቀደም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ አመራር ወሳኝነት አለው ።

ፓርቲው ወሳኝ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚችለው የሕዝቡን ፍላጎት በትክክል ወክሎ ሲገኝ ነው ። ይህም ይሆን ዘንድ አባላቱ በሕዝቡ መካከል የሚኖሩና የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው፣ የሚያገለግሉትን ሕዝብ በሚገባ የሚያውቁና የሕዝቡን አመኔታ ያተረፉ መሆን ይኖርባቸዋል ።

በአብዮት መነሻ ወቅትና የመጀመሪያ ዓመታት ትግሉን የሚመሩት አብዮታውያን ማኅበራዊ ምንጫቸው ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ መካከል መሆኑና የፖለቲካ አቋማቸው ወሳኙ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ልዕልናውን ተቀዳጅቶ በአመዛኙ ወደአዲሱ ኅብረተሰብ ግንባታ ምዕራፍ በሚሸጋገርበት ወቅት ሙያና ቴክኒካዊ ዕውቀት፣ በአጠቃላይ የማደራጀት ጥበብ ታክሎ መገኘት እጅግ አስፈላጊ ነው ።

የፓርቲ አመራር ፍሬያማነት በአባላቱ ትክክለኛ አቋምና ችሎታ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ለዕለት ተዕለት የአመራር ተግባር መሳካት በውስጡ የመረጃ በማያቋርጥ መልክ መፍሰስ አንድ አስፈላጊ ሁኔታ ነው ። ካለው መሠረታዊ ጠቀሜታ አኳያም በየጊዜው እየተሻሻለና እየተጠናከረ መሄድ ያለበትም ነው ። በፓርቲ መዋቅር ውስጥ የሚፈስ መረጃና ይልቁንም ከበላይ አካል የሚተላለፍ መመሪያ ፋይዳ የሚኖረው በሚደርሳቸው ወገኖች በሚገባ ተጤና ተግባራዊነቱ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተተርጉሞ የሚፈለገውን ውጤት ሲያስገኝ ነው። በዚህ መልክ መረጃንም ሆነ መመሪያን እያንዳንዱ የፓርቲ አካልና አባል አብላልቶ፣ ተገንዝቦና የራሱ አድርጐ የተተለመውን ግብ በግልጽ በማመልከት ለተግባራዊነቱ የሚፈለገውን ኃይል ካላንቀሳቀሰ የፓርቲው ዓላማ በሥራ አይተረጐምም ።

የመረጃ ጉድለት ወይም በትክክል ግንዛቤ እንዲያገኝ አለመደረግ አሉባልታና ውዥንብር ሊያስከትል ይችላል ። እንደሚታወቀው አሉባልታ ከተወሰነ ጉጉት ወይም ከፍላጐት አለመሟላት የሚመነጭ እንደመሆኑና ቸል ከተባለም የማይፈለግ ውጤት

Digitized by Google

ስለሚያስከትል በወቅቱ መልስ ይሻል። በጠላት ግፊት ጭምር በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዘንድ ተጨባጩን ሁኔታ ያላገናዘበ ጉጉትና ተገቢ ያልሆነ ስሜት እንዲፈጠር ሊደረግ ስለሚችል አገባብ ያለው አመለካከት እንዲሰፍን ወቅታዊ መረጃ በጣም ጠቃሚ ነው። ይህም ሁኔታ ሠርቶአደሩ ሕዝብ ከፓርቲና ከመንግሥት መቼ፣ምን ሊጠብቅ እንደሚችልና እራሱም መወጣት ያለበትን ኃላፊነት፣ በአጠቃላይ መብትና ግዴታውን በትክክል ያስገነዝበዋል።

በፓርቲ የግንባር ቀደምትነት ሚና ውስጥ አካላትም ሆኑ አባላት አንዱ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ ብቁነትን በተግባር በማስመስከር የሚሰጥ አመራር የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ መሆኑን ነው። በብቁነትና በአርአያነት መምራትም ርዕዮተዓለማዊ ጥንካሬን፣ የዓላማ ፅናትን፣ ለአብዮት ታማኝ መሆንን፣ ሀቀኝነትንና የተግባር ሰው መሆንን ይጠይቃል። በመሠረቱ የመሪነት ሚና ያለማቋረጥ የሚፈተን እንደመሆኑ ምንጊዜም ይህን አለመዘንጋት ለውጤት የሠመረ መሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በተጨማሪም መታወቅ ያለበት የመምራት ችሎታ በተስጥኦ ብቻ ሳይሆን በልምድም የሚገኝ መሆኑ ነው። ስለዚህ በየጊዜው በተግባር እየተፈተነ እንዲዳብር የማያቋርጥ ትኩረት መስጠት ይገባል።

የፓርቲ ሥራ መሠረተ ሐሳብና አጠቃላይ የአፈጻጸም ስልት ታዋቂ ቢሆንም ዝርዝር ተግባራዊነቱ በማናቸውም ሥፍራና ጊዜ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችል አይደለም። ልዩ ልዩ ችግሮችን እንደየባሕርያቸው ተረድቶ የሚገቧቸውን መፍትሔዎች መስጠትን የሚጠይቅ ባለብዙ ፈርጅ ሥራ ነው። ይህም በመሆኑ ምን ዓይነት ርዕዮተዓለማዊ ጥንካሬና የሥራ ችሎታ እንደሚጠይቅ፣ ምን ያህል ተለዋዋጭ ለሆኑ ችግሮች ተገቢ መፍትሔ የመስጠት ብቃት እንደሚያሻው ለመገንዘብ አያዳግትም።

የፓርቲ ሥራ በሳይንሳዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ የማኅበራዊ ዕድገት ማንቀሳቀሻ ታሪካዊ ክንውን እንደመሆኑ አባላት በመሰላቸው የሚፈጽሙት አይደለም። በሚገባ ተመርምሮ አቅጣጫና ግብ ተተልሞለት፣ ውጤቱም ከወዲሁ ተመዝኖ የሚቀየስ የጋራ ጥረትና አመራር የሰፈነበት መሆን ያለበት፣ ለተግባራዊነቱ ሁሉም የየበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ የሚጠበቅበት ነው። በዚህ መሠረት የፓርቲውን ፕሮግራም ምርኩዝ በማድረግ ከጉባዔ፣ ከማዕከላዊ ኮሚቴ፣ ከፖለቲካ ቢሮና ከክልል አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎችን አባላት በሚፈለገው መልክ ወደተግባር መተርጎማቸው አማራጭ የለውም። ያለዚህ፣ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ መገለጫ ከሆነ አሠራር ውጭ ፓርቲው ታሪካዊ የመሪነት ሚናውን ይወጣል ማለት የማይሆን ነው።

ይህ ተገቢ አመራር የመስጠትና አመራርን በሚገባ በተግባር የመተርጎም ሁኔታ ከፓርቲ አሠራር አኳያ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከተያያዘው የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ታሪካዊ እንቅስቃሴም አንፃር መታየት ያለበት ነው። ሕዝቡ አብዮቱ ባቀዳጀው ልዩ ልዩ መድረኮች በመጠቀም የሚበጀውን ማጤንና ከዚያም በሥራ መተርጎም መብቱም ግዴታውም ነው። ከዚህ በመለስ ለማናቸውም ፍላጎቱ መሟላት ከተወሰነ ማዕከል፣ ከፓርቲ ወይም ከመንግሥት ብቻ (በቀድሞ አብዮት በአመዛኙ ከመለኮታዊ ኃይል ነበር) መጠበቅ አገባብ አይሆንም። ይልቁንም እንደ ትክክለኛው ፈር ከተቀየሰና ክንድን አስተባብር ወደሚፈለገው ግብ ለማምራት ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረ በኋላ ወሳኙ ሕዝባዊው የተግባር ተሳትፎ ነው።

Digitized by Google

በዚህ ረገድ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ እስከዛሬ በልዩ ልዩዎቹ የዲሞክራሲያዊ መብቱ መገለጫ በሆኑት ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት የተወሰነ ልምድ ያገኘ ሲሆን ለወደፊቱ ደግሞ በሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መቋቋም ወደላቀ ደረጃ ይሸጋገራል። የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነቱ በተሟላ አኳኋን ይረጋገጣል፤ የዚያኑ ያህል የሚኖረው የተግባር ተሳትፎም የሰፋ ይሆናል።

ብቁ አመራር ከሰፊና ያልተቀጠበ የተግባር ተሳትፎ ጋር ሳይቀናጅ አብዮታዊ ዓላማ ከግብ ስለማይደርስ ይህን ማረጋገጥ በአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ትልማችን ውስጥ ቀድሚያ የምንሰጠው ዐቢይ ጉዳይ ነው። ፓርቲያችን በትክክለኛ ንድፈሐሳባዊ ትንታኔ ላይ ተመሥርቶ በየመስኩ ለተጨባጭ ውጤቶች የሚያበቃ አመራር ካልሰጠ ሠርቶ አደሩም ሕዝብ በመብቱ ተጠቀሞና በትክክለኛ ግንዛቤ ላይ ተመሥርቶ ያለ ምንም መቀጠብ ለተግባር ካልተሰለፈ የአብዮታችን ዓላማ ዳር ሊደርስ፥ ከኋላቀርነት እየተላቀቅን ወደ ብልጽግና ልናመራም አንችልም። ስለዚህ በአንድ በኩል የአመራር ብቃትን በሌላ በኩል ደግሞ የተግባር ተሳትፎን ለማዳበር ጥረታችንን በብዙ እጥፍ ማሳደግ ለአፍታም ቸል ልንለው የማይገባ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው።

Digitized by Google

ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ
ኢትዮጵያን እንመሠርታለን!

Digitized by Google

ሕዝባዊ ድርጅቶች በሕዝባዊ ፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ

አብዱልሐፊዝ ዩሱፍ

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት በሚመለከት የተደረሰበት የግንዛቤ ደረጃ ጥራት አግባብ ባላቸው መስኮች በተደረጉት ጥረቶች ፍሬያማነት ሊለካ የሚችል ነው ። ይህ ግንዛቤ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው የሚገባው ቢሆንም ፣ ከሁኔታዎች መለወጥ፣ ከአብዮቱ አጠቃላይ ግብ ፣ በተለይም በሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ የአዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ በተሟላ መልኩ ለማጠናቀቅ መሰናዶው በሚካሄድበት በአሁኑ ወቅት ስለ ፖለቲካ ሥርዓት ያለውን ግንዛቤ ማዳበር አስፈላጊ እንደሆነ ግልጽ ነው ። በዚህ በኩል የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት ይቻል ዘንድ በየደረጃውና በየመድረኩ ተከታታይ ጥናቶችንና ውይይቶችን ማካሄድ ይጠቅማል ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ይህን ጥረት በማገዝ በኩል መጠነኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ሲሆን በአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ሕዝባዊ ድርጅቶች በሚኖራቸው ሚና ላይ የተለየ ትኩረት ያደርጋል ። በአቀራረቡም የፖለቲካ ሥርዓት አጠቃላይ ባሕርያትን ለመጠቆምና ሕዝባዊ ድርጅቶች በተለያዩ ማኅበራዊ ሥርዓቶች የሚጫወቱትን ሚና ለመዳሰስ ይሞክራል ። ከዚያም በአብዮታዊት ኢትዮ ሕዝባዊ ድርጅቶች ያላቸውንና ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና ፣ ለተግባራቸውም መቃናት በየአቅጣጫው መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች ይጠቁማል ።

የፖለቲካ ሥርዓት

ከማኅበራዊ ሕይወት ልዩ ልዩ ዘርፎች ጋር በብዙ ድርች የተሳሰረው የፖለቲካ ሥርዓት በሥርዓትነቱ ነፃ ሆኖና ራሱን ችሎ የሚገኝ አይደለም ። በዚህም መሠረት በማንኛውም የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ የፖለቲካ ሥርዓት የማኅበራዊ ሥርዓቱ አንድ አካል ወይም ንዑስ ሥርዓት ነው ። ይህ ሥርዓት ከሌሎቹ ማኅበራዊ ሥርዓት አካላት ነፃ የሆነ የራሱ ህላዌ እንዳለው ተደርጎ የሚወሰደው ወይም የሚቀ

Digitized by Google

ርበው ለጥናትና ለትንተና እንዲያመች ብቻ ነው። ይህ የአቀራረብ ዘዴ የፖለቲካ ሥርዓትን ልዩ ባሕርያትና መልኮች ከሌሎች የማኅበራዊ ሥርዓት አካላት ለይቶ ለማጤን ይረዳል።

ማንኛውም የፖለቲካ ሥርዓት የተለያዩ የሥራ ድርሻና ሚና ባላቸው ልዩ ልዩ ክፍሎች የተገነባ ነው። እዚህ ላይ ክፍሎች (Elements) የሚለው ቃል አገባብ አካላዊ (ፊዚካል) ክስተቶችን ብቻ የሚያሳይ ሆኖ መወሰድ የለበትም። በዚህም መሠረት ስለፖለቲካ ሥርዓት ይዘት ሲነገር በውስጡ ያሉትን ድርጅታዊ ክፍሎች ብቻ ማለት አይደለም። የፖለቲካ ሥርዓት፣ ኅብረተሰብ በተማከለ የፖለቲካ ሥልጣን እየተመራ በውሁድ አካልነቱ መኖሩን የሚያረጋግጥ የተወሳሰበ ቅንብር ነው። በመሆኑም የፖለቲካ ሥርዓት ሲባል የኅብረተሰብ ፖለቲካዊ ሕይወት የሚገለጽባቸውን <u>መሠረታዊ ፈርጆችና ጽንሰ ሐሳቦች</u> ሁሉ ያጠቃልላል።[1] የማኅበራዊ ኑሮ ዘርፎችን የሚመለከቱ ፈርጆችና ጽንሰ ሐሳቦች ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ ሕይወት ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ በፖለቲካ ሥርዓት ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉ አይደሉም። በዚህ ምክንያት ነው የፖለቲካ ሥርዓት ፈርጅ የሚያካትተው የፖለቲካ ሕይወትን የሚመለከቱ <u>መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳቦችን ብቻ</u> ነው የሚባለው።

የፖለቲካ ሥርዓትን ምንነት በድርጅታዊ ገጽታው ብቻ መወሰን የተለመደ ነው። ሆኖም ማንኛውም የፖለቲካ ሥርዓት የሚገለጽባቸው ሌሎች ክፍሎች ወይም አካላት አሉት። * በተጨማሪም የፖለቲካ ሥርዓት ድርጅታዊ ገጽታ ብታውን በውስጡ የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ከመሆኑ አኳያ እራሱን እንደቻለ ሥርዓት ሊወሰድ የሚችል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ግን የአንድ ሥርዓት አንድ ክፍል መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም።

የፖለቲካ ሥርዓት ምንነት ከፖለቲካ ሥልጣን፣ ወይም ኃይል ጋር የተቆራኘ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ሥልጣን ጽንሰ ሐሳብ ከመንግሥት ወይም ከመንግሥት ሥልጣን ጽንሰ ሐሳብ የሰፋ ትርጉም ያለው ነው።[2] በዚህም መሠረት የፖለቲካ ሥርዓት ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር ያለው ዝምድና ከመንግሥት ጋር ባለው ግንኙነት ብቻ የሚወሰን አይሆንም። ስለዚህም ነው ከመንግሥትና ከመንግሥታዊ ክስተቶች ውጭ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ሆነው የሚታዩት። ማንኛውም ዓይነት ሥልጣን ወይም ኃይል በተለይ ደግሞ የፖለቲካ ሥልጣን፣ አንድ ወገን (ቡድን፣ ፓርቲ፣ መደብ...) በኅብረተሰቡ ውስጥ ጥቅሙን ለማስከበርና ፍላጎቱን ለማሟላት ያለውን ተጨባጭ ብቃት የሚያመለክት ነው። ይህን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችል ተጨማሪ ዓቅም እስከሆነ ድረስ፣ በየትኛውም አቅጣጫ የሚደረግ እንቅስቃሴና (ድርጅታዊ፣ ተግባራዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ፣ መንፈሳዊ) ግፊት ሁሉ የፖለቲካ ሥልጣን መግለጫ መሣሪያ ይሆናል ማለት ነው። ስለሆነም የፖለቲካ ሥርዓት ድርጅታዊ ገጽታ በፖለቲካ ሥልጣን መሣሪያነቱ መንግሥታዊው ብቻ መሆን አይኖርበትም፤ አይደለም። በተመሳሳይ ሁኔታም የፖለቲካ ሥርዓት ርዕዮተ ዓላማዊና ግዕዛዊ (Normative) ገጽታዎችም ከመንግሥት ባሕርይና ተግባራት የሚመነጩት ብቻ እንዲሆኑ መጠበቅ የለባቸውም።

ስለሆነም ሕዝባዊ ድርጅቶች መንግሥታዊ አካላት ባይሆኑም በፖለቲካ ሥልጣን መግለጫ መሣሪያነታቸው የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ሥርዓቱ ግዕዛዊ ገጽታ የፖለቲካ ሥርዓቱ መሪ ማዕከል የሆነ ፓርቲ በቀየሰው ፖሊሲና በሚያራምደው መሥመር

---

* መስከረም ቅጽ 5፣ ቁጥር 19፣ መስከረም 1977 ገጽ፡ 70—72

Digitized by Google

ላይ ከተመሠረቱና በመንግሥትም በኩል ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚደነገጉና የሚደገፉ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ገዕዛንን ብቻ የሚመለከት አይደለም ። [3] ይህ ገጽታ በኅብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ መስኮች ሊታዩ የሚችሉ ምግባራዊ መመሪያዎችና በዚህ ላይ የተመሠረቱ ማኅበራዊ ዝንባሌዎች ቅንብር ነው ። በመሆኑም የፖለቲካ ሥርዓቱ ገዕዛዊ ገጽታ በፖለቲካ ሥርዓቱ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ባገኙ ገዕዛዊ ባሕርያት የሚገለጹ ልማዶችን፣በጥዱልነት፣ወይም በግነነት የሚታዩ ጠባዮችን ሁሉ ያጠቃልላል ።[4]

ከማንኛውም የፖለቲካ ሥርዓት ንድፈ ሐሳባዊ ትርጓሜና ፣ ይልቁንም ከተግባራዊ እንቅስቃሴው ለመረዳት እንደሚቻለውና ፊውዶር ቡርላትስኪ የሚባሉ የሶቭዬት ምሁር በትክክል እንዳብራሩት የፖለቲካ ሥርዓት ተግባሮች የኅብረተሰቡን ግብና ከዚህም ለመድረስ የሚያስፈልጉ ክንዋኔዎችን መወሰን ፣ ለዓላማ ተፈጻሚነት የሚያስፈልገውን ሀብትና ኃይል ማንቀሳቀስ ፣ ለእንቅስቃሴው ስምረት የንዑስ አካላቱን ጤናማ መስተጋብርና ውህደት ማረጋገጥ ፣ የኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ ሕይወት ከአፈሴላዊ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ገዕዛን ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ የሥርዓቱን ትክክለኛነትና ሁነኛነት ማስመስከር ናቸው ። [5]

ለተዘረዘሩት ተግባሮች ተፈጻሚነት የሚደረገውን ሁለገብ እንቅስቃሴና ጥረት በመምራትና በማስተባበር እንዲሁም በማስፈጸም ረገድ የሚኖረው ሁኔታ በኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ አደረጃጀት ስፋትና ጥንካሬ ይወሰናል ። ይህም የሚያመለክተው የፖለቲካዊ ሥርዓቱን ድርጅታዊ ገጽታ ነው ። ከላይ እንደተመለከተው ይህ ገጽታ በአንፃራዊ ሁኔታ የአንድ ሥርዓት አካል ቢሆንም በተናጠል ሲወሰድ የልዩ ልዩ ድርጅታዊ አካላትና ተቋሞች ቅንብር የሚንፀባረቅበት እራሱን የቻለ ሥርዓት ሆኖ ሊታይ የሚችል ነው ። በዚህ ንዑስ ሥርዓት ውስጥ ያሉ አካላትና እነዚህ የሚጠቃለሉባቸው ልዩ ልዩ ዘርፎችም ለፖለቲካ ሥርዓቱ ተግባሮች ተፈጻሚነት የየበኩላቸውን ሚና የሚጫወቱ ናቸው ። እንደሚታወቀው ሁሉ በፖለቲካ ሥርዓት ድርጅታዊ ገጽታ ውስጥ የሚካተቱት ፓርቲ ፣ መንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅቶች ናቸው ። ድርጅትነትን ወይም ተቋምነትን መሠረት በማድረግ እነዚህን አካላት በአንድ ፈርጅ ማጠቃለል የሚቻል ቢሆንም ፣ በእያንዳንዱ ልዩ ባሕርይ ምክንያት በፖለቲካ ሥርዓቱና በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና የተለያየ ነው ።

ከዚህ በላይ የፖለቲካ ሥርዓትን ምንነትና ትርጓሜ እንዲሁም አጠቃላይ ተግባሮችን ለመጠቆም ተሞክሯል ። እነዚህ ተግባሮች በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙን የፖለቲካ ሥርዓት ተግባራት የሚያመለክቱ ናቸው ። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ሥርዓት ፈርጆች ከየኅብረተሰቡ ታሪካዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ሲተነተኑ መሠረታዊ ልዩነቶች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ መጠቆሙ ተገቢ ነው ። በአብዛኛው በፖለቲካ ሥልጣኑ የመደብ ይዘት ላይ ተመሥርቶ ከሚኖረው የፖለቲካ ሥርዓቱ ዓላማ ፣ ይህንንም ከሚያንፀባርቀው በአካላቱ መካከል ካለው ግንኙነት ሁኔታ (የዓላማ አንድነት ወይም ተፃራሪነት) ፣ ከሥርዓተ ማኅበሮች የተለያዩ መሆን የሚመነጩ ናቸው ። ለምሳሌ በካፒታሊስት ኅብረተሰብ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ያለው ሁኔታ በአጠቃላይ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ቅራኔና እንዲሁም በቡርዧው መደብ መካከል ያለውን ትግልና ተፎካካሪነት የሚያንፀባርቅ ነው ። በፊውዳሉም ሆነ በባሪያ አሳዳሪው ኅብረተሰብ የፖለቲካ ሥርዓትም ሁኔታ በመሠረቱ ከዚህ አይለይም ።

Digitized by Google

በካፒታሊስትና ይህን የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች የሚገኙ ሕዝባዊ ድርጅቶችም የሚገኙበት የፖለቲካ ሥርዓት ባሕርይ ውስጣዊ መግለጫ በመሆን የተለያየ ሚና ሲጫወቱ ይታያሉ ። በአንድ በኩል ለሠራተኛ ሕዝቦች መሠረታዊና የዘለቄታ ፍላጎት መሟላት ለሥር ነቀል ለውጥ የሚታገሉ ሲኖሩ በሌላ በኩል ደግሞ ለገዥ መደቦች በማደር የሠራተኛውን ሕዝብ ትክክለኛ የትግል መሥመር ለማፋለስ የሚሰለፉም አሉ ። ባጠቃላይ ግን በኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና የቅርፃዊ ዲሞክራሲ መግለጫ ከመሆን አያልፍም ። ይህ ማለት ግን በካፒታሊስት አገሮች ሕዝባዊ ድርጅቶች ተራማጅ ሚና የላቸውም ማለት አይደለም ። በተፃራሪ መደብ ኅብረተሰቦች ውስጥ ገዥ መደቦች ያላቸውን ኃይል ተጠቅመው በአስገዳጅነት የበላይነታቸውን ለማቆየት እስከቻሉ ድረስ በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ ያለው ቅራኔ በተለያዩ መልኮች የሚከሰት ቢሆንም የኅብረተሰቡ ባጠቃላይና በተለይም የፖለቲካ ሥርዓቱ ውሁድ አካልነት የተጠበቀ ይሆናል ። የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ያንፀባርቁ ድርጅታዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊና ግዕዛዊ አካላት አይለው በመውጣት የማኅበራዊ ሥርዓት ለውጥ ማስከተል እስካልቻሉ ድረስ የፖለቲካ ሥርዓቱ ውሁድነት አይፈርስም ።

ሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓት የአካላቱን ተደጋጋፊነትና ለእንቅስቃሴው ጥራት ዋስትና የሆነውን ፣ የድርጅታዊ ገጽታውን ውሁድነት በግልጽ በሚያሳይ መልክ የአካላቱ የዓላማ አንድነት የሚንፀባረቅበት ነው ። እንደማንኛውም የፖለቲካ ሥርዓት ሁሉ በሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓት አካላት መካከል ያለው ግንኙነት በፖለቲካ ሥልጣኑ መደባዊ ይዘት ላይ ይመሠረታል ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ መደቦች ቢኖሩም ግንኙነታቸው የተፃራሪነት ሳይሆን የመረዳዳትና የአጋርነት መሆኑ የታወቀ ነው ። የፖለቲካ ሥርዓቱም በዚህ ግንኙነት ላይ በመመሥረት ፣ ይህንኑ መልሶ በማንፀባረቅና በተራውም ለግንኙነቱ መዳበርና ዘላቂ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በሚያስችለው መልክ የሚደራጅ ነው ። በዚህ መልክ በተደራጀ የፖለቲካ ሥርዓት አማካይነት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የሚሰፍነው ፖለቲካዊ አመራር ከብዙኃኑ ጥቅምና ፍላጎት የሚመነጭ እንደመሆኑ አሠራሩና ፖሊሲውን ተግባራዊ የሚያደርግባቸው መሣሪያዎቹ በሙሉ ዲሞክራሲያዊ ናቸው ። የሠራተኛው ሕዝብ ቀጥተኛ የሥልጣን ባለቤትነት በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ የሚኖር ፖለቲካዊ አመራር ከዚህ ውጭ እውን ሊሆን የሚችልም አይደለም ። ሌኒን እንዳለውም ጥልቀት ያለው ለውጥ ለማምጣት የምንፈልገውን ያህል ሺህ በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በለውጡ ላይ የሚኖረውን ስሜት በመቀስቀስ ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖረው ፣ ለውጡ አስፈላጊና የግድ መፈጸም ያለበት መሆኑን ማሳመን ግዴታ ነው ።[6] የሠራተኛው ሕዝብ ንቁና ሁለገብ ተሳትፎ የሶሻሊስት ፖለቲካ ሥርዓት ጥንካሬና ዕድገት መሠረት ነውና ።

ስለዚህ የሶሻሊስት ፖለቲካ ሥርዓት አካላት ዲሞክራሲያዊነት ከብዙኃኑ የፖለቲካ የበላይነት መግለጫነቱ በተጨማሪ ለሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ግዴታ ለሆነው ሕዝባዊ ተሳትፎ አመቺ መድረክ ከመፍጠር አስፈላጊነትም የሚመነጭ ነው። ይህም እውነት ከሁሉም በላይ በኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ አደረጃጀት ውስጥ (በፖለቲካ ሥርዓቱ ድርጅታዊ ገጽታ) በተለይ ደግሞ በመንግሥታዊ አውታሮች ዲሞክራሲያዊነትና በተለያዩ መንገዶች ሕዝቡ በመንግሥታዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ ያለው ቀጥተኛ ተሳትፎ ስፋት ከፍተኛ

Digitized by Google

ድርሻ ባላቸው ሕዝባዊ ድርጅቶቹ ሚና
በገሀድ የሚታይ ነው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በሶሻሊስት
የፖለቲካ ሥርዓት

የሶሻሊስት ፖለቲካ ሥርዓት ዓይነተኛ
መገለጫ ዲሞክራሲያዊነቱ መሆኑ ከላይ
ከሰፈሩት ሐሳቦች መረዳት ይቻላል ። ይሁን
ና ዲሞክራሲ «የመንግሥት ቅርጽ » ከመ
ሆኑ አኳያ የሶሻሊስት ዲሞክራሲ መስ
ፈን ፣ በመንግሥቱ መደባዊ ይዘትና በአ
ውታርቹ አደረጃጀት ላይ ብቻ ይወሰናል
ማለት አይደለም ። ሕዝባዊ ድርጅቶች በፖ
ለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ በሚይዙት ሥፍራና
በማኅበራዊ ሕይወት ልዩ ልዩ መስኮች
ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ በመሆና
ቸው የሶሻሊስት ዲሞክራሲ መገለጫና
ለተፈጻሚነቱም መግሪያ ናቸው ። የሶሻሊ
ስት የፖለቲካ ሥርዓት አሠራር የተቀናጀ
መሆኑ ፣ በመንግሥታዊና በሕዝባዊ ድርጅ
ቶች መካከል መሠረታዊ ቅራኔ ያለመኖ
ሩና ከዚህም በላይ የሶሻሊዝም ማኅበራዊና
መንግሥታዊ ሥርዓት ጥልቀት ያለው ዲሞ
ክራሲያዊ ባሕርይ ይህን ሁኔታ አስፈላጊ
ያደርጉታል ።[7] በሌላ በኩል ደግሞ አንድ
ሶሻሊስት መንግሥት የመላው ሠራተኛ
ሕዝብ የጋራና መሠረታዊ ፍላጎት የሚገለ
ጽበትና ለዚህም መሟላት የሚሠራ በመ
ሆኑ ፣ በዚህ ስብስብ ልዩ ልዩ አካላት ዝር
ዝር ጥቅምና ፍላጎት ላይ ለማተኮር ባሕ
ርዩ አይፈቅድለትም ። በተለያዩ መመዘኛ
ዎች መሠረት በየፈርጁ ሊመደቡ የሚች
ሉት የሠራተኛው ሕዝብ ክፍሎች ለየራሳ
ቸው ልዩ ጥቅምና ፍላጎት መሟላት ብቻ
ሳይሆን በተናጠል የሚያደርጓቸው ጥረቶች
ለአጠቃላዩ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደር
ጉበት አመቺ ሁኔታ የሚፈጠረው በሕዝ
ባዊ ድርጅቶች መድረክነት ነው ።

ይሁንና ሕዝባዊ ድርጅቶች በሶሻሊስት
መንግሥት አጠቃላይ መደባዊ ተልዕኮ
ክልል ውስጥ ሊሐቃለሉ የሚችሉ ዳሩ ግን
የተለየ ትኩረትና የቅርብ ክትትል የሚጠ
ይቁ ፣ የሠራተኛውን ሕዝብ ልዩ ልዩ ክፍ
ሎች ዝርዝር ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል
ብቻ የሚመሠረቱ ሳይሆን ከዚህም የሰፋና
የላቀ ግብ ያላቸው ናቸው ። የሠራተኛ
ውን ሕዝብ እያደገ የሚሄድ ንቁ ተሳ
ትፎ በሚጠይቀው የሶሻሊስት ሥርዓት
ግንባታ ውስጥ ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚ
ጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው ።

በዚህ ሂደት ውስጥ የፖለቲካ ሥርዓቱ
ድርጅታዊ አካላት የሥራ ክፍፍል ባሕርይ
እየተቀየረ የሚሄድ እንደመሆኑ መጠን
በአንድ በኩል የሥራ ድርሻ ለውጥ የሚደረግ
ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለአካላቱ የአዳ
ዲስ የሥራ ድርሻዎች ድልድል በተከታ
ታይ ይደረጋል ። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ
በማንኛውም ሶሻሊስት አገር የሚገኙ ሕዝ
ባዊ ድርጅቶች ቀድሞ ከነበራቸው የሥራ
ድርሻ ተጨማሪ ኃላፊነቶችን ለመውሰድ
በሚያስችል አስተማማኝ ደረጃ ላይ በመገ
ኘታቸው በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ የሚ
ጫወቱት ሚና በጣም ከፍተኛ ነው ። በመ
ንግሥታዊ ተግባሮች ውስጥ ያላቸው ተሳ
ትፎ ይበልጥ ቀጥተኛና በየደረጃውም ከፍ
ተኛ እየሆነ ከመምጣቱም በላይ ቀድሞ
በመንግሥት ብቻ ይከናወኑ የነበሩ ተግባ
ሮች ባለቤት ለመሆን በቅተዋል ። ሕዝባዊ
ድርጅቶች ለተጨማሪ ኃላፊነቶች ወይም
የሥራ ድርሻዎች የበቁበት ይህ ሁኔታ ከቀ
ዳሚው ጋር ሲነፃፀር የመጠን ሳይሆን የዓ
ይነት ለውጥ የሚገለጽበት ነው ። ከዚህም
በተጨማሪ ለተከታታይ የዓይነት ለውጦች
ሽግግር መሠረት የተጣለ ፣ ሕዝባዊ ድር
ጅቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚናራቸው
ሚና ይበልጥ እየሰፋና ጥልቀትም እያገኘ
የሚሄድ መሆኑን የሚጠቁም ነው ።

ለሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓት ቀልጣፋ
አሠራርና ለዓለማውም ሥምረት የሠርቶ
አደሩ ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ከመሆኑ

Digitized by Google

እኳያ ሕዝባዊ ድርጅቶች በሶሻሊስት ዲሞክራሲ መገለጫነትና ለዕድገቱም መፋጠን መሣሪያ በመሆን ረገድ የሚጫወቱት ሚና ቀላል ግምት እንደማይሰጠው ቀደም ሲል ተመልክቷል ። እንደማኅበራዊ ሥርዓትነቱ የሶሻሊዝም ዕድገትና ብስለት አንዱ መለኪያ በኅብረተሰቡ ውስጥ ዲሞክራሲ የሚገኝበት የዕድገት ደረጃ ነው ። [8] በዚህም መሠረት የሕዝባዊ ድርጅቶች ዕድገት የማኅበራዊ ዕድገት ሂደት ግዴታ ያደረገው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም ።

በሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚኖራቸው ሁለገብ ተሳትፎ ስፋትና ደረጃ ከፍተኛነት በኅብረተሰቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ የዕድገት ደረጃ የሚወሰን መሆኑ አያጠያይቅም።ይህ መሆኑ ግን በሶሻሊዝም ግንባታ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ሕዝባዊ ድርጅቶች ከፍተኛ ተሳትፎ ሊኖራቸው አይችልም ማለት አይደለም ። ይልቁንም በዚህም ጊዜ ቢሆን በተወሰኑ አቅጣጫዎች የሚጫወቱት ሚና ለአጠቃላይ ፖለቲካዊ ሥርዓቱ ዕድገት ወሳኝ የሚሆንበት ሁኔታ አለ ። ይህን በሚመለከትና በተለይም አሮጌዎቹን መንግሥታዊ አውታሮች የማፈራረስ ሂደት ያለ ሕዝባዊ ድርጅቶች ተሳትፎ እንደማይሆን ሌኒን ሲገልጽ « የቢሮክራሲያዊ አሠራሮችን በመዋጋት ያለጥርጥር የሠራተኛ ማኅበራት ድጋፍ ያስፈልገናል ፤ በችሎታቸውም ልንተማመን ይገባል» [9] ብሏል ።

ይሁን እንጂ ፓርቲውም ሆነ መንግሥቱ በሕዝባዊ ድርጅቶች አስተዋጽኦ ጥራት ላይ እምነት መጣላቸው በአስተዳደራዊ ዕውቀትና ልምድ አንግር ያለባቸውን ድክመት በመዘንጋት አይደለም።ድክመታቸውን ለማስወገድና ይበልጥ ለመጠናከር የሚያበቃቸው የጠቃሚ ዕውቀት ዋንኛው ምንጭ ከተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚቀስሙት ልምድ እንደሆነ በመገንዘብ ነው። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ሕዝባዊ ድርጅቶች ለሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የተለየ ግምት የሚሰጠው ቢሆንም ፥ በማንኛውም አቅጣጫ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሶሻሊስት ዲሞክራሲ የሚገለጽበት እንጂ የዚህ ተፃራሪ አይደለም ። [10]

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሕዝባዊ ድርጅቶች ከዚህ በላይ በጥቅሉ በተመለከቱት አቅጣጫዎች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የፖለቲካ ሥርዓቱ መሪ የሆነውን ፓርቲ መሥመርና ፖሊሲዎች ተግባራዊነት በማረጋገጥም ረገድ የሚጫወቱት ሚና ፓርቲው ለቆመለት ዓላማ ተግባራዊነት የጐላ ድርሻ አለው ። «ሕዝባዊ ድርጅቶች ግንባር ቀደም መሪውን ከሰፊው ሕዝብ ፥ ሰፊውን ሕዝብ ከግንባር ቀደም መሪው የሚያገናኙ አውታሮች ናቸው።»[11]ከዚህ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የግንኙነት መሥመሩ አቅጣጫ ሁለት በመሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች ያሰባሰቧቸውን አባላት ለፓርቲው ፖሊሲ ተፈጻሚነት በስፋት የሚያንቀሳቅሱ ብቻ ሳይሆኑ ፓርቲው የሠራተኛውን ሕዝብ ልዩ ልዩ ፈርጆች ዝርዝር ፍላጎት ፥ ዝንባሌና ስሜት በትክክል እንዲገነዘብ በከፍተኛ ደረጃ የሚያግዙም ናቸው ። ከዚህም በተጨማሪ የአባሎቻቸውን ፖለቲካዊ ንቃተ ኅሊና በማሳደግ እንዲሁም በየአቅጣጫው ለማኅበራዊ ችግሮች እልባት አሰጣጥ የራስ አነሣሽነትና ጥረት እንዲጐለብት በመቀስቀስ በተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚኖረውን ተሳትፎ ከፍ በማድረግ ፥ የሚወከሉት ስብስብ (Collection) መላ ኅብረተሰቡንና መንግሥትን በሚመለከቱ ጉዳዮች የተጣለበትን ኃላፊነትና አደራ ለመወጣት ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋግጣሉ ። [12]

ፓርቲው ለሕዝባዊ ድርጅቶች ጥንካሬ የተለየ ትኩረት የሚሰጠው የሕዝብ ተሳትፎ ለማኅበራዊ ዕድገት መፋጠን አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት ብቻ ሳይሆን በመንግሥታዊ መዋቅሮች አማካይነትና በሠራተኛው ሕዝብ ውስጥ በሚያሰማራቸው አባላቱ ጥረት ብቻ የቀየሰው መሥመር በሚፈለገው ጥራትና ስፋት ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል ስለሚገነዘብም ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ፓርቲው ሠራተኛውን ሕዝብ

Digitized by Google

በመወከል በሚያደርገው ሁሉአቀፍ እንቅስቃሴና በተለይም ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎት መሟላት በየጊዜውና በተከታታይ ለሚነድፋቸው ፖሊሲዎች ጥራት የሕዝቡን ዝርዝር ፍላጎት ፣ ስሜቱንና ዝንባሌውን በተደራጀና በተቀናበረ መልኩ ያገኝ ዘንድ ለሕዝባዊ ድርጅቶች ብቃት ማደግ የተለየ ትኩረት መስጠቱ የግድ ይሆናል ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች ፓርቲውን ከሰፊው ሕዝብ ጋር የሚያገናኙ ድልድዮች ከመሆናቸው አንፃር የሚሰጣቸው ግምት ከፍተኛነት በዚህ አቅጣጫ ከሚፈጽሟቸው ተግባሮች ይዘት ብቻ የሚመነጭ አይደለም ። ሕዝባዊ ድርጅቶች በአባሎቻቸው ፈቃደኝነት የሚመሠረቱ ማኅበራት እንደመሆናቸው መጠን የሚጠቀሙበት የአመራር ስልት በማሳመንና በአባላቱ ከውዴታ በሚመነጭ ተሳትፎ ላይ የሚመሠረት ነው ። ስለዚህም በሕዝባዊ ድርጅቶች መድረክነት የሚጠበቅ ተሳትፎ ሁሉ በመሠረቱ ከፍቃደኝነት እንጂ በሕግ አስገዳጅነት አይደለም ። ከሰዎች ፈቃደኛነትና ውዴታ የሚመነጭ አስተዋጽኦ ለማንኛውም ክንዋኔ ውጤታማነት ታላቅ ድርሻ ያለው በመሆኑና ይህም ሊገኝ የሚችለው ተሳታፊዎቹ የሚሠሩት ሥራ ተገቢና ትክክል መሆኑን ሲያምኑ በመሆኑ ይህን በመሰለ አመራር ስልት ብዙኃንን በማንቀሳቀስ ለሚሠራ ማኅበራዊ ኃይል ፓርቲው ልዩ ትኩረት መስጠቱ አጠያያቂ አይሆንም ። በመሠረቱ ማንኛውም ኮሚኒስት ወይም ሠራተኛ ፓርቲ ለተነሣለት ዓላማ ግብ መምታት የሚደረጉ ጥረቶችን የሚመራው በማሳመንና በማስተማር ነው ።በኮሚኒስት ሥርዓት ውስጥ ለሚሰፍነው ፣ ሠራተኛው ሕዝብ እራሱን በራሱ ለሚያስተዳድርበት ሁኔታ ተግባራዊ ልምድ የሚቀስምበት አዲሱ ሶሻሊስት ሰው የሚፈጠረው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ላይ ነው ። በዚህ አኳያ ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚጫወቱት ሚና በርግጥም የተለየ ግምት ሊሰጠው ይገባል ። ሕዝባዊ ድርጅቶችን በማጠናከር ለተጨማሪ ኃላፊነቶች በማብቃት በኮሚኒስት ሥርዓት ለሚፈጠረው ሁኔታ ለማዘጋጀት ጥረት ካልተደረገ በስተቀር ሶሻሊስት መንግሥት ወደ ኮሚኒስታዊ ራስ በራስ አስተዳደር ሊያድግ አይችልም ።[13] ስለሆነም በፓርቲው በኩል በዚህ አቅጣጫ የሚሰጠው ትኩረት እጅግ ከፍተኛ ነው ።

በዚህም መሠረት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት የመጀመሪያ ደረጃዎች አካባቢ የመንግሥታዊ አስገዳጅነት ብሕርይ በተቀላቀለበት ሁኔታ በመንግሥት አካላት ሲከናወኑ የነበሩ ተግባሮች የሠራተኛው ሕዝብ ወገኖች ጠቃሚነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን አምነው በመቀበል ለተግባራዊነታቸው ሕጋዊ (መንግሥታዊ) ግዴታ ውስጥ መግባት ሳያስፈልጋቸው የሚያስፈጽሟቸው ተግባሮች ከጊዜ ወደጊዜ እያደጉ መጥተዋል ። አንድን ተግባር የመንግሥት ሌላውን ደግሞ የሕዝባዊ ድርጅት ነው የሚያሰኘው ሁኔታ የሚታየው ከባለቤትነት አኳያ ብቻ ሳይሆን በማስፈጸም ረገድ ካለው ልዩነትም ጭምር ነው ። ሕዝባዊ ድርጅቶች በአባሎቻቸው ፈቃደኝነት የተመሠረቱ እንደመሆናቸው መጠን አባሎቻቸውን የሚያሰማሩት በማሳመን ነው ። በአባላት ላይ በተወሰነ መልክ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ ቢኖርም ይህ ተጽዕኖ ማንበራዊ እንጂ ፖለቲካዊ አይደለም ።[14] ስለሆነም በሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በየደረጃው በማንቀሳቀስ የተሻለ ውጤት በሚገኝባቸው መስኮች መንግሥታዊ ተግባሮች ወደ ሕዝባዊ ድርጅቶች የማይሸጋገሩበት ምክንያት አይኖርም ። ዋናው ነገር ይህን የመሰለ ኃላፊነት ለመውሰድና በጥራት ለመወጣት ያላቸው አስተማማኝ ብቃትና ጥንካሬ ነው ። ባጠቃላይ በሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ

Digitized by Google

ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚይዙት ሥፍራና የሚጫወቱት ሚና የሶሻሊስት ዲሞክራሲን ስፋትና ጥልቀት የሚያንፀባርቅ ብቻ ሳይሆን በዚህም ላይ ተመሥርቶ ሠራተኛውን እራሱን በራሱ በማስተዳደርና በመምራት ረገድ ተግባራዊ ልምድ የሚያገኝበትንና ለአዲሱ ሥርዓት ግንባታ ጠንካራ መሠረት በመጣል ሂደት ውስጥ የሚያበረክቱትን ድርሻ በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በኢትዮጵያ

ከዚህ በላይ በሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓትና ወደዚሁ ሥርዓት በሚያመራው ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ስለሕዝባዊ ድርጅቶች ሚናና መስፈን ያለባቸውን መሠረታዊ ሁኔታዎችንና ሊከተሏቸው የሚገቡ የዕድገት አቅጣጫዎችን ለመጠቆም ተሞክሯል ። በእርግጥ አንድ ሶሻሊስት ሥርዓት ከሌሎች የሚለይባቸው ዝርዝር ባሕርያት ሊኖሩት ቢችሉም በመሠረቱ ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ከመሆን ውጭ የሚደርጉት አይደሉም። በአንፃሩም ከሶሻሊስት የእድገት ደረጃ በመለስ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የበላይነት የሰፈነባቸው ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓቶች በአወቃቀራቸውና በአሠራራቸው አኳያ የሚታዩ የየራሳቸው ባሕርያት ቢኖሯቸውም በሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓትነታቸው ከሶሻሊዝም ጋር የሚመሳሰሉባቸው በርካታ ገጽታዎች አሉአቸው ።

በሁለቱ ደረጃዎች መካከል ሊኖሩ ከሚችሉት አያሌ ልዩነቶች መካከል በተቀዳሚ ሊነሣ የሚገባው የተጠቀሱትን ሥርዓቶች «ሕዝባዊ» የሚያሰኘው ሥልጣን የጨበጠው «ሕዝብ» ይዘት ልዩነት ነው። እዚህ ላይ «ሕዝብ» የሚለው ፈርጅ አገባብ የአንድ አገር ዜጎችን ሁሉ ሊያጠቃልል በሚችል ፍቺው ሳይሆን ብዙኃኑንና ሠርቶ አዳሪውን ወገን ለማመልከት ነው ። ስለሆነም በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ወይም በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች «ሕዝብ» በሚለው ክፍል ወይም ፈርጅ ሊካተቱ የሚችሉት መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ ናቸው ። ለምሳሌ ፣ በሶሻሊዝም የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች እንኳን የ«ሕዝብ» ፈርጅ የሚይዛቸው መደቦችና ክፍሎች ሊለያዩ ይችላሉ ። ሌኒን በ1917 አካባቢ ስለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት ሲጽፍ «ሕዝብ» ሲል በተለይ ወዛደርና ገበሬውን ማለቱ ነበር ። ነገር ግን በዳበረ ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ሕዝብ ማለት ሠራተኞችን ፣ በኅብረት እርሻ የተደራጁ ገበሬዎችን ፣ የቢሮ ሠራተኞችንና ምሁራንን የሚያጠቃልል ነው ።

በዚህ መሠረት ስለሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓት የተጠቀሱት ባሕርያት ሁሉ ከሚገኙበት በታሪክ የተወሰነ ሁኔታና የዕድገት ደረጃ አንፃር የተለያየ ቅርፅ ሊኖራቸው ይችላል ። ነገር ግን የሠርቶ አደሩ ሕዝብ የበላይ ገዥነት የሰፈነ እስከሆነ ድረስ ሕዝባዊ ናቸው ።

በኢትዮጵያ የሚገኙት ሕዝባዊ ድርጅቶች የዛሬ ገጽታም ሆነ የዕድገት አቅጣጫ ግምገማ ከአንድ ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ምንነት አጠቃላይ ማዕቀፍ (Framework) ውጭ ሊሆን አይችልም ። በኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ድርጅቶችን በሚመለከት ያለውን ሁኔታ ለመቃኘት የሚሞከረው ከዚህ ግንዛቤ በመነሣት ነው ።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መቀዳጀቱና በተለይም እራሱን በራሱ በማስተዳደር ረገድ ያገኛቸው ድሎች ከፍተኛ ግምት ከሚሰጣቸው የአብዮቱ ድሎች መካከል ዋንኞቹ እንደሆኑ ይታወቃል ። በዚህ አንፃር ሰፊው ሕዝብ በየፈርጁ የተሰባሰበባቸው የሕዝባዊ ድርጅቶች መመሥረት ታላቅ ግምት ሊሰጠው እንደሚገባ ግልጽ ነው ። ይህም ግምት የሚመነጨው ሕዝባዊ ድርጅቶቹ ካበረከቱት አስተዋጽኦ ብቻ በመነሣት ሳይሆን በፖለቲካው መስክ አብዮቱ ካስመዘገባቸው ሶሻሊስት ይዘት ካላቸው ድሎች መካከል ሊቆጠር የሚችል ከመሆኑም ጭምር ነው ።

ሶሻሊስት የዕድገት ጉዳና በሚከተሉ አገሮች ውስጥ በየጊዜው የተገኙ ድሎችን

Digitized by Google

በመንከባከብና በተጨማሪ ድሎችም አግኪይነት ማኅበራዊ ዕድገትን ለማስከተል የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ። ስለዚህም በእነዚህ አገሮች ፖለቲካዊ ዕድገት ውስጥ የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ እያደገ መምጣትና የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወት የሚመለከቱ ማኅበራዊ ዘርፎች ሁሉ ዲሞክራሲያዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ግዴታ ይሆናል ።

በኅብረተሰቡ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ መስፈን ከሚገለጥባቸው መንገዶች መካከል ሠርቶ አደሩ ሕዝብና የአብዮቱ ወገኖች በየፈርጃቸው ተደራጅተው የሚያደርጉት የእንቅስቃሴ ስፋት መጠን እንደመሆኑ በዚህ በኩል አመቺ መድረክ የሚፈጥሩት ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ አያጠያይቅም ። በኢትዮጵያችንም የሥራ ሥምሪትን ፣ የመኖሪያ ክልልን ፣ ጾታንና ዕድሜን መሠረት በማድረግ ሕዝባዊ ድርጅቶች የተመሠረቱትና ከጊዜ ወደጊዜም እንዲጠናከሩ በማድረግ ለፓርቲው ዓላማዎች ተፈጻሚነትና ለአባሎቻቸው ፍላጐት መሟላት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከአብዮቱ ዕድገት ጋር እኩል በመራመድ እየዳበረ ይሄድ ዘንድ የማያቋርጥ ጥረት ማስፈለጉም ለዚህ ነው ። እንደሚታወቀው ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ አንጋፋዎቹ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ፣ የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር ፣ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበርና የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር ናቸው ። በብሔራዊ ደረጃ የተደራጁ ባይሆንም (በባሕርያቸው ሊደራጁም አይችሉምና) በከተሞች ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የተዋቀሩት የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራትም ይገኛሉ።በበርካታ መመዘኛዎች እኪያ ሲታይ ከተቀሩት ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚለይ ቢሆንም በተለይም በመሠረታዊ አካላቱ አመሠራረትና ከዚያም በላይ ያሉት አመራር አካላቱ በሕዝባዊ ድርጅቶች መድረክነት የሚቋቋሙ በመሆናቸው ምክንያት የሠርቶ አደሩ ቁጥጥር ኮሚቴም እንደሕዝባዊ ድርጅት ሊታይ ይችላል ።

በኢትዮጵያ ከ1928-33 በተካሄደው የፀረ ፋሺስት ትግል ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ አባት አርበኞች የተሰባሰቡበትና በብሔራዊ ደረጃና በአንዳንድ ክፍላተ ሀገር የሚገኘው የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበርም ሌላው ሕዝባዊ ድርጅት ነው ።

ከእነዚህም በተጨማሪ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በተለያዩ መድረኮች የተወሰኑና አልፎ አልፎም በጣም ጠቃሚ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ የሙያ ማኅበራት አሉ ። እነዚህ ማኅበራት በሚያሰባስቧቸው አባላት በዓላማና በአሠራር ስልታቸው እንዲሁም በአደረጃጀታቸው የተለየ ባሕርይ የሚያንፀባርቁ ቢሆኑም በመሠረቱ በሕዝባዊ ድርጅት ፈርጅ ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው ። በአሁኑ ጊዜ ከኢሠፓ የቅርብ አመራር እያገኙ በአዲስ መልክ በመደራጀት ላይ ያሉት የሙያ ማኅበራት ፣ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፣ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማኅበር ፣ የኢትዮጵያ ተውኔት ባለሙያዎች ማኅበር ፣ የኢትዮጵያ ሠዓሊያን ማኅበር ፣ የኢትዮጵያ ጤና ባለሙዎች አንድነት ማኅበር ፣ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ማኅበርና የጋዜጠኞች ማኅበር ናቸው ።

የተጠቀሱት አንጋፋ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት ባብዛኛው የተመሠረቱት አብዮቱ በፈጠረላቸው አመቺ ሁኔታ ነው ። የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር በመባል ይታወቅ የነበረው የሠራተኛ ማኅበርም ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ በመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር በአዲስ ይዘትና በአዲስ ዓላማ የተደራጀ ነው። ከዚህም የተነሣ የሁሉም መሠረታዊ ዓላ

Digitized by Google

ማዎች የአሰባሰቧቸውን አባላት ለማስተማር ወይንም በአሰባሰቧቸው አባላት ውስጥ ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ ሥራዎችን በማካሄድ ለአብዮቱ ዓላማዎች ተፈጻሚነት ፣ ለአብዮቱ ወደፊት እርምጃ አጋዥ ኃይል ከመፍጠርና ከማጠናከር ውጭ አይደሉም ። ከዚህም በተጨማሪ በአብዮታዊው መንግሥትና ቀደም ሲል ከኢሠፓአኮ ዛሬ ደግሞ ከኢሠፓ በሚያገኙት አመራር የአባሎቻቸውን ፍላጎት የማሟላትና ጥቅማቸውን የማስከበር ዓላማ አላቸው ። በዚህ ዓይነት ሊታዩ የሚችሉ ሕዝባዊ ድርጅቶች ዓላማዎች በቁጥር በርካታ ሊሆኑ ቢችሉም ከተጠቀሱት ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ውጭ ሊታዩ የሚችሉ አይደሉም ። ለምሳሌ የኢሴማን ዓላማ ብንወስድ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ ሴቶችን በሰፊው ከማሰለፍ ባሻገር የሴቶች እኩልነት ይበልጥ ተጨባጭ እንዲሆን ፣ ሴቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ሥፍራ እንዲሻሻል፣ባጠቃላይ ሴቶች በኅብረተሰቡ ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ለሚያደርጉት ተሳትፎ ግደግ አስፈላጊ ሁኔታዎች በመፍጠር ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ። በሌላ በኩል ደግሞ የሴቶች ተሳትፎ አጥጋቢ አለመሆን ካለመማር ፣ ካለማወቅ ፣ ከቤስተብ ኃላፊነት ጭነት ክብደት የሚመነጭ እንደመሆኑ መጠን አኢሴማ እነዚህን ሁኔታዎች ለማሻሻልና እንዲለወጡ በማድረግ የሴቶችን እኩልነትተጨባጭ የማድረግ ዓላማ ይዞ የተነሣ ድርጅት ነው ።

የወጣቱ ድርጅትም እንደዚሁ የወጣቱን ፍላጎትና ልዩ ባሕርይ መሠረት በማድረግ በወጣቶች መሠራት ያለባቸውን ፣ ለወጣቱ መደረግ ያለበትን በማከናወን ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ የተመሠረተ ማኅበር ነው። መኢገማና መኢወማም በዚሁ መልክ የእያንዳንዳቸውን ልዩ ባሕርይ መሠረት ያደረጉ ዝርዝር ዓላማዎች አሏቸው ። ሲጠቃለሉ ግን አባሎቻቸውን ለአብዮቱ ዓላማ ተግባራዊነት ለማሰለፍና ለአባሎቻቸው ጥቅም በራሳቸውም ሆነ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ከመሥራት ውጭ ሊታዩ የሚችሉ አይደሉም።

በሌላ በኩል ሕዝባዊ ድርጅቶች ከቆሙለት ዓላማ ተፈጻሚነት ጋር በተያያዘ መልክ ሊታይ የሚችለው በውጭ ግንኙነት መስክ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው። ከተቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ከአቻ ማኅበራት ፣ ከዓለም አቀፍና ከአህጉራዊ ድርጅቶች ጋር በፈጠሯቸው ግንኙነቶች ያተረፉት ተቀባይነትና ተሰሚነት እያደገ መጥቷል ። ከዚህም በላይ አብዮቱን በማስተዋወቅና አዳዲስ ወዳጆችን በማፍራት ፣ ጠላቶችን በማጋለጥና በተለያዩ መድረኮችም የነበራቸውን ሥፍራ በማሳጣት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና ተጫውተዋል ፣ እየተጫወቱም ናቸው ።

በአሁኑ ጊዜ ካሉት ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በተለይ ፣ መኢሠማ ፣ አኢወማና አኢሴማ በአህጉራዊ ወይም በዓለምአቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ከአመራር ደረጃ ላይ ሁሉ ለመድረስ ችለዋል ። በዚህ መሠረት መኢሠማ የዓለም ሠራተኞች ማኅበር ፌዴሬሽን (WFTU) ምክር ቤት የፕሬዚዲየም አባል ነው ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሥር ባለው የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) ውስጥ የአፍሪካ ቡድን አስተባባሪ አካል ሰብሳቢ ነው ። የመላ አፍሪካ ሠራተኞች ማኅበር አባል ነው። በሶሻሊስት አገሮች ከሚገኙ አቻዎችና ከሌሎቹም ተራማጅ ሠራተኛ ማኅበራት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ሲሆን ፣ ከተወሰኑት ጋር የወዳጅነትና የትብብር ስምምነቶችን ተፈራርሟል ።

አኢወማም የዓለምአቀፍ ተማሪዎች ማኅበር የሴክሬታሪያት አባልና እንዲሁም የዓለም ዲሞክራሲያዊ ወጣቶች ፌዴሬሽን (WFDY) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ነው ። በአመራር አካላቱ ውስጥ ቦታ ያልያዘ ቢሆንም በመላ አፍሪካ ተማሪዎች ማኅበር ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነት ያለው

Digitized by Google

አባል ነው ። በቅርቡም የመላ አፍሪካ ወጣቶች ንቅናቄ አባል ሆኗል ። ከዚህም በተጨማሪ ከሶሻሊስት አገሮች ወጣት ድርጅቶችና ከሌሎችም ተራማጅና ዲሞክራሲያዊ የወጣትና የተማሪዎች ማኅበራት ጋር ጠንካራ ግንኙነት የመሠረተ ከመሆኑም በላይ ከአንዳንዶቹ ጋር የወዳጅነትና የትብብር ስምምነት ተፈራርሟል ።

አኢሴማ የዓለም ዲሞክራሲያዊ ሴቶች ፌደሬሽን (WIDF) የቢሮ አባል ሲሆን ፣ የመላ አፍሪካ ሴቶች ድርጅት ተሰሚነት ያለው አባል ነው ። በሶሻሊስትና በተራማጅ አገሮች ካሉ አቻ ማኅበራት ጋር የተቀራረበ ግንኙነት የመሠረተ ከመሆኑም በላይ ከተወሰኑ ማኅበራት ጋር የወዳጅነትና ትብብር ስምምነት ተፈራርሟል ። መኢገማም ከተለያዩ አገሮች መሰል ማኅበራት ጋር በፈጠረው ግንኙነት የአብዮቱን ግኝቶች በማስተዋወቅ በኩል የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ሲሆን ፣ ከአንዳንድ አቻ ማኅበራት ጋር በተፈራረመው የወዳጅነትና የትብብር ስምምነት አማካይነት ልምድ በመለዋወጥና በሌሎችም መንገዶች ጠቃሚ ውጤት እያስገኘ ነው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በዓለም አቀፍና አህጉራዊ መድረኮች ያላቸው ሥፍራ የኢትዮጵያ አብዮት በተራማጁ ዓለም ያለውን ተቀባይነት የሚያንፀባርቅ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ እነዚህ ድርጅቶች ይህን የመሰለ ተሰሚነት ማግኘታቸው የሚደነቅ ነው ።

እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች በሶሻሊስት አገሮች እንደሚገኙት ተመሳሳይ ድርጅቶች ሁሉ የየራሳቸው ልዩና ገላጭ ባሕርያት እንደተጠበቁ ሆነው የጋራ የሆኑ መሠረታዊ ባሕርያትም አሏቸው ። ሁሉም አንድ ወጥነት ያላቸው ድርጅቶች ናቸው ። ሁሉም የፓርቲውን የመሪነት ሚና ይቀበላሉ ። ለሶሻሊዝም ግንባታ በሚደረገው ጥረት ወገንነት የመሳተፍ የጋራ ዓላማ አላቸው ። በአወቃቀራቸውና በአሠራራቸው ዲሞክራሲያዊ መርሆዎችን ይከተላሉ ። [15]

በአደራጃጀት ረገድ ድርጅታዊ አንድነት እንዳለ ሆኖ ከአንዳንድ ሕዝባዊ ድርጅቶች ባሕርይ የተነሣ መጠነኛ ለውጦችና ልዩነቶች ከመኖራቸው በስተቀር ሁሉም ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚደራጁበት መርህ የሥራ ቦታንና የመኖሪያ ክልልን የተከተለ ነው ። በዚህም መሠረት እንደሁኔታው መሠረታዊ ማኅበራት በሥራ ቦታዎች ወይም በመኖሪያ አካባቢዎች ይመሠረታሉ ። ከዚያም መሠረታዊ ማኅበሮች እየተሰባሰቡ በዝቅተኛ ክልል ደረጃ ፣ እነዚህም በማዕከላዊና በከፍተኛ ክልል ደረጃ በመሰባሰብ በየደረጃው ያሉት አካላት ሁሉ በተዋረድ ከአንድ ማዕከል የሚሰጣቸውን አመራር ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል ከታች ወደላይ ሲታይ እየጠበበ በሚሄድ (ፒራሚዳዊ በሆነ) አወቃቀር የተደራጁ ናቸው ።

ቀደም ሲል የተጠቀሰው መጠነኛ ልዩነት የሚታየው የኢሠማንና የአኢሴማን አደረጃጀት የሚመለከተው ነው ። አኢሴማና አኢወማ በከተማና በገጠር በቀበሌ ደረጃ ከሚገኙት መሠረታዊ ማኅበሮቻቸው በተጨማሪ ለዓላማዎቻቸው ተፈጻሚነት በመ/ቤቶች ፣ በት/ቤቶችና በማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው አባላት የሚኖሩ ከሆነና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የወጣቶችና የሴቶች ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ።

ከዚህ በተረፈ ሁሉም ሕዝባዊ ድርጅቶች ከመሠረታዊ ማኅበራት እንሥቶ እስከ ማዕከል ድረስ ጠቅላላ ስብሰባ ፣ ኮሚቴ ፣ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተብለው የሚታወቁ የአመራር አካላት አሏቸው ።

አጠቃላይ ጉዳዮችን በሚመለከት በሕዝባዊ ድርጅቶች ዘንድ የሚታየው ሁኔታ ከዚህ በላይ የተመለከተውን ይመስላል ። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱን ሕዝባዊ ድርጅት በሚመለከት ሊኖር የሚገባው

Digitized by Google

ማኅባቢ የተሟላ እንዲሆን ሊያግዙ የሚችሉ አኃዛዊ መረጃዎችን እንደሚከተለው ማየት ይቻላል ።

የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር (መኢሠማ)፡—

በአሁኑ ጊዜ መኢሠማ 1600 መሠረታዊ ማኅበራት (ቢያንስ 20 አባላት ባሉበት ድርጅት ወይም ተቋም ወይም ከአንድ አካባቢ በተመሳሳይ የሥራ መስክ በተሰማሩ ሠራተኞች የሚመሠረቱ) እንዳሉት ይገመታል ። * በቁጥሩ ላይ እርግጠኛ መሆን የማይቻለው በተለያዩ የአሠራር ችግሮችና በልዩ ልዩ ምክንያቶች በአባላትና በአካላት ቁጥር መለዋወጥ የተነሣ የመሠረታዊ ማኅበራትም ሆነ የአጠቃላይ አባላት ቁጥር በየጊዜው ስለሚቀያየር ነው ።

በአንድ በኩል መኢሠማ በተቋቋመበት አዋጅ መሠረት አባል ሊሆኑ የሚችሉ ሠራተኞችን ሁሉ በአባልነት አሰባስቦ ባለመነግቱ በየጊዜው በአዲስነት የሚመዘገቡ አባላትና የሚደራጁ ማኅበራት በርካታ ናቸው። በሌላ በኩል አንዳንድ ድርጅቶች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ስለሚዘጉ የመሠረታዊ ማኅበራት ቁጥር ይቀንሳል ።

የአገሪቱን አስተዳደራዊ ክልል መሠረት በማድረግ እንደሁኔታው በወረዳ፣ በአውራጃና በክፍለ ሀገር ደረጃ ከሚመሠረቱት የመኢሠማ አካላት በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ማኅበራትም ተደራጅተዋል ። እነዚህ የክልል አካላት ሊመሠረቱ የሚችሉት በሥራቸው የተወሰኑ አባላትና መሠረታዊ ማኅበራት ሲኖራቸው ብቻ በመሆኑም በሁሉም ወረዳዎችና አውራጃዎች አይገኙም ። በሌላ በኩልም ደግሞ በአንድ ክልል ውስጥ ከአንድ በላይ የኢንዱስትሪ ማኅበራት ሊኖሩ ይችላሉ ። በዚህም መሠረት 176 የወረዳ ሠራተኛ ማኅበራትና 274 የወረዳ ኢንዱስትሪ ማኅበራት፣ 64 የአውራጃ ማኅበራትና 158 የአውራጃ ኢንዱስትሪ ማኅበራት፣ 15 የክፍለ ሀገር ሠራተኛ ማኅበራትና 71 የክፍለ ሀገር ኢንዱስትሪ ማኅበራት ይገኛሉ ። በመጨረሻም በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ብሔራዊ ማኅበርና ዘጠኝ የኢንዱስትሪ ማኅበራት ተደራጅተዋል ። በአሁኑ ጊዜ በመኢሠማ ሥር የተሰባሰቡ አባላት ቁጥርም ከ315 ሺህ እንደማያንስ የሚገመት ሲሆን፣ ከመሠረታዊ ማኅበር አንሥቶ እስከ አገር አቀፍ ደረጃ ባሉት አካላቱ ያሉት መሪዎች ብዛት 86,514 ነው።

መኢሠማ ተደም ሲል ከተጠቀሱት መሠረታዊ ዓላማዎች በመነሣት ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ መ/ቤቶች ጋር በመወያየትና እንዳስፈላጊነቱም በመደራደር ለሠራተኛው ጥቅም መጠበቅ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ጥረት ያደርጋል ። የሠራተኛው ደኅንነት ዋስትና እንዲኖረውና አመቺ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር የራሱን ጥረት ከማድረግ ባሻገር የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ይህን እንዲያሟሉ ግፊት ያደርጋል ። የሠራተኛውን ርዕዮተዓለማዊ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ይሞክራል ። ከዚህ በተጨማሪ በየጊዜው በአብዮታዊው መንግሥትም ሆነ በፓርቲው ለሚደረጉ ልዩ ልዩ ወቅታዊ ጥሪዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚያዊና በማኅበራዊ መስኮች ሠራተኛው ንቁ ተሳትፎ

---

* የቀረቡት አኃዛዊ መረጃዎች የማኅበራቱ አመራር አካላት በተለያዩ ስብሰባዎች በተለያዩ ጊዜያት ካቀረቧቸው ሪፖርቶች የሠፈሩትን መነሻ በማድረግ የተወሰዱ ግምቶች ናቸው።

Digitized by Google

ዲሞክራሲ ከሚገለጽባቸው ገጽታዎች አንዱ ።

Digitized by Google

እንዲያደርግ ይቀሰቅሳል ፤ ያስተባብራል ። አባላት ልዩ ጥረት በማድረግ የተጓተቱ ተግባሮችን ለማፋጠን ፣ የተወዘፉ ሥራ ዎችን ለማቃለል የሚያስችሉ እንቅስቃ ሴዎችን ያደርጋል ።

በአጠቃላይ ከዕድሜው አጭርነት፣ ከል ምዱ አነስተኛነትና ከመሳሰሉት ሁኔታዎች አኳያ ሲገመገም የመላ ኢትዮጵያ ሠራ ተኞች ማኅበር በየደረጃው ባሉት አካላቱ አማካይነት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በቀ ላሉ የሚታይ አይደለም ።

የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር (መኢገማ)

የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር ቀደም ሲል በልዩ ልዩዎቹ ማኅበራት የወል ባሕርያት ውስጥ በተመለከተው መልክ የተደራጀ ሲሆን በየ20 ጋሻ መሬት ክልል የሚገኙ ገበሬዎችን ያሰባሰቡ ከ20 ሺህ በላይ መሠረታዊ ማኅበራት ወይም የቀበሌ ገበሬ ማኅበራት አሉት ። * ከዚ ህም ሌላ በአሁኑ ጊዜ ወደ 5,000 የሚ ጠጉ የወረዳና 95 የሚሆኑ የአውራጃ ፣ 14 የክፍላተ ሀገር አካላት ይገኛሉ ።

ቀደም ሲል በነበረው ምዝገባ መሠረት በሚታወቁት ከ20,000 በላይ በሆኑ መሠረ ታዊ ማኅበራት ው ስ ጥ በአሁኑ ጊዜ 5.5,000,000 ያህል የመኢገማ አባላት ይገ ኛሉ ። ከእነዚህ መካከል 430,156 (የፍርድ ሸንጎ አባላትንም ጨምሮ) በአመራር ደረጃ የሚሠሩ ናቸው ።

የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር ለዓ ላማዎቹ ተግባራዊነት ከሚያደርጋቸው በር ካታ እንቅስቃሴዎች መካከል የሚከተሉት ን መጥቀስ ይቻላል።የገጠሩን ኢኮኖሚ በሶ ሻሊስት ፈር ላይ በመምራት ረገድ ከፍተኛ ሚና ያላቸው የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ገበ

ኅብረት ለበለጠ ምርታማነት

---

* ይህ ቁጥር በሰፈራ መንደር የተቋቋሙትን አዳዲስ ማኅበራት የማይጨምርና በድርቁ ሳቢያ ምናልባት ሊፈርሱ የሚችሉትንም የሚያጠቃልል ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በሠፈራ መንደሮች የሚ ቋቋሙት የገበሬ ማኅበራት መሠረትና በሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የሚቋቋሙት የገበሬ ማኅበራት ሁኔታ የተለየ ስለሆነ የመሠረታዊ ማኅበራት ቁጥር ለውጥ ሊኖር ይችላል ።

Digitized by Google

የተባበረ ክንድ ተፈጥሮን ለመግራት

ሬውን ከመቀስቀስም ባሻገር ለማኅበራቱ
መጕልበት በተለያዩ መስኮች ቁሳዊ ድጋፎ
ችን ይሰጣል። በተመሳሳይ ሁኔታም ለአገል
ግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ጥንካሬና
በአጠቃላይም ለምርት ስርጭት ቅልጥፍናና
ውጤታማነት ገበሬው ጠቃሚ ድርሻ የሚ
ያበረክትበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት
ያደርጋል። ከዚህም በላይ ለእርሻ መግሪያ
ዎችና ለአስተራረስ ዘዴዎች መሻሻል፣
ለገጠር ልማት መስፋፋትና መፋጠን ገበ
ሬው የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በብቃት
እንዲወጣ ያግዛል።

በተበሌ፣ በወረዳና በአውራጃ ደረጃዎች
ባሉት የፍርድ ሸንጎዎች አማካይነት ገበሩ
ው እራሱን የሚዳኝበት ሁኔታ እንዲቀላጠፍ
ያግዛል። በአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች አማ
ካይነት ለአካባቢ ሰላምና ደኅንነት መረጋ
ገጥ ያላይናት አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በገጠር ለማይምነት መወገድና ለሙ
ተረ ጨና አገልግሎት መስፋፋት በየደረ
ጃው የሚገኙ የመኢገማ አካላት የሚያበ
ረክቱት ድርሻ የማይናቅ ነው። በአጠቃላ
ይም የገበሬውን ተሳትፎ ለሚጠይቁ የፓ
ርቲ ፖሊሲዎችና ለአብዮታዊው መንግ
ሥት መመሪያዎች ተፈጻሚነት እርሶ አደ
ሩን በማስተባበርና በማንቀሳቀስ ረገድ
መኢገማ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ግም
ት የሚሰጠው ነው።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበር (አኢወማ)

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅ
በር ከ3.6 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ከ15-30
ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣ
ቶችን ያሰባሰቡ ወደ 20,000 የሚጠጉ መሠ
ረታዊ ማኅበራት አሉት። ከእነዚህ ውስጥ
ከ18,000 በላይ የሚሆኑት በየ20 ጋሻ
መሬት ክልል የተመሠረቱና በየገጠሩ የሚ

Digitized by Google

ወጣቱ በምርታማ ሥራ

ገኙ ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ በከተሞች ውስጥ በየቀበሌ ደረጃ የሚገኙ ናቸው ። በመኖሪያ ክልል ከተመሠረቱት ሌላ የአባላቱ የሥራ ስምሪትና መኖሪያ እዚያው በሆነባቸው ዩኒቨርሲታዎች ፣ መለስተኛ ኮሌጆችና ልዩ ልዩ ማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥ 57 መሠረታዊ ማኅበራት ይገኛሉ ። ከዚህም በተጨማሪ እንደአስፈላጊነቱ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የኢሠማን ዓላማ ለማራመድ የወጣት ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ። ት/ቤት ውስጥ ያለ ወጣት የዚያ ት/ቤት የወጣት ኮሚቴ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ተሳታፊና ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል ። በአባልነቱ የሚመዘገበው ግን ባለበት ቀበሌ መሠረታዊ ማኅበር ነው ። በአሁኑ ጊዜ በዚህ መልክ በት/ቤቶች የተመሠረቱ የወጣቶች ማኅበር ኮሚቴዎችም ቁጥር ወደ 550 ደርሷል ። ከዚህም በተጨማሪ በፋብሪካዎች ፣ በመንግሥት እርሻዎችና እንደ ሁኔታውም በኮንስትራክሽን ቦታዎች ቁጥራቸው በርካታ የሆነ የወጣት ኮሚቴዎች ይገኛሉ ። የሠራተኞቹ መኖሪያና መስሪያ አንድ ቦታ ላይ በሆነባቸው ትላልቅ ፋብሪካዎችና የመንግሥት እርሻዎች ውስጥ 134 መሠረታዊ ማኅበራት ይገኛሉ ።

እንደተቀሩት ሕዝባዊ ድርጅቶች ሁሉ ኢሠማም በገጠርና በከተማ በተደራጁት መሠረታዊ ማኅበራት በተወከሉ አባላት አማካይነት የተመሠረቱ 604 * የወረዳ ኮሚቴዎች እንዲሁም 116** የአውራጃና 15 የክፍላተ ሀገር ኮሚቴዎች ይገኛሉ ። በዚህ መልክ በየደረጃው በተቋቋሙት ኮሚቴዎች ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች የተሰማሩ ወደ 450 ሺህ የሚጠጉ መሪዎች ይገኛሉ ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበር ድርጅታዊ መዋቅሩን በውጭ አገር

---

* ከዚህ ውስጥ 88ቱ የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው የከተሞች ወይም የከተማ ክፍሎች ወይም የትምህርት ተቋሞች ኮሚቴዎች ናቸው ።

** ከዚህ ውስጥ 14ቱ የአውራጃ ደረጃ የተሰጣቸው ከተሞች ወይም የከተማ ክፍሎች ናቸው ።

Digitized by Google

ችም የዘረጋ መሆኑ ይታወቃል ። በዚህም መሠረት በአውሮፓና በኩባ በድምሩ ወደ 9.000 አባላት ያሏቸው 14 የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅርንጫፍ ማኅበራት ተቋቁመዋል ።

እንደሚታወቀው አኢወማ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ15-30 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ወጣቶች በሙላ በአባልነት ለማሰባሰብ አልቻለም ። ይሁን እንጂ የቆመለት ዓላማ የሙላ ኢትዮጵያን ወጣቶች ጥቅም የሚያስጠብቅና አብዮቱን የሚያጠናክር ነው ። በዚህም መሠረት ወጣቱን ማኅበራዊ ጠቃሚነት ባላቸው ሥራዎች ላይ ለማሰማራትና አንዳንድ ፍላጎቶቹን በማሟላት ረገድ በየደረጃው የሚገኙት የአኢወማ አካላት የሚያደርጉት ትረት ብዙ መሻሻልና መጠናከር ቢኖርበትም በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።

አኢወማ የወጣቱን ንቃተ ኅሊና በማዳበርና ዕውቀቱንና ትኩስ ጉልበቱን ለኢኮኖሚና ለማኅበራዊ ልማት የሚያውልበት አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ የሚጫወተው ሚና አበረታች ነው ። በየክፍለ ሀገሩ የሚገኙ የአኢወማ አባላት በፋብሪካዎችና በመንግሥት እርሻዎች በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመት አገልግሎት ያበረክታሉ ። ከዚህ ሌላ በአካባቢ ጽዳት አጠባበቅና በሌሎችም የማኅበራዊ አገልግሎት መስኮች ተመሳሳይ ተሳትፎ ያደርጋሉ ። ለወጣቱ መደረግና መሆን ያለበት ጉዳይ ዋንኛ ባለቤት አኢወማ ቢሆንም በዚህ በኩል ሌላውም የኅብረተሰብ ክፍል የሚኖረው ኃላፊነት ቀላል አይደለም ። አኢወማ ዛሬ በሚገኝበት ደረጃ በዚህ አቅጣጫ ሊሰጠው የሚገባው ድጋፍ ወሳኝ ነው ።

የወጣቱን የመዝናናት ፍላጎት በማርካት በኩልም ገና ብዙ መጠናከር የሚቀረው ቢሆንም በአንዳንድ አካባቢዎች የተደራጁት ማዕከሎችና ተዛማጅ ዝግጅቶች ወጣቶችን ከአልባሌ ሥፍራዎች እንዲርቁ በማድረግ በኩል ጥሩ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው ።

የአካባቢ ንጽሕና ለጤንነት

Digitized by Google

መደራጀት የወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነትን ግዴታ ለመወጣት ያስችላል ። (ለደቡብ አፍሪካ ሴቶች የትግል አንድነት መግለጫ በአኢሴማ)

ባጠቃላይ አኢወማ ፣ ለኢሠፓና ለአብዮታዊው መንግሥት ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ተፈጻሚነት ወጣቶችን በማንቀሳቀስና በማሰለፍ ረገድ አበረታታች እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን በአገራችን ድርቅ ያስከተለውን ችግር ለመቋቋም በተቀየሱት የዕለት ዕርዳታ አሰጣጥና የመልሶ መቋቋም መርሐ ግብሮች አፈጻጸም ካበረከተው ጉልህ አስተዋጽኦ ለመረዳት ይቻላል ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር (አኢሴማ)

አኢሴማ በአሁኑ ጊዜ በ20339 መሠረታዊ ማኅበራት እና በመ/ቤቶች ፣ በት/ቤቶችና በማምረቻ ተቋሞች ውስጥ በተመሠረቱ 387 የሴቶች ኮሚቴዎች በላይ የተደራጁ ከ5 ሚሊዮን አባላት በላይ ያሉት ማኅበር ነው ። ከዚህ ውስጥ በአመራር አካላት ላይ ያሉ ከ250,000 በላይ ናቸው ። እንደተቀሩት ሕዝባዊ ድርጅቶች ሁሉ አኢሴማም በክልል የተደራጀ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ 588 * የወረዳ ፣ 111** የአውራጃና 15 የክፍለ ሀገር ኮሚቴዎች አሉት ።

አኢሴማ ለነደፋቸው ዓላማዎቹ መሟላት በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚያደርገው እንቅስቃሴ ውጤታማነት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መምጣቱ ይታያል ። የሴቶችን የቤት ውስጥ የሥራ ሸክም በማቃለል ረገድ (በተለይ በገጠር) አግባብ ካላቸው መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበርም በራሳቸው ጥረት የአኢሴማ አካላት ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ነው ።

* ከእነዚህ መካከል 34ቱ የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው ከተሞች ወይም የከተማ ክፍሎች ናቸው ።

** ከእነዚህ መካከል 10ሩ የአውራጃ ደረጃ የተሰጣቸው ከተሞች ወይም የከተማ ክፍሎች ናቸው ።

Digitized by Google

በዚህ በልኩ ዕቁራ ቤቶችን በመሥራትና በማስተዳደር ለሚጫወቱት ሚና የተለየ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው ። ይሁን እንጂ ካለው ችግርና ለችግሩም መቃለል የቤቶችን የማኅበራዊ ተሳትፎ አድማስ ለማስፋት የሚያስችል ዓይነተኛ ሁኔታ ከመሆኑ አኳያ በዚህ አቅጣጫ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበትና የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶችን የቅርብ ድጋፍና ትብብር የሚጠይቅ እን ደሆነ ይታያል ።

የኢሴማ አካላት የተለያዩ ጳጊና ጊዜያዊ የሙያ ማሠልጠኛ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የአባሎቻቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ፤ ለተሻለ አሠራርና ውጤት በማብቃት በኩልም አጥጋቢ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው ። በባልትና ፣ በጤና አጠባበቅ በተለይም ለልምድ አዋላጅነት የዘመናዊ አሠራር ድጋፍ በመስጠት የኢሴማ አካላት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ የሚያበረታታ ነው ። ከዚህም በተጨማሪ እንደሌሎቹ ሕዝባዊ ድርጅቶች ኢሴማ የአባላቱን ንቃተ ኅሊና ለማሳደግና ከአድኃሪና ከጐታች ባህሎችና ልምዶች ለማላቀቅ ርዕዮተዓለማዊ ሥራዎችን ያካሂዳል ። አባላቱን በመቀስቀስና በማስተባበር በኅብረተሰባችን ልዩ ልዩ መስኮች ለሚቀየሱ ትልሞች ተፈጻሚነት የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛል ።

የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰውና ከስማቸው ለመረዳት እንደሚቻለው የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት አገር አቀፍ ማኅበር ወይንም የክልል ማኅበራት የሌላቸው በአንድ ከተማ ክልል ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የሚመሠረቱ ማኅበራት ናቸው ። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ውስጥ ካሉት 300 የሚሆኑ ማዘጋጃ ቤት ያላቸው ከተሞች ውስጥ የተደራጁ ከ700 በላይ የሆኑ የቀበሌ ከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት፣ ወደ90 የሚጠጉ የከፍተኛ ከተማ ነዋሪዎች ማኅበራትና 27 አጠቃ

ሴቶች በማኅበራዊ ዕድገት መስክ

Digitized by Google

ላይ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት አሉ ። ከነዚህም ላይ በድምሩ ከ600 በላይ የሚሆኑ ልዩ ከፍተኞችና የልዩ ከፍተኞች ቀበሌዎችና ልዩ ቀበሌዎች ይገኛሉ ።

ኢትዮጵያ ውስጥ በከተማ ነዋሪነት የተመዘገበው ሕዝብ 4,742,855 [16] የሚደርስ ሲሆን ፣ የከነማት አባላት ቁጥር ከዚህ ያነሰ ነው ። ምክንያቱም የከነማት አባላት ቁጥር ልዩ ቀበሌዎች ሊኖራቸው በሚችሉ «ከተሞች» ውስጥ የሚገኙ ኗሪዎችን ስለማይጨምር ነው ። በከነማት አመራር ላይ ያሉ ገለሰቦች ወደ 30,000 የሚጠጉ ሲሆን ፣ ከነዚህ ውስጥ ከከፍተኞች ሊቃነ መናብርትና ከአጠቃላይ ከነማት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በስተቀር ከመደበኛ የሥራ ሰዓታቸው ውጭና በመንግሥት በተፈቀደው መሠረት በተወሰኑ ቀናች ከመደበኛ ሥራቸው ላይ እየተነሡ የሚያገለግሉ ናቸው ።

የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት በአንጋፋነት ከሚቆጠሩት ሕዝባዊ ድርጅቶች መካከል የሚገኙ ከመሆናቸውም በላይ ለአብዮቱ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱና በማበርከትም ላይ ያሉ መሆናቸው ይታወቃል ። የከተማ ነዋሪዎችን በመቀስቀስና በማስተባበር ለተለያዩ የግንባታና የልማት ሥራዎች መስፋፋት ከነማት የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ግልጽ ነው ። በኅብረት ሱቆችና በሌሎችም አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች አማካይነት መሠረታዊ ዕቃዎችን በማሰራጨት በኩል ጉልህ ድርሻ እያበረከቱ ከመሆናቸውም ሌላ የሰብሰባ አዳራሾችን ፣ ሙአለ ሕፃናትን ፣ የመዝናኛ ማዕከሎችና ሌሎችንም የማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋሞች በማደራጀት በኩል በሚያደርጉት ጥረት አበረታች ውጤቶች አስገኝተዋል ። በፍትሕ አስተዳደርና በአካባቢ ሰላምና ደኅንነት ጥበቃ በኩልም በየደረጃው በሚገኙ ፍርድ ሸንጎዎችና የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች አማካይነት ከነማት የሚጫወቱት ሚናም ሊጠቀስ የሚገባው ነው ።



የነገዎቹ የኅብረተሰብ ገንቢዎች ከፍተኛ እንክብካቤ ይሻሉ

Digitized by Google

እያንዳንዱ ሕዝባዊ ድርጅት የተቋቋመ
በት ዓላማ እውን ይሆን ዘንድ ያደረገው
ንና በማድረግ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ
በጥቅሉ ለማየት ተሞክሯል ። በዚህ ሙከራ
ውስጥ እንደተንፀባረቀው ሁሉም ሕዝባዊ
ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን ከመወጣት
አኳያ የሚያሳዩት በጎ ገጽታ ጉልህ ነው ።
ይህ መሆኑ ግን ምንም ዓይነት ድክመቶች
እንደሌሉ በመቁጠርና መወገድ የሚገባ
ቸው ችግሮችን በመዘንጋት አይደለም ።
ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ድክመቶች ከርዕ
ዮተዓለማዊ ብስለት ዝቅተኛነትና ከአስተ
ዳደራዊ ሥራ ልምድ ማነስ ጋር የተያያዙና
በአብዮቱ ሂደት የሕዝቡ ንቃት የሚገኝበ
ትን ደረጃ የሚያመለክቱ ከመሆናቸውም
ሌላ በተወሰነ መልካቸው ተጨባጭ ሁኔ
ታውን የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው በዚህ
በኩል የሚታዩት ችግሮች በመሠረቱ ነባ
ራዊ ናቸው ። [17] ከዚህ አንፃር የተገኙት
ውጤቶች ወይም የማኅበራቱ በጎ ገጽታ
ዎች በችግርነት ከሚታዩትና ከሚታወቁት
በርካታ ሁኔታዎች ጋር ሲነፃፀሩ ያለጥር
ጥር ጉልተው የሚገኙ ናቸው ።

የሕዝባዊ ድርጅቶች ሚና ከኢሠፓ ፕሮግራም አንፃር

በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ ያሉትም ሆነ ወደ
ፊት በብዛት ሊመሠረቱ የሚችሉት ሕዝ
ባዊ ድርጅቶች ሚና እንዴት ነው የሚታየ
ው ? በኢሠፓ ፕሮግራም የተመለከቱት
በኩረ ሐሳቦች ትርጓሜ ምንድን ነው ? በፕ
ሮግራሙ ላይ ምን ዓይነት ኃላፊነቶች ለሕ
ዝባዊ ድርጅቶች ተሰጥተዋል ? ለምን ?
እንደሚታወቀው ሁሉ በአንድ ፓርቲ ፕሮ
ግራም ውስጥ የሚንፀባረቁ ጉዳዮችና የሚነ
ደፉ ትልሞች ኅብረተሰቡ ከደረሰበት ደረ
ጃና ከወቅቱ ሁኔታዎች አኳያ የተለየ ግምት
የሚሰጣቸው መሠረታዊና አጠቃላይ ጉዳ
ዮችን ብቻ የሚመለከቱ ናቸው ። በዚሁ
መንፈስ በኢሠፓ ፕሮግራም ውስጥ ለሕ
ዝባዊ ድርጅቶች በአጠቃላይና በተናጠ
ልም ለእያንዳንዱ ሕዝባዊ ድርጅት የተለየ
ትኩረት ተሰጥቶ ምንና እንዴት መደረግ
እንዳለበት በጥቅሉ ተመልክቷል ። ፕሮግ
ራሙ ከሕዝባዊ ድርጅቶች የሚጠበቀውን
በማመልከት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ይል
ቁንም የሚፈለጉትን ሆነው ለመገኘታቸው
የሚያስፈልጋቸውን ጥንካሬ ለመጐናፀፍም
ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ በግልጽ አሳ
ይቷል ። ምክንያቱም «ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ
ጋር ከሚኖረው ግንኙነት አኳያ ዓይነተኛ
መድረኮች በመሆናቸው ነው ። የግንኙነ
ቱም ዓላማ በሠርቶ አደሩ ሕዝብ ቀጥተኛ
ተሳትፎ ላይ በሚመሠረተው አዲስ የፖለ
ቲካ ሥርዓት አካልነት የሚጠበቅባቸውን
ድርሻ በተሟላ ሁኔታ እንዲያበረክቱ ለማ
ስቻል ነው » ። [18]

ለኢሠፓ ፕሮግራም ተግባራዊነትና በው
ጤቱም ለአብዮታችን ከዘላቂ ግቡ መድ
ረስ በየደረጃውና በየአቅጣጫው ለሚከና
ወኑት ሥራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ መካ
ሄድና መሳካት በንቃት ላይ የተመሠረተ
ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው ። በታሪክ
ነባራዊ ዕድገት ሂደት መሠረት መፈጸም
ያለባቸው እውነታዎች በራሳቸው እንዲ
መጡ ሊጠበቁ አይችሉም ። በኅብረተሰብ
ዕድገት ነባራዊ ሕግጋት መሠረት መፈጸም
ያለባቸው ለውጦች እውን ይሆኑ ዘንድ በሳ
ይንሳዊ ፖሊሲዎች አማካይነት መመራ
ትን ይጠይቃል ። በንቃት ላይ የተመሠረተ
ተሳትፎ መኖር ዓይነተኛ መገለጫ ደግሞ
ድርጅት ነው ።

ሠርቶ አደሩን በንቃት በማንቀሳቀስ የኅ
ብረተሰቡን ፍላጎት ፣ የኅብረተሰቡን ዓላማና
ምኞት እውን ለማድረግ የሚካሄዱ እንቅ
ስቃሴዎችን ለመምራት ፣ በየአቅጣጫው
የሚደረጉ ጥረቶችን ለማስተባበርና በየመ
ስኩ የተጣሉ ትልሞችን በሥራ ለመተር
ጐም የሚችለው በተደራጀና በተቀናጀ
መልክ በሚንቀሳቀሱ በፖለቲካ ሥርዓት
የተለያዩ አካላት አማካይነት ነው ። ስለሆ
ነም በኢሠፓ ፕሮግራም ላይ በትክክል
እንደተመለከተው በፖለቲካ ሥርዓቱ አካ
ላት መካከል መኖር ከሚገባው መተሳሰር

Digitized by Google

እንፃር የየትኛውም አካል ድክመት ውጤት የፖለቲካ ሥርዓቱ ድክመት ይሆናል ። የእያንዳንዱ አካል ድክመትና ጥንካሬ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ስለሚኖረው የአንዱን ጥንካሬ ለማረጋገጥ የሚወሰድ እርምጃ ለተቀሩትም አስተዋጽኦ አለው ። [19]

ስለሕዝባዊ ድርጅቶች ዓላማ ፣ ጥንካሬ ፣ ወይም ድክመት ሲነገር እነሱ ከሌሎች የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ተነጥለው እንደታዩ መገመት የለበትም ። የእነሱ ድክመት ማለት የአጠቃላይ የፖለቲካ ሥርዓቱ ድክመት ማለት ነው ። የአንድ ሥርዓት አካላት የተቆላለፉ ፣ የተሳሰሩና እርስ በርስ የተደጋገፉ በመሆናቸው አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ ናቸው። በዚህም መሠረት ለሕዝባዊ ድርጅቶች የተሰጠው ኃላፊነትና ለመወጣትም ያላቸው ብቃት ከተቀሩት የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ድርሻ ጋር ምንም ዝምድና እንደሌለው ተደርጎ ብቻውን ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። ሕዝባዊ ድርጅቶች በፖለቲካ ሥርዓቱ አካልነታቸው የሚጠበቅባቸው ተግባር ፣ የፖለቲካ ሥርዓቱ አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ በየመስኩ የሚደረገውን ጥረት በማስተባበርና ባጠቃላይም መላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ በማንቀሳቀስ ከሚጠበቀው ውጭ የሚታይ አይደለም ።

እያንዳንዱን ሕዝባዊ ድርጅት በሚመለከት በኢሠፓ ፕሮግራም ውስጥ የተጠቀሱት ጉዳዮችም ቢሆኑ ከብዙ ነገሮች መካከል በሕዝባዊ ድርጅቶችና በፓርቲው መካከል ፣ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በመንግሥት መካከል ያለውን የዓላማ ግንኙነት የሚያንፀባርቁ ናቸው ። በመሠረቱ ማንኛውም ሕዝባዊ ድርጅት የቆመላቸው ዓላማዎች በአጠቃላይ ሲታዩ የመላው የኅብረተሰብ ዓላማዎች እንጂ የግሉ አይደሉም ። የፓርቲውን ፕሮግራም ተቀብሎ ለመሥራት የተዘጋጀ እንደመሆኑ ለዓላማዎቹ መሟላትና መሳካት በፓርቲውም ሆነ በመንግሥቱም በኩል አስፈላጊው ድጋፍ መኖር እንዳለበት ተገቢው ትኩረት እንደሚሰጠውና የፓርቲው አመራር እንደማይለይ በተደጋጋሚ መነገሩም ለዚህ ነው ።

ለምሳሌ ፣ ኢኢሴማ ለሴቶች እኩልነት መረጋገጥ ሴቶች በተለያዩ መድረኮች የሚያደርጉት ተሳትፎ መስፋትና መጉልበት ስለሆነ ይህን የማረጋገጥን ዓላማ ይዞ ተነሥቷል ። ለሴቶች እኩልነት በተጨባጭ መረጋገጥ በባህል ፣ በሕግና በመሳሰሉት አቅጣጫዎች ያለው ተጽዕኖ የሚወገድበትና ሴቶች የሚያደርጉት አስተዋጽኦ የሚያድግበት ሁኔታ ሕጋዊ መሠረቱ ምንድን ነው ? ለሚፈለገው ሁኔታ መፈጠር የሚያግዝ ምን ዓይነት ሕግ ይውጣ ? እነዚህንና መሰል ጉዳዮችን በሚመለከት ኢኢሴማ ጠቃሚ ሐሳቦችን ማቅረብ አለበት ። ከሁሉም ሕዝባዊ ድርጅቶች በላይ የሴቶችን ማኅበራዊ ችግር ለማቃለል ተገቢ ሐሳብ በማቅረብ ረገድ የሚጠበቅበት እሱ ነውና ። ይህም ሆና ኢኢሴማ የሚጠበቅበትን ሚና መጫወቱ ብቻ በቂ አይሆንም ። በፖለቲካ አመራር ሰጭው ፣ በሕግ አውጭውና በሕግ አስፈጻሚው መካከል የዓላማ አንድነት እስካለ ድረስ ኢኢሴማ ይዞት ለተነሣው ዓላማ ተግባራዊነት የኢኢሴማ ኃላፊነት ብቻ መሆን የለበትም ። ስለዚህ ለአባሎቻቸው ፍላጎትና ጥቅም መሟላትና ለአብዮታዊ አተስዋጽኦዋቸው ዕድገት ፣ ባጠቃላይም ለሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከርና መጐልበት ፣ የሚሰጠው ትኩረት በአንድ አቅጣጫ ብቻ የተወሰነ ሊሆን አይገባም ። ሕዝባዊ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ኢሠፓ ተገቢውን ትኩረት እንደሚሰጥ በፕሮግራሙ ውስጥ በተደጋጋሚ የገለጸውም በዚሁ ግንዛቤ ላይ በመመሥረት ነው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች ፓርቲውን ከሕዝቡ ጋር የሚያገናኙ ድልድዮች መሆናቸው በተደጋጋሚ ይነገራል ። ይሁንና ቀ ደ ም ሲል እንደተገለጸው በተለምዶ እንደሚታሰበው ሕዝባዊ ድርጅቶች በድልድይነት የሚጫወቱት ሚና የአንድ አቅጣጫ ብቻ

Digitized by Google

አይደለም ። የፓርቲውን ፖሊሲ በሥራ በመተርጐምና በአባሎቻቸው ፍላጎት አንፃር በመተንተን ለተፈጻሚነቱ አባሎቻቸውን የማንቀሳቀስ ብቻ ሳይሆን የአባሎቻቸውን ስሜት ፣ አስተያየት ፣ ፍላጎትና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለፓርቲው የማድረስ ሚናም አላቸው። የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ፍላጎት ምንድን ነው? በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ምን አስተያየት አለው? ምን ማድረግ ይቻላል? ከልዩ ልዩ ጉዳዮችና ሁኔታዎች አኳያ ስሜቱ ምንድን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ፓርቲው በቅርብና በትክክል ሊረዳ የሚችለው ከሕዝቡ ጋር በሚያገናኙት ድልድዮች አማካይነት ነውና ለፖሊሲዎቹ ተፈጻሚነት በእነሱ የመጠቀሙን ያህል የሕዝቡን ፍላጎትና ስሜት ለማወቅም በእነሱ መጠቀም አለበት ። ለብቃታችን መረጋገጥ ትኩረት የሚሰጠውም በተለይ በዚህ አቅጣጫ የሚጫወቱት ሚና አስተማማኝና የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ ነው ።

በየሕዝባዊ ድርጅቱ የተሰባሰቡት አባላት ፍላጎታቸውንና ጥቅሞቻቸውን ለማሟላትና ለፓርቲውም ሆነ ለመንግሥት መመሪያዎችና ፖሊሲዎች ተፈጻሚነት ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች መድረክነትና አስተባባሪነት ታላቅ ድርሻ አለው ። በፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት መሠረታዊ ዓላማዎች አኳያ ቅራኔ ስለሌለ በመካከላቸው የሚኖረው የሥራ ክፍፍል መመዘኛ በተለይ ጥራትንና ቅንጅትን የሚመለከት ነው ። ስለዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች ባላቸው ባሕርይ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በስፋት በማንቀሳቀስ የተሻለ ውጤት ሊያስገኙላቸው ይችላሉ የሚባሉ ተግባሮች ከመንግሥት ሊተላለፉላቸው ይችላሉ ።

በዚህ ምክንያትና ከዳበሩ ሶሻሊስት አገሮች ልምድ ለመረዳት እንደሚቻለውም 1 ቀደም ሲል በመንግሥት ሲከናወኑ የነበሩ በርካታ ተግባሮች ወደ ሕዝባዊ ድርጅቶች እየተሸጋገሩ ነው ። ስለሆነም በኢሠፓ ፕሮግራም ላይ በተመለከተው መሠረት ሕዝባዊ ድርጅቶችን በማጠናከርና በማሳደግ ሚናቸውን በጥራት እንዲጫወቱ ማድረግ የሚያርብኝ ወደፊት ለምንመሠርተው ኅብረተሰብ ጠንካራ መሠረት ለመጣልና የምሥረታውን ሂደት ለማፋጠን ነው ። ስለሆነም ዛሬ የሚሠራው ሥራ እንዲሁ የሚያልፍና ፣ ከነገው ጋር ምንም ዝምድናና ግንኙነት የሌለው ሳይሆን ይልቁንም የነገው ጥንካሬያችን ዋስትና ዛሬ ከምንጥለው መሠረት የሚመነጭ ነው ። ለሕዝባዊ ድርጅቶቹ ጥንካሬ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጥ የሚገባውም ለዚህ ነው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች ማድረግ ላለባቸው ሁሉ ያልተቆጠበ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ለሠፊው ሕዝብ ታሪክ ሠሪነት ዓይነተኛ መግለያ በመሆናቸው ነው ። በኢሠፓ ፕሮግራም ላይ እንደሠፈረው ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ታሪክ ሠሪነት መሠረት የሆነው ተሳትፎ « ወሳኝነት የሚመነጨው ከሕዝቡ ቁጥር ከፍተኛነት ብቻ ሳይሆን በንቃት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ከመቻሉ ነው።ይህም ተጨባጭ ይሆን ዘንድ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መደራጀት መሠረታዊ ጉዳይ ነው።» [20] ከዚህም በላይ ሕዝባዊ ድርጅቶች በኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ መስኮች በሚያደርጉት ተሳትፎ ስፋት የፖለቲካዊ ዲሞክራሲ ዕድገት ተጨማሪ ማረጋገጫ እንደመሆኑ በኢሠፓ ፕሮግራም ውስጥ ለሕዝባዊ ድርጅቶች ጥንካሬና ዕድገት ከፍተኛ ግምት እንዲሰጥ ተደርጓል ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በዚህ በኩል የሚጫወቱትን ሚና ይበልጥ ጉልህ የሚያደርገው የሕዝባዊ ፖለቲካ ሥርዓት ዲሞክራሲያዊነት ዓይነተኛ ማረጋገጫ በሆነው በመንግሥታዊ ተግባር ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በመንግሥታዊ ተግባሮች መሳተፍ ብቻ ሳይሆን ሕዝባዊ ድርጅቶች የመንግሥታዊ ተግባሮች ባለቤት የሚሆኑበት መስከ ስፋት ለሶሻሊስት ዲሞክራሲ ዕድገት ዋነኛ ማስረጃ ነው ። [21]

ስለዚህ በሕዝባዊ ድርጅቶች ጥንካሬ ላይ ተገቢውን ትኩረት ማድረግና ተጨባጭ ድጋፍም መስጠት ፣ ለሶሻሊስት ዲሞክራሲ መስፈን መሠረት በመጣል ረገድ የሚደረገው

Digitized by Google

ጥረት ዋንኛ አካል መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሶሻሊስት ዲሞክራሲ ስፋት ደረጃ አንዱ መለኪያ የሕዝባዊ ድርጅቶች የመንግሥታዊ ተግባሮች ባለቤትነት መጠን ቢሆንም ከዚህ በመለስ የሚኖራቸውም ድርሻ ቀላል ግምት የሚሰጠው መሆን የለበትም ። በበርካታ መንግሥታዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ለተወሰኑ መንግሥታዊ ተግባሮች ባለቤትነት የሚያበቃቸው ጠቃሚ መለማመጃ በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነው ።

ከሁሉም ሶሻሊስት አገሮች ልምድ እንደሚታየው ሕዝባዊ ድርጅቶች መንግሥታዊ ተግባሮችን በባለቤትነት ከመረከብ፣በመለስ በልዩ ልዩ መንግሥታዊ ክንዋኔዎች ውስጥ ቀጥተኛ ተካፋይ ናቸው ። በዚህም መሠረት ፣ ልዩ ልዩ ሕጎችና መንግሥታዊ ፖሊሲዎች እንዲወጡ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ ። ረቂቆችንም በማዘጋጀት እንዲጸድቁ ያቀርባሉ ፤ ከዚህም በተጨማሪ በእነርሱ አሳሳቢነት ወይም ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ሕጎችና ደንቦች ተፈጻሚነት በሕግ የተወሰነ ድርሻ አላቸው ። በዚህ ረገድ በአካባቢ ሰላምና ደኅንነት ጥበቃና በግለሰቦች መካከል ጤናማ የርስበርስ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያግዙ ዳኝነት ነክ ተግባሮችን በማከናወን ከፍተኛ ድርሻ ያበረክታሉ ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በሕጎችና በደንቦች ወይም በልዩ ልዩ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ዝግጅት የሚኖራቸው ተሳትፎ ከራሳቸው አነሣሽነት የሚመነጭ ብቻ አይደለም ። እንደሁኔታውና እንደአስፈላጊነቱ በዝግጅት ውስጥ ሐሳብ የማቅረብ ፣ የሚመለከተውን የመንግሥት አካል የማማከር ፣ ወይም በጋራ ውሳኔ የሚሰጡበት ሁኔታ በሕግ ይደነገጋል ። 22 ይህም ስልት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ከመደረሱ በፊት ፣ እንደሁኔታው በተለያየ መልክ የሚገለጽን የሕዝባዊ ድርጅቶች ተሳትፎ ግዴታ የሚያደርግ በመሆኑ የሚጫወቱትን ሚና የሚያሳድግ ዋና መሣሪያ ነው ።

በኢትዮጵያም ውስጥ ይህን የመሰለ ስልት ከሞላ ጎደል ተግባራዊ ለማድረግ እየተሞከረ ቢሆንም በአፈጻጸም ረገድ ያሉት ችግሮች ካልተወገዱ በስተቀር የሚፈለገውን ያህል ውጤት ለማስገኘት ያዳግታል ። ስለሆነም ጓድ መንግሥቱ ኃይለማርያም እንዳስገነዘቡት ሕዝባዊ ድርጅቶችን ስለማጠናከር በሚመለከት ያሉት ችግሮች ተወግደው አስፈላጊው ብቃት ይኖራቸው ዘንድ የራሳቸው ጥረት በፓርቲውና በአብዮታዊው መንግሥት ድጋፍ ሊዳብር ይገባዋል ። 23

ለሕዝባዊ ድርጅቶች ይበልጥ መጠናከር ምን መደረግ አለበት ?

ሕዝባዊ ድርጅቶች ሚናቸውን በሚፈለገው ስፋትና ጥራት እንዲጫወቱ ምን መደረግ አለበት? መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው ? እነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከመሞከራችን በፊት ቀደም ሲል ተነሥተው የነበሩ አንዳንድ ነጥቦችን በድጋሚ ማውሳቱ ይጠቅማል ።

በፓርቲያችን ፕሮግራም ላይ እንደተመለከተውና ቀደም ብሎም እንደተጠቀሰው የሕዝባዊ ድርጅቶች ጥንካሬም ሆነ ድክመት ከአጠቃላይ ፖለቲካ ሥርዓት አካላት ውጭ ሊታይ የሚችል አይደለም ። ለሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከር እያንዳንዳቸው የራሳቸው ድርሻ አላቸው ። ለሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከርና ከጉድለታቸው ለመጽዳት እርምጃ መውሰድ የሚገባቸው ፓርቲው፣መንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅቶች እራሳቸው ናቸው ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝባዊ ድርጅቶችን ለማጠናከር ምን መደረግ እንዳለበት ሲታሰብ አንድ በሚገባ መታየት ያለበት ጉዳይ አለ ። ይኸውም ሕዝባዊ ድርጅቶች ራሳቸውን የቻሉ ፣ የራሳቸው ሕጋዊ ሕልውና ያላቸው ድርጅቶች መሆናቸውን በሚመለከት ያለው የግንዛቤ ጉድለት ነው። የሕዝባዊ ድርጅቶች እራሳቸውን የቻሉ አካላት የመሆን ሕጋዊ ገጽታ በጣም እየተጋነነ ከተነሣንበት ኋላቀር የፖለቲካ ባህል አኳያ ሊኖሩባቸው የሚችሉትን ጉድለቶች ለማስ

Digitized by Google

ወገድ በአግባቡ በግጤን መደገፍ እንዳለባቸው የመዘንጋት ሁኔታ ይታያል ። በሕዝባዊ ድርጅቶች አካባቢ ለሚያጋጥሙ ጉድለቶች መወገድና ይበልጥም ተጠናክረው እንዲገኙ ለማድረግ በዚህ በኩል ያለው የግንዛቤ ችግር መስተካከል በጣም አስፈላጊ ነው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በየራሳቸው መዋቅር ከሌላው ተለይተው የተደራጁ የራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት ቢሆኑም በማስፈጸም ረገድ በማንኛውም ጉዳይ እራሳቸውን ችለው ለመገኘት ገና ብዙ ይቀራቸዋል። «ሕዝባዊ ድርጅቶች ሲመሠረቱና ከተለያዩ የፓርቲና የመንግሥት አካላት ጋር በአንድነት የሚሠሩበት ሁኔታ ሲወጠን ... በግንኙነቱ ሂደት ውስጥ እየተማሩና እያስተማሩ ከሚፈለገው ደረጃ ላይ እንደሚደርሱ በመገመት እንጂ በሕዝባዊ ድርጅቶች አመራር ውስጥ የሚታዩትን አንዳንድ ድክመቶች ምክንያት በማድረግ በጋራ መሥራት ባለባቸው ተግባሮች ውስጥ እንዳይሳተፉ የሚደረግ ከሆነ መመሥረታቸውም ባላስፈለገ ነበር።» [24] ስለዚህ የተሳሳቱ አመለካከቶች ተስተካክለው ሕዝባዊ ድርጅቶች መሥራት የሚችሉትን ሁሉ በሚፈለገው ጥራትና ጥንካሬ እንዲሠሩ የራሳቸውን ጥረት፣የፓርቲውንና የመንግሥትን ድጋፍና እገዛ ይፈልጋሉ ማለት ነው ። እንዲያውም አሁን ባለንበት የመነሻ ጊዜ ለሥራቸው ውጤታማነት ከራሳቸው ጥረት ይልቅ በመንግሥትና በፓርቲ በኩል የሚሰጣቸው ድጋፍ ወሳኝ ነው ። እስከአሁንም በአብዮታዊው መንግሥት የተሰጣቸው ቁሳዊ ድጋፍ ባይኖር፣ ለሚያደረጉት እንቅስቃሴ እንኳ ባልበቁም ነበር ። በሚሊዮን ከሚቆጠሩ አባላት እንደሚገኝ የሚገመተውን መዋጮ ገና በሚገባ ለማሰባሰብ ባለመቻሉ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ እጥረት ይታያል ። ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የሚያስችላቸውን የሠለጠነ የሰው ኃይል በማግኘት በኩልም ችግር እንዳለባቸው ይታወቃል ። ስለዚህ ይህንን ችግር ለማቃለል፣ በመንግሥት በኩል በተለያዩ መንገዶች ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል ። በፓርቲውም በኩል የተለያዩ ርዕዮተዓለማዊ ሥልጠናዎች በማደራጀት ይበልጥ ማገዙና ጠቃሚ ልምድ የሚያገኙበት አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ማድረጉ ተገቢ ነው ። ይህ ካልተሟላ በስተቀር በሚፈለገው ፍጥነት ሊራመዱና የሚፈለግባቸውን ውጤት በአፋጣኝ ሊያከናውኑ ይችላሉ ማለት ያስቸግራል ።

ከዚህ በላይ የተነሡትን አጠቃላይና መሠረታዊ ነጥቦች መንደርደሪያ በማድረግ የሕዝባዊ ድርጅቶችን ብቃት ለማሳደግ መወገድ ያለባቸውን ድክመቶችና መሟላት ያለባቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ይዘትና ክብደት መረዳት አዳጋች አይሆንም ።

ቀደም ብሎ በተጠቀሱትና በሌሎችም ምክንያቶች በአገራችን ውስጥ የሚገኙት ሕዝባዊ ድርጅቶች ድክመቶችና ጉድለቶች ያሉባቸው ቢሆንም ጥንካሬ አይታይባቸውም ማለት አይደለም ። ስለድክመቶቻቸው መወገድ የሚነገረው በአብዛኛው እየሰፋ ለመጣው ኃላፊነታቸው ብቃት እንዲኖራቸው፣ የበለጠ እንዲጠናከሩ ለማመልከት እንጂ ዛሬ ባሉበት ሁኔታ ፋይዳ የላቸውም የሚያሰኝ አይደለም ። የችግሮቻቸው መሠረት ጥልቅና ውስብስብ በመሆኑ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሊወገድ ባለመቻሉ እንጂ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በተወሰዱት ተከታታይ እርምጃዎች የተገኙት ውጤቶች እንኳ በቀላሉ የማይገመቱ ናቸው ። ከጊዜ ወደ ጊዜ በራሳቸው አነሣሽነት የሚሠሯቸው ሥራዎች እየተበራከቱና እየሰፉ መጥተዋል ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በውጭ ግንኙነት መስክ የሚያደርጉት እንቅስቃሴም ከፍተኛ ውጤት እያስገኘ ነው ።

ከዚህ በላይ ከምሥረታቸው አንሥቶ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ በየወቅቱና በተለያዩ መስኮች ከተካሄዱት እንቅስቃሴዎች መካከል ሕዝባዊ ድርጅቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያላበረከቱበት አንድም መስክ እንደሌለም ይታወቃል ። በመሆኑም በተለያዩ መስኮች አብዮታችን ላስገኛቸው ውጤቶች

ሙሉ ባለድርሻ መሆናቸውም አሌ የሚባል አይደለም ።

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በሕዝባዊ ድርጅቶች አካባቢ የሚታዩትን ድክመቶችና ጉድለቶች ለማስወገድ በሕዝባዊ ድርጅቶች በራሳቸው በኩል የተወሰኑ ሁኔታዎች መስተካከልና መለወጥ አለባቸው ። በመንግሥታዊ አካላት በኩል መፈጸም ያለባቸውም ጉዳዮች አሉ ። በፓርቲው በኩል ሊታሰብባቸውና ሊሟሉ የሚገባቸው ሁኔታዎችም አሉ። በተጨማሪም ከሕዝባዊ ድርጅቶች መላ አባላት አኳያም መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ ። በተለያዩ አቅጣጫዎች ሊታዩ የሚችሉት ድክመቶች አንዱ ለሌላው ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ጥረቱ በተቀናጀ መልክና በጋራ መከናወን ይኖርበታል ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች በራሳቸው በኩል ሊያስወግዷቸው የሚገቡ ድክመቶች

በሕዝባዊ ድርጅቶች በኩል በራስ አነሣሽነት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ ቢሄዱም ሙሉ በሙሉ በሚፈለገው መስክና ዓቅም በሚፈቅደው መጠን ነው ማለት ያስቸግራል ። በተለይ የአብዮቱን ሂደት ለማፋጠን ወደፊት ከሚጠብቀን ተግባር አንጻር ሕዝባዊ ድርጅቶች በራሳቸው አነሣሽነት መሥራት ያለባቸው ተግባሮች ብዙ ናቸው ። ደግሞ በራስ አነሣሽነት ለመሥራት ችሎታ ፣ ዕውቀትና፣ልምድ የሚጠይቅ እንደመሆኑ እነዚህን ሁኔታዎች የማሟላቱ ጥያቄ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሊታይ ቢችልም በዚህ በኩል ያለው ድክመት ጉልህና ማኅበራቱ የሚኖራቸው ተጠያቂነትም ቀላል አይደለም ።

ሕዝባዊ ድርጅቶቹ ለተለያዩ ተግባሮች ተፈጻሚነት አባሎቻቸውን በማንቀሳቀስ የቆሙለትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ሲያደርጉ የሚታይባቸው ድክመት በአፋጣኝ መወገድ ይኖርበታል ። በተለያዩ ሁኔታዎች ተስማሚ የአሠራር ስልት በመቀየስ በኩልም ድክመት አለ ። ከዚሁ ጋር በሌላ የመተማመን ወይንም በሌላ ላይ የመመርኮዝ መንፈስ ብዙ ቦታ ይታያል ። ሁሉም ነገር የሚሠራው በመመሪያ ብቻ እንደሆነ በመገመት ሁል ጊዜ የበላይ አካልን መመሪያ መጠባበቅ ወይም ከላይ የተላለፉ ተመሳሳይ መመሪያዎችን እንደተጨባጩ ሁኔታ በተለያዩ ዘዴዎች አማካይነት ተግባራዊ አለማድረግ በሰፊው ይታያል ።

በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በስፋት የሚንጸባረቀው ሌላው ድክመት ግብታዊነት ነው በስሜት ብቻ በመገፋፋትና አንድን ጉዳይ በተለያዩ አቅጣጫዎች ሳይገመግሙ በግርድፉ ብቻ አይቶ እርምጃ የመውሰድ ወይም አቋም የመያዝ ዝንባሌዎች በአፋጣኝ ሊወገዱ የሚገባቸው ሲሆን ፣ ለብዙ ድክመቶች ምክንያት የሆኑትና በመሪዎች አካባቢ አልፎ አልፎ የሚንጸባረቁት የመሳነፍ ስሜቶችም ባልተቆጠበ ታታሪነት መተካት አለባቸው ። በዚህ በኩል ላለው ጉድለት ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም እየከበዱ ከመጡት ኃላፊነቶች አንጻር ብቁ ሆኖ ለመገኘት ተገቢው ጥረት መደረግ ይኖርበታል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ በዝቅተኛ ደረጃዎች በስፋት የሚታየው የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች ቢሮክራሲያዊ አመለካከት ለማኅበራቱ መሠረታዊ ባሕርይ ባዕድ የሆነና በአፋጣኝ መወገድ ያለበት አዝማሚያ ነው ። የዚህ ችግር ዋንኛ ምክንያት የሕዝባዊ መሪነትን ትርጉም በትክክል አለመረዳትና ኃላፊነትን ለመወጣትና ሥራን ለማስተባበር ተገቢ ስልት መከተል አለመቻል ነው ። በአመራሩና በተከታዩ መካከል የአንድነት ስሜት ለመፍጠርና ለማሳመን ሳይሞከር በግብታዊ አስተሳሰብ በመመራት ወይም በጭፍንና ትዕቢት በተመላበት ሁኔታ ለማሠራትና ለማስተባበር መሞከር በሕዝባዊ አመራር ውስጥ ፍጹም ቦታ ሊኖረው የማይገባው ድርጊት ነው ፤ በዚህ የተሳሳተ አመራር በቅርጽ ላይ በማተኮር ሥነ ሥርዓትን ከመሠረቱና ከጠቀሜታው አንጻር ከመረዳት ይልቅ በራሱ ብቻ የመውሰድና እንዲያውም

Digitized by Google

በሥነ ሥርዓቱ ሊንጸባረቅ ለሚገባው ይዘት ደንታ ማጣት ይታያል ። ይህም ከአንድ ሕዝባዊ አመራርና አሠራር የማይጠበቅና መወገድ ያለበት ችግር ነው ።

ሌላው መወገድ ያለበት ድክመት በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ እንዲከናወን የሚጠበቅ ተግባር ሁሉ በአመራር ላይ ያሉት ጥቂት ግለሰቦች ኃላፊነት እንደሆነ ተደርጐ መወሰዱ ነው ። በዚህ ምክንያት በየሕዝባዊ ድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ ዕውቀት ፣ ሙያና ልምድ ያላቸው አባሎች ተሳትፎ ወይም የመሳተፍ ሁኔታ ይህን ያህል ተስፋፍቶና ተጠናክሮ አይታይም ። ይህ ድክመት በተለይ በከፍተኛ ደረጃ ያሉትን አመራር አካላትና ባብዛኛውም መኢሠማን ፣ አኢወማንና አኢሴማን የሚመለከት ነው ። በአመራር ደረጃ የሚገኙ ግለሰቦች ኃላፊነታቸው አቅጣጫ ማመልከት ፣ ማስተባበር ፣ ሥራን ማቀነባበርና ጥረቶችን ማቀናጀት እንጂ መደረግ ያለበት ሁሉ ከእነርሱ እንደሚጠበቅ ማሰብ አይኖርባቸውም ። በዚህ ረገድ ሕዝባዊ ድርጅቶች የአባሎቻቸውን ዕውቀትና ችሎታ ለመጠቀም ምንም ሙከራ አላደረጉም ለማለት ሳይሆን አብዮቱን የበለጠ ለማጠናከር በሚረዳ ስፋትና የቋሚነት ባሕርይ አለመሆኑን ለማመልከት ነው ።

ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የሕዝባዊ ድርጅቶች አመራር ከአባላቱ ጋር ያለው ግንኙነት የሚፈለገውን ያህል የተቀራረበ አለመሆን ነው ። የሕዝባዊ ድርጅቶች አንዱ ዋንኛ ዓላማ የአባሎችን ጥቅም ማስከበር ሆኖ ሳለ ከአባሎቻቸው ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለመኖር ከፍተኛ ድክመት ነው ። ሌላው ቢቀር የአባሎቻቸውን ጥቅም ለማስከበር የሚያደርጉት ጥረት በአባሎቻቸው ዘንድ እንዲታወቅና ከአባሎቹ ከራሳቸው የሚጠበቅ ጉዳይ ካለም ይህን ለማስረዳት የተቀራረበ ግንኙነት መኖር ወሳኝ ነው ። ለግንኙነቱ መቀራረብ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና ማኅበራቱ ሊያሰባስቡ በሚችሏቸው ሰዎች ዘንድ ያላቸው ተወዳጅነትና ተቀባይነት ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው ነው ።

ሕዝባዊ ድርጅቶች የቆሙለት ዓላማ ብቻውን በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ሊያስገኝላቸው እንደማይችል ግልጽ ነው ። ስለሆነም ሕዝባዊ ድርጅቶች በአባሎቻቸው ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ እንዲሆኑና ተጨማሪ አባላትን ለማፍራት እንዲችሉ የአባሎቻቸውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ። የዚህም ጥረት ውጤታማነት ለማኅበራቱ ተወዳጅነትን የማትረፍ ብቻ ሳይሆን የጥንካሬአቸውም ዋንኛ ምንጭ ከአባሎቻቸው የሚያገኙት ድጋፍ በመሆኑ የአመራር አካላት ሁኔታ ምን ጊዜም ቸል ሊሉት አይገባም ።

ለመወገዳቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች ተቀዳሚ ኃላፊዎች ከሚሆኑባቸው ዋና ዋና ድክመቶች መካከል ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ጠቃቅሰናል ። ይሁንና እነዚህ ችግሮች የሚኖሩበት ስፋትና የአሳሳቢነት ደረጃ እንደ የሁኔታው ሊለያይ የሚችልና ምናልባትም በአንዳንድ አካባቢዎች የሌሉ ወይም ያልነበሩ ፣ ከነበሩም የተወገዱ ሊሆኑ ይችላሉ ። በዚህም ምክንያት ችግሮቹ በሁሉም ሕዝባዊ ድርጅትና በማንኛውም ደረጃ እንዳሉ ተደርገው መታየት የሌለባቸው ናቸው።

በመንግሥታዊ አካላት በኩል መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

በዚህ በኩል ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮች በአብዛኛው ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው የሕዝባዊ ድርጅቶችን ምንነትና የሥራ ድርሻ በትክክል ካለመረዳትና ባጠቃላይም ከግንዛቤ ጉድለት ካልሆነ በስተቀር በመሠረቱ የመመሪያ ጉድለት ያስከተላቸው አይደለም ። ይሁንና ለሕዝባዊ ድርጅቶች አስፈላጊውን እገዛ አለመስጠት በአንዳንድ መንግሥታዊ አካላት ውስጥ የሚታይና በአፋጣኝ መወገድ ያለበት ችግር ነው ። አንዳንድ መንግሥታዊ አካላት ሕዝባዊ ድርጅቶችን

Digitized by Google

የሚመለከቱ ድርጊቶች በሚፈጸሙበት
ወይም ውሳኔዎች በሚሰጡበት ጊዜ የሕዝ
ባዊ ድርጅቶችን አካላት አስተያየት ወይም
ሐሳብ አይጠይቁም ። በዚህ መልክ እነሱ
ያልተሳተፉበት ፤ እነሱ የማያውቁት ነገር
ተፈጽሞ ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ግን ችግ
ሩን ለማስወገድ ጥሪ ይቀርብላቸዋል ። ይህ
በተለያዩ ደረጃዎች በተደጋጋሚ የታየና
ቀስ በቀስ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም
አሁንም ሙሉ በሙሉ ያልተወገደ ችግር
ነው ። ሕዝባዊ ድርጅቶች በየሚመለ
ከቷቸው ጉዳዮች ላይ ሐሳብ በመስጠት ፥
መፍትሔ በማመንጨት በተለያዩ ምክንያ
ቶች ይህን ያህል የጐላ አስተዋጽኦ ሊያደ
ርጉ የማይችሉባቸው ነገር ግን የሚመለከቷ
ቸው ጉዳዮች ለውይይት በሚቀርቡበት ጊዜ
እንዲሳተፉ ቢደረግ በአፈጻጸም ደረጃ
ለሚጠበቅባቸው ኃላፊነት በተሻለ እንደ
ሚያዘጋጃቸው እሙን ነው ። ስለዚህም
ሕዝባዊ ድርጅቶች « እየሠሩ የሚማሩ፥
እየተማሩ የሚሠሩ መሆናቸውን በመገን
ዘብ ለዚህ ጣምራ ክንዋኔ የተሻለ ዕውቀትና
ዝግጅት ካለው ወገን ሁሉአቀፍ ድጋፍ ጋር
በሚመለከታቸው ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸ
ውን ተሳትፎ ማሳደግ ያስፈልጋል ።» [25]

በሕዝባዊ ድርጅቶች በኩል ያሉት ችግሮች
እንዲወገዱ መርዳት እንጅ ከድክመቶቻቸው
ሳይላቀቁ እንዲቀመጡ ገለል ማድረግ መፍ
ትሔ እንደማይሆንና በመሠረቱም የተሳሳተ
መሆኑን መገንዘብ ይገባል ።

ለሕዝባዊ ድርጅቶች ይልበጥ መጠናከር
በመንግሥታዊ አካላት ሊታሰብበት የሚገ
ባው አንዱ ጉዳይ ባለሙያዎችና ልዩ
ቴክኒካዊ ድጋፎችን የሚመለከት ነው ።
በዚህም በኩል ምንም በጐ እርምጃ አልተ
ወሰደም ለማለት ሳይሆን የበለጠ ተጠናክሮ
መቀጠል እንዳለበት ለማመልከት ነው ።

እንደሚታወቀው በአሁኑ ጊዜ ሕዝባዊ
ድርጅቶች በተመራጮቻቸው በተለይም
ሙሉ ጊዜያቸውን ለማኅበራቱ ሥራ በሚያ
ውሉት ብቻ ተግባራቸውን የሚያከናውኑ
አይደሉም። በመሆኑም ለየሥራ ባሕርያቸው
ተስማሚና ተመጣጣኝ ሙያ ያላቸው ቅጥር
ሠራተኞች ስለሚያስፈልጋቸውና ባላቸው
ዓቅም ደግሞ ሁሉንም ሙያተኞች ለመቅጠ
ር ስለማይችሉ በዚህ በኩል ለሕዝባዊ ድር
ጅቶች በመንግሥታዊ አካላት የሚደረገው
እገዛ መስፋፋት አለበት ። ከዚህም በተ
ጨማሪ በመንግሥታዊ መመሪያ በተወሰነው
መሠረት ለአንዳንድ ሕዝባዊ ድርጅቶች ተ
መራጮች ከመደበኛ ሥራ ነጻ እንዲሆኑ የሚ
ሰጣቸው ቋሚ ፍቃድ እንደአስፈላጊነቱ ለሁ
ሉም ማኅበራት ተፈጻሚ እንዲሆን መደረጉ
ጠቃሚ ነው ።

በፓርቲው በኩል መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

የሕዝባዊ ድርጅቶችን አመራር በሚመለከ
ት ሊጠቀሱ የሚችሉ ድክመቶች በአመዛኙ
ከመሪዎቹ ርዕዮተዓለማዊ ብቃት ማነስ፥
ከትክክለኛ አመራር ስልቶች ጋር በጥልቀት
አለመተዋወቅ ነው ። ቀደም ሲል የተጠቀ
ሱት ቢሮክራሲያዊነትና የመሳሰሉት የኢሕ
ዝባዊ አሠራር ስልቶች ምንጭም ይኸው
ነው ። ስለሆነም የሕዝባዊ ድርጅቶች አመ
ራር መሠረታዊ መለያ በሆነው የማስተማ
ርና የማሳመን ጥረት በፈቃደኝነት ለሥራ
ማሰማራት እንዲቻል የመሪዎቹን ርዕዮተ
ዓለማዊ ብቃትና የመምራት ችሎታ ለማ
ሳደግ በፓርቲው በኩል ያልተቆጠበ ትኩ
ረት መስጠት ያስፈልጋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝባዊ ድርጅቶችን
ጥንካሬ ለማረጋገጥና በነርሱም አማካይነት
ፓርቲው የራሱን የአመራር ሰጪነት ሚና
ለማሳደግ በየደረጃው ባሉት አካላቱ አማካይ
ነት የቅርብ ድጋፍና ክትትል ማድረጉ በጣም
አስፈላጊ ነው ። ከዚህም በላይ ፓርቲው በሕ
ዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ አባላቱን ማበራከት
አለበት ። ዛሬ የክልል አካላት የሚፈለገውን
ያህል በየአካባቢው ሊመሠረቱ ባልቻሉበት
ሁኔታ የፓርቲያችንን አመራር እውን የማድ
ረጊያው ዓይነተኛ መድረክ መሠረታዊ ድር
ጅቶች እንደመሆናቸው ፥ በዚህ በኩል የተ
ለየ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ።

Digitized by Google

ለሕዝባዊ ድርጅቶች መሪነት የሚመረጡ ግለሰቦች ለማኅበራቸው በቂ ግልጋሎት እን ዲሰጡ ኢሠፓ በፖለቲካ ሥርዓት መሪነቱና አስተባባሪ ማዕከልነቱ ተመራጮች የሚሰ ጡት ሕዝባዊ አገልግሎት ተገቢው ግምት ተሰጥቶት አስፈላጊው መደረጉን ማረጋገጥ አለበት ። ከዚህም ሌላ በዝቅተኛ ደረጃ ዎችና(በተለይም በገጠር) የተወሰኑ ግለ ሰቦች በተለያዩ ማኅበራት አመራር አካላት ውስጥ ቦታ መያዛቸው የሚያስከትለውን የሥራ መደራረብ ችግርና የሥራ ቅልጥ ፍና ማጣት የሚወገድበትን ሁኔታ መሻት ይገባል ።

በሕዝባዊ ድርጅቶች አባላት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው ለሕዝባዊ ድርጅቶች ዓላማ ተግባራዊነት በየደረጃው ያሉት የአመራር አካላት ድርሻ አቅጣጫ ማሳየትና ሥራን ማስተባበር ነው ። ለሕዝ ባዊ ድርጅቶች ጥንካሬ መሠረት የአባሎቹ ተሳትፎ ነው ። ስለዚህ በየሕዝባዊ ድርጅ ቶቹ ውስጥ ያሉት አባላት ከየማኅበራቸው የሚጠብቁትን ሁሉ ለማግኘት የተሟላ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል ።

የተለያዩ ምክንያቶች መስጠት ቢቻ ልም በሁሉም ሕዝባዊ ድርጅቶች ዘንድ የሚታየው የአባላት ተሳትፎ የሚፈ ለገውን ያህል የተሟላ እንዳልሆነ መገ ንዘብ አያስቸግርም። በሌላ በኩል ደግሞ በሕዝባዊ ድርጅቶች መሠራት ስለሚገባ ቸው ጉዳዮች ከአባላት በርካታ አስተያየቶ ችና በአመራር አካላቱም ላይ ኂሶች ሲሰነ ዘሩ ይሰማል ። በተለያዩ መልኮች የሚቀርቡ ገንቢ አስተያየቶች በመሠረቱ ሊደገፉና ሊበ ረታቱ የሚገባቸው ናቸው ። ይሁንና ከአባ ላቱ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች ለተፈጻሚነታ ቸው ምንም ድርሻ ከሌለው ተመልካች ሊቀ ርቡ በሚችሉበት መልክ መሆን የለባቸው ም ። ማንኛውም አባል ለተዛቡ አሠራሮች መስተካከል አስተዋጽኦ ሊኖረው ይገባል። በመሆኑም ዛሬ በሁሉም ሕዝባዊ ድርጅቶች አባላት ዘንድ በሰፋት የሚታየው ፣ ለማኅበሩ ሥራ ደንታ ማጣትና ተሳትፎም ቢኖር እን ኳን የቀዘቀዘ መሆኑ ሊቀጥል አይገባውም።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የሕዝባዊ ድርጅቶች ግለሰብ መሪዎችና የአመራር አካ ላት ኃላፊነት ለተወሰኑ ክንዋኔዎች ተሰ ማሚ ስልት መቀየስና የአባላቱን ተግባራዊ ተሳትፎ በማስተባበር ለፍሬያማነት እንዲበ ቃ ከማድረግ ብዙ የሚያልፍ ሊሆን አይች ልም ። ከፍ ብሎ የተጠቀሱት አይነት ድክ መቶች ከአመራር አካላቱ አካባቢ የሚኖሩ ከሆነ ለአባላት ንቁና የተሟላ ተሳትፎ መቀ ነስ በአንዳንድ ሁኔታም ጨርሶ አለመኖር ምክንያት ሊሆን ይችላል። ለችግሩ መፍትሔ ማግኘት ፣ የአመራር አባላትን ጉድለት ለማ ረምና ለማስተካከል ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በየ ተሰባሰበባቸው ድርጅቶቹ አማካይነት በፖለ ቲካው ፣ በኢኮኖሚውና በማናቸውም አቅ ጣጫ አብዮቱ ባቀዳጀው መብት ተጠ ቃሚ ለመሆን ንቁ ተሳትፎ ማድረጉ ወሳኝነት አለው ። በአንዳንድ አካባቢ እንደሚታየው ሕዝቡ ሀብቱና መብቱ የግ ለኞች መጠቀሚያ ሲሆን እያየ ቸል ማለ ቱና ብሶት በማሰማት ብቻ መወሰኑ ፣ ሌላው ቀርቶ እራሱ የመረጣቸውን መሪዎች እንኳ አለመቆጣጠሩና የመሳሰሉት ድክመቶች በአፋጣኝ መወገድ ያለባቸው ጉዳይ አዝማሚ ያዎች ናቸው ።[26] በዚህም መሠረት በሕ ዝባዊ ድርጅቶች አመራር አካላት አካባቢ ለሚኖሩ ድክመቶች የአባላቱ ቸልተኝነትም ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ታውቆ ለድክ መቶቹ መወገድ መላ አባላት በጋራ መነ ሳት ይኖርባቸዋል ።

ስለሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎችና ስለአባ ላቱ ሲወሳ ሊታለፍ የማይገባው አንድ መሠ ረታዊ ነጥብ አለ።ይኸውም ባላቸው ዓቅምና ችሎታ ብዙኃኑን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆ ን የተሰማሩ ግለሰቦች በኅብረተሰቡ ዘንድ ሊኖራቸው ስለሚገባው ክበሬታ ነው።በየደረ ጃው የሚገኙ የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት በመዘ

Digitized by Google

ጋጀታቸውና ለዚህም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ አነስም አደገ ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ (በተለይ ከተራ አባሎች ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር) የተወሰነ መሥዋዕትነት መክፈላቸው አይቀርም ። ይህ ሕዝባዊ አደራን ከመቀበል ጋር የተያያዘ ግዴታ መሆኑ ባይካድም ለዚህ በመዘጋጀታቸው ብቻ እንኳን የተወሰነ ክብርና ምስጋና ሊሰጣቸው ይገባል። የሕዝብ አደራ እንዳልተቀበሉ ግለሰቦች በትርፍ ጊዜያቸው የግል ጉዳያቸውን ማከናወን ወይም መዝናናት ሲችሉ እራሳቸውን ይህን የመሰለ ነፃነት በመንፈጋቸው ከአባላት በሚሰጥ ከበሬታ አማካይነት መንፈሳዊ እርካታ እንዲያገኙ ማድረግ የሚበዛባቸው አይሆንም ።

ሕዝባዊ ድርጅቶችን ይልበጥ በማጠናከር፣ በተሻለ ጥራት ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ለማድረግ በተለያዩ አቅጣጫዎች መሟላት ያለባቸውን መሠረታዊ ሁኔታዎች ለመጠቆም ተሞክሯል። ለየጉዳዮቹ ተቀዳሚ ተጠሪ የሆኑ ባለቤቶችን በማመልከት መወገድ ያለባቸው ድክመቶች ደተዘረዘሩ ቢሆንም መፍትሔአቸውን ግን በዚሁ መልክ በተናጠል ብቻ መሻት አጥጋቢ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። ምክንያቱም ችግሮቹ እርስ በርስ የተሳሰሩና አንዱ ለሌላው መንሥኤ ሊሆን ስለሚችል ነው ። ስለዚህ የተጠቀሱትን ችግሮች ለማቃለልና ለማስወገድ የሁሉንም የጋራና የተቀናጀ ጥረት ማሳደግ ያስፈልጋል

ማጠቃለያ

ለሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከር ከዚህ በላይ ለተጠቆሙትና ለሌሎችም ተመሳሳይ ድክመቶች መወገድ የፖለቲካ ሥርዓቱን አካላት የተቀናጀ ጥረትና በዚህም አማካይነት የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም ። ይሁንና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ለማጠናከር ድክመቶችን በማስወገድ ላይ ብቻ የሚወሰን ጥረት በቂ አይደለም ። ስለዚህ ለአደረጃጀታቸውም ሆነ ለአሠራራቸው ቅልጥፍናና ለእንቅስቃሴአቸው ውጤታማነት አዳዲስ ስልቶችን በመቀየስ ሥራ ላይ ማዋል በተከታታይ መከናወን የሚኖርበት ጉዳይ ነው ።

በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ለሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከር ተገቢውን ትኩረት የመስጠቱ አስፈላጊነት ይበልጥ ጉልቶ የሚታየው ወደፊት ከሚጠብቃቸው ኃላፊነት ስፋትና ክብደት አኳያ ነው። ስለሆነም ለአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ጥንካሬና ዕድገት በዚህም አማካይነት በኅብረተሰቡ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ መፋጠን ከራሳችንና ከሌሎችም ልምድ በተጨባጭ ሁኔታዎች ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ የተመሠረቱ አዳዲስ አሠራሮችን በመፍጠርና በማዳበር የሕዝባዊ ድርጅቶችን ብቃት ማሳደግ ግዴታ ነው ።

አብዮታችን ዛሬ ከደረሰበት ደረጃና በተለይም ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምሥረታ ዋዜማ ላይ በምንገኝበት በአሁኑ ወቅት ለሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከር የሚሰጠው ግምት ከፍተኛ መሆን ይኖርበታል ። « በሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት ሕዝቡ በአገሪቱ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ውስጥ የሚያደርገውን ተሳትፎ ይበልጥ ማስፋትና ማጠናከሩ በሪፐብሊኩ ውስጥ የሚጠበቅበትን ድርሻ በተሻለ ብቃት ለመወጣት እንደሚያዘጋጀው መገንዘብ ያሻል ። ስለዚህም በአሁኑ ጊዜ ሕዝባዊ ድርጅቶችን የማጠናከሩ ተግባር በቀላሉ የሚታይ መሆን የለበትም ። » [27]

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ለሶሻሊዝም እውን መሆን በየዘርፉ ለሚደረገው ትግል ሥምረትና የዚህም ዋንኛ መሠረት ለሆነው ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ ዕድገት ከሕዝባዊ ድርጅቶች የሚጠበቀው የአስተዋጽኦ ስፋት ያሉትን ሕዝባዊ ድርጅቶች ማጠናከር ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም መመሥረት መጠየቁ የማይቀር ነው ። በዚህ በኩል በተለያዩ መስኮች የተሰማሩ ሙያተኞችና የፈጠራ ሰዎች በየፈርጃቸው ሊደራጁ የሚችሉበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ። የሙያ ማኅበራት መመሥረት የተለያዩ ሙያተኞችን የተናጠል ጥረት ለማቀናበር የሚያስችል አመቺ መድረክ የሚያስገኝ ከመሆኑም ሌላ ሙያተኞቹ እርስ በርስ በመ

Digitized by Google

ግግር ብቃታቸውን ለማሳደግ የሚያግዛቸው ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል ። በዚህም አማካይነት በሳይንስና በቴክኖሎጂ እንዲሁም በርዕዮተዓለምና በባህል መስኮች ጥናትና ምርምር በማስፋፋት ለአዳዲስ መግሪያዎችና ዘዴዎች መፈጠር ተገቢውን ሥነኪነታዊ የጥራት ደረጃ የጠበቁ የፈጠራ ሥራዎች መመረት በአጠቃላይም ኢሠፓ ለሚነድፋቸው ትልሞች ተፈጻሚነት ከፍተኛ ድርሻ የሚኖረውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል ።

ስለዚህ ነባርና ድክመታቸውን አስወግደውና ጥንካሬያቸውን ይበልጥ አጐልብተው ለበለጠ ኃላፊነት እንዲዘጋጁ ፣ አዳዲሶቹም እንዲመሠረቱ በማድረግ ሕዝባዊ ድርጅቶች በምንገነባው ሕዝባዊ ፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ተገቢ ሥፍራቸውን መያዛቸውን ማረጋገጥ የኢሠፓን የቅርብ አመራር የሚጠይቅ የማያቋርጥ ሂደት ነው ።

የ ማ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

1. F. Burlatsky, *The Modern State and Politics* (Moscow: Progress Publishers, 1978), p. 47.
2. F. Burlatsky, *loc. cit.*, p. 22.
3. F. Burlatsky, *Ibid.* p. 122.
4. F. Burlatsky, *Ibid.*
5. F. Burlatsky, *Ibid.*, p. 48.
6. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 31, p. 498, Quoted in Social Science, Vol. XII, No. 1 ,1981, p. 55.
7. B. Topornin E. Machulsky, *Socialism and Democracy*, (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 146.
8. D.A. Kermov, (Ed.) *Soviet Democracy In The Period of Developed Socialism*, (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 66.
9. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 42, p. 171 (Russ. Ed.) Quoted in *Socialism, Principles, Practice, Prospects*, No. 6, June 1985, p. 14.
10. D.A. Kerimov, (Ed.) *Ibid.*, p. 85.
11. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 32, p. 21, quoted in A. Kh. Makhnenko, *The State Law of Socialist Countries*, Moscow: Progress Publishers, 1976), p. 144.
12. A. Kh. Makhnenko, *The State Law of Socialist Countries*, (Moscow: Progress Publishers, 1976), p. 144.
13. B. Topornin, E. Machulsky, *loc. cit.*, p. 143.
14. A. Kh. Makhnenko, *loc. cit.*, p. 166.
15. A.Kh. Makhnenko, *loc. cit.*, p. 147.
16. የሕዝብና የቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ፣ የሕዝብና የቤት ቆጠራ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ፣ ቅጽ 1 ፣ ቁ- 1 አዲስ አበባ ፣ መስከረም 1977 ፣ ገጽ 15 ።
17. ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበው የድርጅት ዘርፍ ሪፖርት ፣ ገጽ 55 ።
18. የኢሠፓ ፕሮግራም ፣ ገጽ 44. ።
19. የኢሠፓ ፕሮግራም ፣ ገጽ 44 ።
20. የኢሠፓ ፕሮግራም ፣ ገጽ 43 ።
21. A.Kh. Makhnenko, *loc. cit.*, p. 159.
22. *Ibid.*, pp. 154-155.
23. ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት፣ ገጽ 65 ።
24. የድርጅት ዘርፍ ሪፖርት ገጽ 52 ፣
25. የድርጅት ዘርፍ ሪፖርት ፣ ገጽ 58
26. ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ፣ ገጽ 70 ።
27. የተጠቀሰው ሰነድ ፣ ገጽ 25 ።

Digitized by Google

ስለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት

—አንዳንድ ነጥቦች *

ጌታቸው ሀደታ

ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግን የመረጡ አገሮች የሚመሠርቱትን የመንግሥት ዓይነት በተለይ ከሚገኙበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በውል መገንዘባቸው ለሶሻሊዝም ግንባታ ዓላማቸው ምሥረት ወሳኝ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የሚፈለገውን የመንግሥት ዓይነት ለመመሥረት ፍላጐት ብቻ አይበቃም። የኅብረተሰብን የዕድገት ደረጃና የወቅቱን ሁኔታ በትክክል ማጤን ያሻል። ሌሎች የተጓዙበትን ጉዳና መመርመር ተገቢ ሲሆን በተለይ የራስን ተጨባጭ ሁኔታ በጥሞና ማገናዘብ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በታዳጊ አገሮች በሚካሄደው ትግል በአንድ በኩል ኢምፔሪያሊስቶች፣ ፊውዳሎችና ለኢምፔሪያሊዝም ያጐበደዱ የቡርዧው መደብ ክፍሎች፣ በሌላ በኩል ሠራተኛው፣ አርሶአደሩ፣ አብዮታዊ ምሁራንና አብዮታዊ ሠራዊት እንዲሁም ሌሎች የትግሉ ደጋፊ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደየአገሩ ሁኔታ መለስተኛ ብሔራዊ ቡርዧዎች ጭምር (በአጭሩ ዲሞክራሲያዊ ኃይላት) ሆነው የሚፋለሙበት ነው። በትግሉ አሸናፊ ለመሆን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችን ሁሉ በማስተባበርና ኃይልን አጠናክር፣ ለኢምፔሪያሊስቶችና ለሌሎች አድኃሪ ኃይላት ደባ በር ሳይከፍቱ መታገል ያስፈልጋል። በዚህም የአብዮታዊ ፓርቲ ግንባር ቀደም አመራር የማይታለፍ መሠረታዊ ጉዳይ ሲሆን የአብዮቱን ደጋፊዎች ሁሉ የሚያስተባብር ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት መመሥረትም አማራጭ የሌለው የትግል መሣሪያ ነው። ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ስለሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ምሥረታ የቀረበው ማዕከላዊ ሪፖርት የዚህን መንግሥት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ሲገልጽ እንደሚከተለው ዘግቧል።

* ይህ ጽሑፍ በሸዋ ክፍለ ሀገር ኢሠፓ ኮሚቴ አማካይነት ለመስከረም ዝግጅት የቀረበ ነው።

Digitized by Google

ኋላቀር አገሮች በካፒታሊስት ዕድገት ሰልፈው ለሕዝቦቻቸው ዕድገትና ብልፅግና ሊያስገኙ ስለማይችሉ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በማካሄድ ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችን ያስተባበረ ሰፊ ማኅበራዊ መሠረት ያለው መንግሥት መመሥረት የማይታለፍ ተግባር ሆኗል።[1]

እንደሌሎች ታዳጊ አገሮች ሁሉ የኢትዮጵያም ተጨባጭ ሁኔታ ለመላው ሠርቶ አደር ሕዝብ የቆመና ዲሞክራሲያዊ የሆነ መንግሥት መመሥረትን የግዴታ አስፈላጊ አድርጎታል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ለማጠናቀቅና ለሶሻሊዝም መሠረት ለመጣል በሚካሄደው የትግል ሂደት ውስጥ በኢሠፓ መሪነት የሚመሠረተው መንግሥት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ይሆናል። ይህ መንግሥት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በመባል የሚሰየም ሲሆን በመደባዊ ይዘቱ የሠራተኛውና የገበሬው ባጠቃላይም የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ የበላይነት የሚረጋገጥበት ይሆናል። ማለትም ይህ መንግሥት የወዝአደሩን መደብ የበላይነት የሚያሰፍን ሳይሆን ወደዚሁ የሚያደርስ ይሆናል። የኢሠፓ ፕሮግራም የዚህን መንግሥት ምንነትና ተግባር እንደሚከተለው ገልጾታል።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማኅበራዊ መሠረት በሠራተኛውና በገበሬው ኅብረት፣ በአብዮታዊ ምሁር፣ በአብዮታዊ ሠራዊት፣ ለአብዮቱ ዓላማ በቆሙ የእጅ ጥበብ ሙያተኞችና በቢሮ ሠራተኞች ተባባሪነት የሚገለጽ ይሆናል። ይህም ሁኔታ ወደ ወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መሸጋገሪያ ድልድይ ነው። በአገራችን በመካሄድ ላይ ያለውን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ለማጠናቀቅ የሶሻሊዝምን ግንባታ ማካሄድ ይሆናል። ይህም የሚገለጸው በሠራተኛውና በገበሬው ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት በተጓላ ሁኔታ መመሥረትና ከዚያም ደረጃ በደረጃ በሠራተኛው መደብ ልዕልና በማሻያማ ሁኔታ መረጋገጥ ነው።[2]

የአርጌውን ሥርዓት መዋቅር አፍርሶ በአዲስና ተራማጅ መዋቅር ለመተካት የተለያዩ ነገር ግን ወደ አንድ ግብ የሚያደርሱ ስልቶችን መከተል ይቻላል። በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አወቃቀርና አሠራር ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ አገናዝቦ ካለምነው ግብ ሊያደርሰን የሚችል ስልት የሚከተል፣ የራሱ የሆነ የአሠራር ባሕርይ ይኑረው እንጂ «--- ሁለንተናዊ በሆኑ ማርክሲስት ሌኒኒስት የመንግሥት አወቃቀርና አሠራር መርሆዎች የሚገዛ ነው። በዚሁ መሠረት ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት፣ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት፣ ሶሻሊስት ሕጋዊነትና ንቁ የሕዝብ ተሳትፎ ያለበት አሠራርና አወቃቀር»[3] ሪፐብሊኩ የሚመራባቸው መርሆዎች ይሆናሉ።

ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት

ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት የሁሉም አገር ወዝአደሮችና ሠርቶአደር ሕዝቦች ከብዝበዛና ከጭቆና ለመላቀቅ በሚያካሂዱት ትግል በአንድነት የሚያስልፋቸው መርህ ነው። ይህ መርህ ነባራዊ መሠረት አለው። የሁሉም አገር ምዝብር ሕዝቦች ድል ለመጐናጸፍና እውነተኛ ነፃነት የሰፈነበት ኅብረተሰብ ለመገንባት የሚችሉት ኃይላቸውን በማስተባበርና የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር ኢምፔሪያሊዝምንና ካፒታሊዝምን ድል ሲያደርጉ ብቻ ነው። ወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት የተለያዩ ብሔረሰቦችና ብሔሮች አባል የሆኑ ሠርቶአደሮች በሚያደርጉት ትብብር ይገለጻል። ለምሳሌ በዓለምአቀፍ ደረጃ የተለያዩ አገሮች ሠርቶአደሮች ለእኩልነትና ለሰላም መከበር በሚያደርጉት የትግል እንቅስቃሴ፣ በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ብሔሮች ወይም ብሔረሰቦች ሠርቶአደሮች ለመንግሥት ሥልጣን ተግባራዊነት በሚያደርጉት ተሳትፎና በብሔረሰቦች እኩልነት መከበርና ዋስትና ማግኘት ይገለጻል።

በኢትዮጵያም በሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የብሔረሰቦች ሠርቶ አደሮች

Digitized by Google

ሁሉ እኩልነት በይበልጥ በተግባር የሚገ
ለጽ ይሆናል ። የሁሉም ብሔረሰቦች ህል
ውና ተረጋግጦ በሪፐብሊኩ ውስጥ ተገቢ
ቦታቸውን ይዘው ለአንዲት የጋራ አገር
ማለትም ለኢትዮጵያ ዕድገትና ብልጽግና
የየበኩላቸውን ድርሻ ያበረክታሉ ።

በየደረጃው በተግባር በሚገለጸው የአካ
ባቢ የራስ በራስ አስተዳደር መብት በመ
ጠቀም ብሔረሰቦች በክልልም ሆነ በአጠ
ቃላይ የመንግሥት አመራር ውስጥ ቀጥታ
ተሳትፎ ስለሚኖራቸው [4] በዚህ መድረክ
ነት ሁሉም ብሔረሰቦች በይበልጥ እየተ
ቀራረቡ ፣ እየተዋወቁና እየተዋሐዱ ይሄ
ዳሉ ። በቁጥር አነስተኛ የሆኑትና በዕድ
ገታቸው ኋላቀር የሆኑት ዕድገታቸው ከሌ
ሎች ጋር እየተቀራረበ እንዲሄድና እንዲፋ
ጠን ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል ። ስለዚህ በኢ
ትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
አንዱ የጥንካሬያችን ምንጭ የሆነው የብ
ሔረሰቦች አንድነት ይበልጥ ይጐለብ
ታል ።

እንደውስጥ ፖሊሲ ሁሉ የውጭውም
ፖሊሲ በወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት
መርህ ላይ ተመሥርቶ እንዲራመድ ለሶሻ
ሊዝም የቆሙ ሁሉ አጥብቀው ይታገላሉ ።
ሶሻሊስት አገሮች በሕገ መንግሥት ውስ
ጥም ይገልጹታል ። እርስ በርሳቸውና
ከሌሎች ተራማጅ አገሮች ጋር በወዝአ
ደራዊ ዓለምአቀፋዊነት መርህ ላይ የተመ
ሠረቱና የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓትን
የወሳኝነት ሚና የሚያጐለብቱ ወንድማ
ዊና ጓዳዊ ግንኙነቶች ያደርጋሉ ። በዚህ
ግንኙነት አንዱ በሌላ ኪሣራ ሊበለጽግ
አይፈልግም ። «የሁሉም አገር ሠራተኞች
ተባበሩ» በሚለው ማርክሳዊ ጥሪ ላይ በመ
መሥረት የሶሻሊስት አገሮች ሠራተኞች
ለጋራ ችግሮች የጋራ መፍትሔ እንዲሹ
የሶሻሊስት አገሮች መንግሥታት አመቺ
ሁኔታዎችን ይፈጥሩላቸዋል ። ለምሳሌ የሶ
ቭዬት ኅብረት ሕገ መንግሥት ስለ ሶሻሊ
ስት ዓለምአቀፋዊነት የተሰጠውን ትኩረት
ሲገልጽ ፦

ሶቭዬት ኅብረት የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓ
ትና የዓለም ሶሻሊስት ኅብረተሰብ አካል እን
ደመሆኗ መጠን ከሌሎች ሶሻሊስት አገሮች
ጋር በሶሻሊስት ዓለምአቀፋዊነት መርህ
ላይ የተመሠረተ ወዳጅነት፣ ትብብርና ጓዳዊ
መረዳዳትን ታራምዳለች ፤ ሶሻሊስት ኢኮኖ
ሚያዊ ውህደትና በዓለምአቀፍ ሶሻሊ
ስት የሥራ ክፍፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ታደ
ርጋለች [5]

ይላል ። የሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ሕገ
መንግሥታትም በተመሳሳይ ሁኔታ የዚህን
መርህ አስፈላጊነት ሳይጠቅሱ አያልፉም ።
የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ሕገ መን
ግሥት «የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ
በሶሻሊስት ዓለምአቀፋዊነት መርህ መሠ
ረት ከሶቭዬት ኅብረትና ከሌሎች ሶሻሊ
ስት መንግሥታት ሁለንተናዊ ትብብርና
ወዳጅነት ታደርጋለች ፤ ታዳብራለች» [6]
ይላል ።

ያለዚህ መርህ ተግባራዊነት ሶሻሊዝ
ምን ማራመድ አይቻልም ። ሌላ ቀርቶ ሥር
ዓቱን እራሱን ባለበት ሁኔታ ማቆ
የትም አዳጋች ይሆናል ። በተለይም
በአሁኑ ጊዜ ኢምፔሪያሊዝም የዓለምን
አድኅሮት አስተባብሮ «ኮሚኒዝምን ለመ
ገደብ» በሚል ሰላምን በማደፍረስ ላይ
በሚገኝበት ወቅት ዓለምን ከአጠቃላይ
ጥፋት ለማዳንና ኢምፔሪያሊዝም በተራ
ማጅና ሶሻሊስት አገሮች ውስጥ የሚያደ
ርገውን ጣልቃ ገብነት በጋራ ለመቋቋም
የወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት መርህ አስ
ፈላጊነት ከምንጊዜውም ጐልቶ ይታያል ።
ተራማጅ ታዳጊ አገሮችም ይህን መርህ
ተግባራዊ ካላደረጉ ሁለንተናዊ ነፃነታቸ
ውን ለማረጋገጥ የሚያደርጉት ትግል አስ
ፈላጊ ያልሆነ መሥዋዕትነት ማስከፈሉ
የማይቀር ነው ።

የአገራችንን አንድነት ለመጠበቅ ፣ ኢኮ
ኖሚያዊ ግንባታችንን ለማፋጠንና በየጊ
ዜው የተነሡትን ሰው ሠራሽና ተፈጥሮ
አዊ ችግሮች ለመፍታት ባደረግነው ትግል

Digitized by Google

ሁሉ የብሔረሰቦቻችን መረዳዳት ጉልቶ
የታየ ሲሆን በዚሁ መንፈስ የትግላ
ቸው አንድነት የበለጠ መጠናከር ያለ
በት መሆኑና ጠቃሚነቱ የሚያጠያይቅ
አይደለም ። በዓለም አቀፍ ደረጃም የሶሻሊ
ስትና የተራማጅ አገር ሕዝቦች ፣ በካፒታሊ
ስት አገሮች ያሉ ሠርቶአደሮች ድጋፍ በተግ
ባር እየታየ በመምጣቱ የወዝአደራዊ ዓለም
አቀፋዊነት መርህ አስፈላጊነት ከኢትዮጵያ
ሰፊ ሕዝብ የተሰወረ አይደለም ። የሚቋቋ
መው መንግሥት የሕዝቡ ስለሆነና ይህም
የራሱ የሆነ መንግሥት የሚከተለውን መርህ
ከሚያውቀው ተጨባጭ ነገር ተነሥቶ
ስለሚያስገነዝበው ለትግሉ በቆራጥነት
እንዲነሣሣና በአመራሩም እንዲተማመን
ያደርገዋል።የዓለም ተራማጅ ሕዝቦች አካል
የመሆን ስሜቱን ያጐለብተዋል ። እሱ ለሌ
ሎች፣ሌሎችም ለእሱ ዕድገትና ነፃነት እንደ
ሚቆሙና ምንጊዜም እንደሚደርሱለትና
እንደሚደርስላቸው የወዝአደራዊ ዓለምአ
ቀፋዊነት መርህ ስለሚያስገነዝበው ሕዝቡ
ለመርሁ ተግባራዊነት በግንባር ተሰላፊ
ይሆናል ። ስለዚህ የመርሁ ተግባራዊ
መሆን እጅግ አስፈላጊ ይሆናል ።

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት

እንደወዝአደራዊ ዓለምአቀፋዊነት ሁሉ
ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትም በሕዝባዊ
ዲሞክራሲያዊ መንግሥት አወቃቀርና አመ
ራር ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው ። ዲሞክ
ራሲና ማዕከላዊነት በመንግሥት አካላት
አወቃቀርና አሠራር ውስጥ እንደየወቅቱ
ተጨባጭ ሁኔታ እየታዩ ተግባራዊ ይሆ
ናሉ ። በዲሞክራሲያዊ መልኩ ሕዝቡ
በጾታ ፣ በጐሣ ፣ በሃይማኖት ፣ በሥራ መኳከ
ወዘተ . ልዩነት ሳይደረግበት ከዝቅተ ው
እስከ ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን
አካል እርከኖች የሚወክሉትን እንደራሴ
ዎች ይመርጣል ። የምርጫው ሥርዓት
አፈጻጸምና ሂደት በሕገ መንግሥት ይወሰ
ናል ። ለምሳሌ በሶቭዬት ኅብረት ሕገ
መንግሥት እንደተደነገገው «ወደ ሶቭዬ
ቶች (ሕዝባዊ ኮሚቴዎች) የሚመጡ ተወ
ካዮች ሁሉ የሚመረጡት በሁሉን አቀፍ ፣
በእኩልነትና ቀጥታ የምርጫ መብት ላይ
በተመሠረተ በምሥጢር የምርጫ
ካርድ »[7] ነው ።

ምርጫው ሁሉን አቀፍ በመሆኑ በተረ
ጋገጠ የአእምሮ መታወክና በሌሎችም ምክ
ንያቶች በሕግ ካልታገደ በስተቀር ዕድ
ሜው 18 ዓመት የሞላው ማንኛውም ዜጋ
የመምረጥና የመመረጥ (ለከፍተኛ የመንግ
ሥት አካል የሚመረጥ ፣ 21 ዓመት የሞላው)
መብት አለው ። በተጨማሪም ሁሉም
እኩል የምርጫ ድምፅ ሲኖራቸው ተወካዮ
ቻቸውን በቀጥታና በምሥጢር ይመር
ጣሉ ። በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚ
መረጡ ተወካዮች ለወከላቸው ሕዝብ ምን
ጊዜም ተጠሪነት አለባቸው ። ሕዝቡ በወከ
ለው ሰው ላይ ጥርጣሬ ሲያድርበትና እም
ነት ሲያጣ የሰጠውን ውክልና ሊያነሣ
ማለትም ከሥልጣን ሊያወርደው ይችላል።
በሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት አወ
ቃቀርና አሠራር ሂደት ውስጥ የዜጎች እው
ነተኛ የዲሞክራሲ መብት በዚህ ዓይነት
የሚገለጽ ሲሆን የመንግሥት አካላት እን
ደዚሁ ማዕከላዊነትን ጠብቀው ዲሞክራ
ሲያዊ በሆነ መንገድ ሥራቸውን ያከናው
ናሉ ።

የመንግሥት አካላት እንደየአካባቢያ
ቸው ተጨባጭ ሁኔታ የክልላቸውን ፖለ
ቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ርዕዮተ
ዓለማዊ ሥራዎችን የማቀድና የመምራት
ወይም እራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳ
ደር ፣ ለበላይ አካል ገንቢ ሐሳቦችን የማቅ
ረብ መብት ሲኖራቸው በሌላ በኩል በየደ
ረጃው ላሉ የበላይ አካላት ተጠሪነት አለ
ባቸው ። የከፍተኛ መንግሥት አካላት ውሳ
ኔዎች በበታች አካላት ተግባራዊ መሆን
ግዴታ ነው ። እዚህ ላይ በተጨማሪ መታ
ወቅ ያለበት በየደረጃው የአካባቢ የአስተ
ዳደር ክልሎች እንደየአካባቢያቸው ተጨ
ባጭ ሁኔታ ከፍተኛ የፓርቲና የመንግሥት
አካሎች በሚቀይሱት አጠቃላይ ዕቅድ
ላይ በመመሥረት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማ

Digitized by Google

ድረግ የራሳቸውን እርምጃ ይወስዳሉ እንጂ እንቅስቃሴያቸው ከአጠቃላዩ ዕቅድ ውጭ በዘፈቀደ የሚደረግ አይደለም። የሥራ ውጤታቸው አካባቢውን ብቻ ሳይሆን የመላ አገሪቱን ሥርተአደሮች ፍላጎት የሚያረካ መሆን ይኖርበታል። የሚወስዱት እርምጃ አንዱን አካባቢ አበልጽጎ ሌላውን የሚጎዳ እንዳይሆን አስፈላጊው ጥንቃቄ ሁሉ ይደረጋል። የማዕከላዊ አመራር አስፈላጊነትም ግብታዊ እንቅስቃሴዎችን አስወግዶ ዕቅዳዊ አመራር ለማስፈን ስለሆነ ያልተገናዘበና ያልተስተዋለ እንቅስቃሴ ሁሉ እንዲወገድ ጥረት ይደረጋል።

በዕቅዱም መሠረት የመንግሥት አካላት ተግባራቸውን በየደረጃው ጤናማ በሆነ መንገድ እንዲያከናውኑ በዲሞክራሲና በማዕከላዊነት መካከል ያለው ሚዛን መጠበቅና መጣጣም አለበት። ይሁን እንጂ በሁለቱ መካከል ያለው ሚዛን ሁልጊዜ እንዳይዛባ መጠበቅ አስቸጋሪ ነው።

የሶሻሊስት መንግሥት ማዕከላዊነትን የመጠበቅ ደረጃ በተለያዩ የአዝጋሚ ለውጥ ጊዜና በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ይለያያል። የእርስ በርስ ጦርነት፣ የከረረ የመደብ ትግል፣ የአካባቢ የሠለጠኑ ሠራተኞች እጥረት ወዘተ. ማዕከላዊነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጠበቅ ያደርጋሉ። የሶሻሊስት መንግሥት መጠናከር፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ዕድገትና ልምድ ያላቸው የአካባቢ ሠራተኞች መብዛት የአካባቢ የሥልጣን አካላትና ሰፊው ሕዝብ የተጠናከረ ነፃ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ሰፊ ዕድል ሲከፍቱላቸው አስፈላጊ ማዕከላዊነትም ተጠብቆ እንዲቀይ ያደርጋሉ።[8]

ስለዚህ እንደተደረሰበት የዕድገት ደረጃና እንደወቅቱ ሁኔታ ማዕከላዊነት ሊጠብቅ ወይም ሊላላ ይችላል። ሆኖም ከመጠን በላይ የላላ ማዕከላዊነት የሶሻሊዝምን ግንባታ ሊጎዳ ስለሚችል ጥንቃቄ ይደረግበታል።

ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮችም ውስጥ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን መርህ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። በእርግጥ መርሁን በተቻለ መጠን በተግባር ለመተርጐም እውነተኛ አብዮታውያን ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ነገር ግን የአገሩ ኢኮኖሚያዊ አቋም ደካማነት፣ የሕዝቡ ጠቅላላ ዕውቀት ዝቅተኛነትና የፖለቲካዊ ባህል በአብዛኛው ኋላቀር መሆን፣ አድኃሪ መደቦች በዓለምአቀፍ አድኅሮት አመራርና ድጋፍ ወደ ሥልጣን ለመመለስ የሚያደርጉት ጥረት ብቻውን በዲሞክራሲያዊ መድረኮች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕና ቀላል አይደለም። ምክንያቱም እነሱን ለመከላከል ሲባል ዲሞክራሲን ሰብሰብ ማዕከላዊነትን ጠበቅ ማድረግ የግድ ይሆናል። በተጨማሪም ቢሮክራሲያዊ ዝንባሌ ያላቸውና በተለያዩ ምክንያቶች ከዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ሥልጣን የተጋሩ ግለሰቦች አመቺ የመሰላቸውን ሁኔታ ሁሉ በመጠቀም ቢሮክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ለማስፈንና እያደርም የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብት ለማፈን ስለሚጥሩ ችግሩ የተባባሰ ሊሆን ይችላል።

እውነተኛ የሕዝብ ወገኖችና ወኪሎች የሚያራምዱትን ሥርዓት በይበልጥ ሕዝባዊ ወይም ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ ካላቸው ፍላጎት በሚመነጭ ምክንያት በአጠቃላይ «የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሆች ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች በተለያዩ ሰነዶች ውስጥ በተደጋጋሚ ቢጠቀሱም እስካሁን የተሟላ መልካቸውን ሊይዙ አልቻሉም። በአንዳንድ አገሮች በሁኔታዎች አስገዳጅነት ብዙ የፓርቲና የማኅበራዊ ተቋሞች አካላት በምርጫ ሳይሆን በሹመት መመደባቸው»[9] በመርህ ደረጃ ለማድረግ በሚፈለገውና በሁኔታው አስገዳጅነት በተግባር መካከል አለመጣጣምን ያመለክታል። ለአብዮታውያን ይህን በፍላጎትና በተጨባጭ ሁኔታ መካከል የሚፈጠረውን ቅራኔ ለመፍታት ጠንክር

Digitized by Google

መታገል አግራቂ የሌለው ጉዳይ ነው ።

በመሠረቱ የሕዝቡ ዲሞክራሲያዊ መብት የመደብ ጠላቶች መጠቀሚያ መሆን ከቻለ ለሕዝቡ አንዳችም ፋይዳ አይኖረውም ። ይህንን ለመከላከል መቻል የአንድን አብዮታዊ ኃይል ወይም ፓርቲ የአመራር ብቃት ያረጋግጣል ። በተለይም እንደ አገራችን ባሉ የሕዝቡ ፖለቲካዊ ባህል በማቆጥቆጥ ላይ ባለባቸው አገሮች ሕዝቡ ባገኘው መብት የመደብ ጠላቶቹን ጥልቃ ሳያስገባ በብቸኝነት ለመጠቀም እንዲችል ከቁጥጥር ባሻገር ሕዝቡን ማስተማርና መርዳት ፣ የሰፊውን ሕ ዝ ብ ዲሞክራሲያዊ መብት ከለላ በማድረግ የሚስነዘረውን የአድኃሪዎች ሤራ ለማክሸፍ መቻል ያስፈልጋል ።

ዛሬ አብዮቱ በአሸናፊነት ወጥቶ በሁለት እግሩ ቆሟል ማለት አብዮቱ ጠላቶች የሉትም ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው ። የአድኃሪው መደብ ርዝራዦችና በተለያዩ መልኮች የኢምፔሪያሊዝም ወኪሎች ሆነው በፀረ ሕዝብ ተግባር ላይ የተሰማሩ ቡድኖች በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምሥረታ ውስጥ ሰርገው በመግባት አብዮቱን ለመቦርቦር ስለሚፍጨረጨሩ አብዮታውያን ነቅተው መጠበቅ ይኖርባቸዋል ።

የመንግሥቱ ዲሞክራሲያዊነት የሚለካው ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለሰፊው ሕዝብ ብቻ ለማስጨበጥ በሚኖረው የችሎታ መጠን ነው ። አድኃርያን የመንግሥቱን ዲሞክራሲያዊነት የሚለኩት ከራሳቸው ፍላጎት አንፃር በመሆኑ እንደተለመደው ተቃውሞና ፀረ ሕ ዝ ብ ፕሮፓጋንዳ ማሠራጨታቸው የማይቀር ነው ። የፊውዳሉ መንግሥት እንኳን በሕዝባዊ ዓመፅ ተወግዶ በተግባሩ የሕዝቡን ፍላጎት የሚያራምድ አብዮታዊ መንግሥት ሲተካ «ሰብአዊ መብት ተደፈረ» በማለት ያላዝኑ እንደነበር የሚታወስ ነው ። ወደፊትም ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምሥረታ መሠረታዊ ሰነድ በሚሆነው ሕገ መንግሥት ላይ ሕዝቡ በተደራጀባቸው ሕዝባዊና የሙያ ማኅበራት ፣ በውይይት ክበቦች ፣ በገጠር፣ በከተማና በአብዮታዊ ሠራዊት ውስጥ በሚፈጠሩ አመቺ መድረኮች በመጠቀም ውይይት እንዲያደርግና አስተያየት እንዲያቀርብ በሚደረግበት ጊዜ ተመሳሳይ ፀረ ሕዝብ ፕሮፓጋንዳ እንደሚያካሂዱ ይገመታል። ይህንኑ የሐሰት ፕሮፓጋንዳቸውን ለማክሸፍ የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ ባህልና ንቃት ማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ከፊታችን የተደቀነ ርዕዮተዓለማዊ ሥራ ነው ።

ለዚህ ተግባር መከናወን የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች በፖለቲካ ትምህርት (በፖለቲካ ሥልጠና ጭምር) ማሳተፍና የተለያዩ የመወያያ መድረኮችም መክፈት ያስፈልጋል ። ሕዝቡ ፖለቲካዊ ትምህርትና ሥልጠና ማግኘቱ ለሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊኩ መንግሥት ጥንካሬ ዋስትና ነው ። ለዚህም ነበር ሌኒን የሶቭዬት መንግሥት «የጥንካሬ ምንጩ የሕዝቡ ፖሊቲካዊ ንቃት» 10 መሆኑን አበክሮ ያስገነዘበው ።

ሕዝባዊ ተሳትፎ

በማንኛውም የሶሻሊዝም ግንባታ ክንውን ውስጥ የሕዝቡ የነቃ ተሳትፎ መኖርና ለዚህም አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር እጅግ አስፈላጊ ነው ። የሕዝቡ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ የሶሻሊስት መንግሥት ከሚከተላቸው መርሆዎች አንዱ ነው። ሕዝቡ የማይሳተፍበት የአስተዳደር ጉዳይ አይኖርም ። ለምሳሌ የሶቭዬት ሕገ መንግሥት «የሶቭዬት ዜጎች የመንግሥትንና የሕዝቡን ጉዳዮች አስተዳደርና ማኔጅመንት በሚመለከት የመካፈል ፣ በአካባቢ ሁኔታዎችና በሁሉም ኅብረቶች በሚወሰዱ እርምጃዎችና በሚወጡ ሕጎች ላይ የመወያየትና የመቀበል መብት አላቸው» 11 ይላል። መርህዎችን በሕገ መንግሥት መደንገግ ብቻ በቂ ባለመሆኑ የሶሻሊስት አገር ሕዝቦች በመንግሥት ጉዳዮች ውስጥሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተለያዩ ስልቶች ይቀየሳሉ ።

Digitized by Google

በመንግሥት አካላት ውስጥ የሚመረጡትን ዕጩዎች በማቅረብ ፣ መንግሥት በሚያወጣው የሕገ ረቂቅ ላይ አገር አቀፍ ውይይት በማድረግ በቀጥታ በመሳተፍ፣ በተወካዮቻቸው አማካይነት በመንግሥት ሥራ ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ፣ ኢኮኖሚንና ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት በመንግሥት በሚዘጋጁ ስብሰባዎች ፣ በሚቋቋሙ ኮሚቴዎችና በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ መሳተፍ፣ የአገሪቱን ብሔራዊ ሀብትና የኅብረተሰቡን ንብረት በመጠበቅና በመንከባከብ በራስ አነሣሽነት ተሳታፊ በመሆን ፣ በመንግሥት ተቋሞች ወይም ድርጅቶች ውስጥ በሚመሠረቱ ቦርዶች ተወካዮችን በመምረጥ የድርጅቱን አስተዳደር በጋራ በመምራትና በመሳሰሉት ሕዝቡ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል ።[12]

እዚህ ላይ ንቁ የሕዝብ ተሳትፎ የሚለው መርህ ከዲሞክራሲያዊ መብቶች ጋር ፍጹም አንድ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ምክንያቱም ሕዝቡ ሰፊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ስለተሰጡት ብቻ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል ማለት አይደለም ። ለምሳሌ በሕገ መንግሥት ረቂቅ ላይ ሕዝቡ እንዲወያይና አስተያየት እንዲሠነዝር መድረክ ሲመቻችለት ይህንን በመጠቀም መተቸትና በተፈጠረለት ምቹ ሁኔታ ተጠቅሞ በሕገ መንግሥቱ ላይ የማሻሻያ ሐሳቦችን ለማቅረብ ካልቻለ ዲሞክራሲያዊ መብት እያለው ንቁ ተሳትፎ አለማድረጉን ያሳያል ። በተመሳሳይ ሁኔታ ሕዝቡ በትክክል ሊወክለው የሚችለውን ሰው ለመምረጥ ካልቻለ ፣ ከመረጠም በኋላ የተመረጠው ግለሰብ በተሰጠው ውክልና መሠረት ኃላፊነቱን መወጣቱን ካልተከታተለና ስሕተትም ሲፈጽም አስፈላጊውን እርምት ማድረግ ካልቻለ ዲሞክራሲያዊ መብት እያለው ንቁ ተሳትፎ አለማድረጉን ያመለክታል ። እንደዚሁም የሕዝቡን ንብረት ከማናቸውም ዓይነት ብኩንነትና ትክክል ካልሆነ አጠቃቀም መከላከል እንደመብት በሚቆጠርበት በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ የራስን ንብረት ለመጠበቅ አለመቻል በመብት አለመጠቀምንና በሥርዓቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አለማድረግን ያሳያል ። በአጠቃላይ ንቁ የሕዝብ ተሳትፎ በዲሞክራሲያዊ መድረኮች ሊገለጽ ቢችልም የእውነተኛ ዲሞክራሲ መኖር በራሱ የንቃ ሕዝባዊ ተሳትፎን ላይፈጥር ይችላል ። ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ሕዝቡ በራሱ አነሣሽነት ኑሮውንና እራሱን ለመለወጥ በሚያደርገው ሰፊ እንቅስቃሴ የሚገለጽ ነው።

ስለዚህ በሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ምሥረታ ወቅትና ከዚያም በኋላ ሕዝቡ በሚኖረው ዲሞክራሲያዊ መብት በትክክል መጠቀም መቻልና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የተጠናከረ መንግሥት ለመመሥረት ያስችላል ። በተለይም ለሪፐብሊኩ ምሥረታ ዋነኛ ሰነድ በሚሆነውና ወደፊትም ረዘም ላለ ጊዜ የሕዝቡን ጥቅም ማስጠበቂያና ግዴታውን ማሳወቂያ መሠረታዊ ሕጋዊ መግሪያ ሆኖ በሚቆየው በሕገ መንግሥቱ ረቂቅ ላይ ገንቢ አስተያየቶችንና ትችቶችን ለማቅረብ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ሕዝባዊ ተሳትፎን የሚያዳብር ነው ። ይህንን በሚመለከት ከሶሻሊስት አገሮች ልምድ ብዙ መማር ይቻላል ።

የሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥት ዲሞክራሲያዊነት የሚገለጸው የመጨረሻ መልኩን ይዞ ከወጣ በኋላ በሚኖረው ይዘት ብቻ ሳይሆን ሰፊው ሕዝብ በረቂቁ አነዳደፉ ፣ በሥራ አተረጓጎሙና በማሻሻያ ሐሳቦች አቀራረቡ ጭምር ሲሳተፍ ነው ። ረቂቁ ገና ከጅምሩ የሚዘጋጀው ለሕዝቡ ፍላጎት መሟላት የሚታገሉ ከፍተኛ የፓርቲ አመራር አባላት በሚገኙበት በሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ነው ። ሕዝቡም በረቂቁ ዝግጅት ላይ ይሳተፋል ። ሕገ መንግሥቱ ለከፍተኛ የመንግሥት አካል ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት አገር አቀፍ ውይይት ይደረግበታል ።[13]

የሶሻሊስት ሕገ መንግሥት ለሌሎች ሕጎች ሁሉ መሠረትና ምንጭ በመሆኑ በከፍተኛ ጥንቃቄና ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚዘጋጅ ሰነድ ነው ። በሕዝቡም ዘንድ ተቀባ

Digitized by Google

ይነት ሊኖረው የሚችለው ተግባራዊ በግድረጉ ላይ ብቻ ሳይሆን በማዘጋጀቱም ጭምር የሕዝቡን ትኩረት ሲያገኝ ነው ። ለምሳሌ በ1960* በቼኮዝሎቫኪያ በረቂት ሕገ መንግሥት ላይ ውይይት ለማካሄድ 47,000 ስብሰባዎች የተደረጉ ሲሆን ፤ በእነዚህም ስብሰባዎች 4,040,170 ሰዎች ተሳትፈዋል ። በውይይቱ ላይም 732,800 ተሳታፊዎች ሐሳብ አቅርበዋል [14] ። በዚያው ዓመት በሞንጎልያ 1,166 ስብሰባዎች ተደርገው በሕገ መንግሥት ረቂት ላይ 2,902 ዜጎች የማሻሻያ ሐሳብ ሰንዝረዋል ። [15]

ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮችም በሕገ መንግሥት ረቂት አነዳደፍና ረቂቁን ለአገር አቀፍ ውይይት ማቅረብን በተመለከተ የሶሻሊስት አገሮችን ልምድ ይጠቀማሉ ።

በ1976 የቤኒን ሕዝባዊ ሰብዮታዊ ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ የሕገ መንግሥት ሰርቃቂ ኮሚሽን ሰቋቋሞ ረቂቁ በ1977 በሕዝባዊ ሸንጎዎችና ስብሰባዎች ላይ ለውይይት ቀርቦ 115 የማሻሻያ ሐሳቦች ታክለዋል ፤ እንዲሁም ከሦስት ወር በላይ የውይይት ጊዜ በወሰደው የየመን ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ በ1970ው ረቂቀ ሕገ መንግሥት ላይ 40 ጠቃሚ የማሻሻያ ሐሳቦች ቀርበዋል ። [16]

ስለሆነም ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ መድረኮች በመታገዝ በሕገ መንግሥት ረቂት ላይ ሰፊ ውይይት አድርጎ የሚተዳደርበት ሕግ በሚፈለገው መልክ እንዲዘጋጅ የመጨረሻውን አስተያየት ሰጥቶ ከደመደመ በኋላ ብቻ ነው ለከፍተኛ የመንግሥት አካል ለውሳኔ የሚቀርበው ።

የሕገ መንግሥት ረቂት ማጽደቅን በሚመለከት በተለያዩ አገሮች የተለያዩ ልምዶች ታይተዋል ። ከከፍተኛ የመንግሥት አካል ሌላ በፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አካል ወይም በውሳኔ ሕዝብ (Referendum) ሕገ መንግሥት የሚጸድቅበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ። ለምሳሌ በቡልጋሪያ በ1971 99.7% ፤ በጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ በ1968 94.5% የድምፅ ሰጭዎችን ድጋፍ በማግኘት ሕገጋተ መንግሥታቱ በውሳኔ ሕዝብ ጸድቀዋል ። [17] ነፃነታቸውን ከተቀዳጁ በኋላ በ1975 የአንጎላና የሞዛምቢክ ሕገጋተ መንግሥታት ደግሞ የጸደቁት በአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎቻቸው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ነበር ። [18]

በአገራችን ሁኔታም ንቁ የሕዝብ ተሳትፎ በሚለው መርህ መሠረት ሰፊው ሕዝብ በሕገ መንግሥት ማጽደቅ ተግባር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ። ስለዚህ ረቂት ሕገ መንግሥቱ የሚጸድቅበት ሂደትና በዚህም ሂደት ውስጥ ሰፊው ሕዝብ የሚሳተፍበት ስልት እንደሚዘጋጅ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሰነድ ውስጥ ተመልክቷል ። [19] በመንግሥት ጉዳዮች ውስጥ የሕዝቡ ተሳትፎ ሲዳብር ዲሞክራሲ በይበልጥ እየተጠናከረና እያበበ ይሄዳል ። ኅብረተሰቡም የሚቋቋመው መንግሥት ለእርሱ የቆመ መሆኑን ከልምዱ ስለሚረዳ የአገር ፍቅር ስሜቱ፣ ሶሻሊስት አርበኝነቱና ለማንኛውም ዓይነት ውጭያዊም ሆነ ውስጣዊ ተጽዕኖ ወይም ለጥቃት አልበገር ባይነቱ በየጊዜው ይጨምራል ፤ ይጎለብታል ። የእውነተኛ መብትንና ነፃነትን ምንነት ስለሚያውቅ ምንም ዓይነት የአድኅርት ፕሮፓጋንዳ ሊፈታው አይችልም ።

ሶሻሊስት ሕጋዊነት

ሕዝቡ በሰፊ ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ሲጠቀም ከዚሁ ጋር በተጓዳኝነት ግዴታዎችም አሉ ። የሶሻሊስት መንግሥት ሕጎች በሁሉም ዜጎች መከበርና ተግባራዊ መሆን አለባቸው ። ሶሻሊስት ሕጋዊነት የሕግ መኖርንና ይህ የወጣው ሕግ በማናቸውም መንግሥታዊ አካሎች ፣ ባለሥልጣኖችና ግለሰቦች ያለማወላወል መከበርንና ተግባራዊ መሆንን

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የዓመታት አቆጣጠር እ. ኤ. አ ነው ።

Digitized by Google

የሚያስገነዝብ ነው። [20] የወጣው ሕግ መከበሩን የሚያረጋግጥና በአስፈጻሚነት የሚሰየመው አካል በሶሻሊስት አገሮች ፕሮክዩሬተር (ሕግ አስከባሪ) በመባል ይታወቃል። [21] «የአብዛኞቹ ሶሻሊስት አገሮች ሕገጋተ መንግሥታት እንደሚያመለክቱት የፕሮክዩሬተሩ ተቋም ዋንኛ ተግባር ሕጎችና ሌሎች ሕጋዊ እርምጃዎች ተጧልተው በመንግሥታዊ አካሎች፣ በባለሥልጣኖችና በዜጎች በትክክል በሥራ መተርጐማቸውን ማረጋገጥ ነው።» [22]

ሶሻሊስት ሕግ የሕዝቡን ጥቅምና ፍላጐት ማስጠበቂያ እንጂ የመጨቆኛ መሣሪያ ባለመሆኑ ሕዝቡ አጥብቆ ያከብረዋል፣ እንዲከበርም በጽኑ ይታገላል። ስለሆኑም ለሶሻሊዝም የቆሙ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ የሠርቶ አደሮች ቡድኖችና ግለሰቦች ሕግን፣ ደንብንና መመሪያን ማክበር ባህላቸው ይሆናል።

«ሶሻሊስት ሕጋዊነት የሶሻሊስት ዲሞክራሲ አንዱ ገጽታ በመሆኑ»[23] በመንግሥቱ የተደነገጉትን ሕጎች አለማክበር መብትን አካሉ ከሆነው ከግዴታ መነጠል ይሆናል። የሶሻሊዝምን ግንባታ ማደናቀፍ የሕዝብን ጥቅም መጻረር ነው። ከሕዝብ በላይ ደግሞ ምንም ስለሌለና ሥርዓቱም የቆመው ለብዙኃን ስለሆነ የብዙኃኑን ጥቅምና ፍላጐት የሚቃረን ማንኛውም የግለሰብ ወይም የቡድን ድርጊት በተመጣጣኝ የእርምት እርምጃ ይስተካከላል።

የሚወጡትን ሕጎች ኃያልነት የሚያስጠብቅ፣ ፍትሕ ሳይጓደል በደል ሳይፈጸም ሁሉም በሥርዓት እንዲተዳደር ለማድረግና ጥፋቶች ሲፈጸሙ ተመጣጣኝ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ተቋም በሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያም እንደሚመሠረት ይጠበቃል። ስያሜን በሚመለከት «በሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እነዚህን ተግባራት እንዲያከናውን የሚቋቋመው አካል ዓቃቤ ሕግ ተብሎ ሊጠራ ይችላል።» [24]

የመንግሥት አወቃቀርና ምርጫ

ከዚህ በላይ ልዩ ልዩ ልምዶችን በማገናዘብ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የሚመራባቸው መርሆች ምን እንደሆኑ ለመቃኘት ሞክረናል። ሌላው መነጋት ያለበት ነገር የመንግሥት አካላት አወቃቀር ጉዳይ ነው። የሪፐብሊኩ «የመንግሥት ሥልጣን ከዝቅተኛው የአስተዳደር ክልል አንሥቶ እስከ ከፍተኛው አገር አቀፍ ደረጃ በሕዝብ ምርጫ ላይ በመመሥረት በሚዋቀሩት አካላት የሚገለጽ ይሆናል።» [25] የሪፐብሊኩ መንግሥት አወቃቀር የራሱ በሆነ ልዩ ባሕርይ ላይ ተመሥርቶ የሚፈጸም መሆኑ ቢታመንም ስለተወካዮቹ ጥቆማ፣ ስለ ምርጫው ሂደት፣ የተወካዮቹ መደባዊ ስብጥርና በመሳሰሉት ላይ የሌሎች ሶሻሊስት አገሮችን ልምድ በመጠኑም ቢሆን ማየት በእነዚህ ነጥቦች ላይ አጠቃላይ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል።

እንደሚታወቀው የሶሻሊስት አገሮች የመንግሥት አካሎች ከአነስተኛ የአስተዳደር ክልል እስከ ከፍተኛው አካል የሚዋቀሩት በምርጫ ላይ በመመሥረት ነው።

ሁሉንም በምርጫ ላይ ማሳተፍ፣ እኩል የምርጫ መብት፣ ተወካዮችን በቀጥታ መምረጥና በምርጫ ወቅት ከተጽዕና ነፃ በሆነ መንገድ በካርድ በምሥጢር መምረጥ በሁሉም ሶሻሊስት አገሮች ተቀባይነትን ያገኘ የምርጫ አፈጻጸም ሥርዓት የሚገዛባቸው መርሆዎች ሲሆኑ በዕጩነት የሚመዘገቡ ተመራጮች የሚቀርቡት በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በሠራተኞች ቡድን አማካይነት ነው። በተመራጮችና በመራጮች መካከል የጠበቀ ግንኙነት ከመኖሩም ሌላ መራጮች እምነት ያጡባቸውን ተወካዮች መልሰው ከሥልጣን ሊያወርዱቸው ይችላሉ። [26]

ከእነዚህ የምርጫ አፈጻጸም መርሆች መገንዘብ እንደሚቻለው ከምርጫው መነሻ ጀምሮ ምርጫው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ

Digitized by Google

ድረስ ሕዝቡ በተደራጀባቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካይነት ወይም ሠርቶ አደሮች በቡድን ተወያይተው ግን እነሱን ወክሎ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ በየደረጃው ላሉት የኃላፊነት ቦታዎች መመረጥ እንደሚገባው በግጨን ንቁ ተሳትፎ ስለሚያደርግ የቀረቡለትን ብቻ እንዲመርጥ የሚወሰን ሳይሆን አቅራቢውም መራጩም እራሱ ሕዝቡ ነው ። የሚመሠረተው መንግሥት ዲሞክራሲያዊነትና የጥንካሬ ምንጩም ይኸው ነው ።

የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ሁሉ በምርጫ የሚሳተፉ በመሆናቸው በዘር ፣ በሃይማኖት በትምህርት ደረጃ ፣ በመኖሪያ አካባቢ ፣ በኅብረተሰብ ክፍል ፣ በሥራ ወይም በሀብት ልዩነት ሳይደረግባቸው በዜግነት መብታቸው ተጠቅመው በአካባቢ የአስተዳደር ክልልና (ወረዳ ፣ አውራጃ ፣ ክፍለሀገር ፣)በከፍተኛው የመንግሥት አካል ውስጥ ተወካዮቻቸውን ይመርጣሉ ፤ ይመረጣሉ ። ገበሬ ፣ወዝ አደር ፣ ወታደር ፣ ምሁር ፣ ገጠሬ ፣ ከተሜ ፣ ወንድ ፣ ሴት ፣ ወዘተ. ሳይባል የሁሉም የምርጫ ድምፅ እኩል ሆኖ በከፍተኛው የመንግሥት አካል ውስጥ የሚመረጡት ተወካዮች ብዛት እንደመደቡና የኅብረተሰብ ክፍሉ ማኅበራዊ አቋም ሁኔታ የሚለያይ ነው ። የሠራተኛው መደብ በተጠናከረባቸውና የሶሻሊስት ሥርዓት በመሠረቱ አገሮች ከሌሎች መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች አንፃር ሲታይ ይህ መደብ ከፍተኛ የውክልና ቁጥር ይዟል ።

በሶቭዬት ኅብረት በ1974 በተካሄደው ምርጫ ከፍተኛ የሶቭዬት (ሱፕሪዬም ሶቭዬት) አካል ውስጥ የነበሩትን የተወካዮችን ስብጥር እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል ። በአካሉ ውስጥ ከነበሩት ከ1,517 አባላት ውስጥ ሠራተኞች (32.8%) ፣ በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር የተደራጁ ገበሬዎች 271 (17.9%) ፤ ማኔጀሮችና በተለያዩ የብሔራዊ ኢኮኖሚ መስክ የተሰማሩ በሰሎች (ስፔሺያሊስቶች) 77(4.7%) ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች 215(14.2%) ፣ የፓርቲ ባለሥልጣኖች 241(15.9%) ፣ የሠራተኛና የወጣት ማኅበራት ተጠሪዎች 17(1.1%) ፣ በሳይንስ ፣ በባህል ፣ በኪነ ጥበብ በትምህርትና በጤና ፣ በኅትመት መስክ የተሰማሩ ሠራተኞች 142(9.3%) እና የጦር ኃይል አባሎች 56(3.7%) ነበሩ ።[27]

ከፍተኛው የመንግሥት አካል በየአገሩ የተለያየ ስያሜ ፣ አደረጃጀትና አሠራር ይኑረው እንጂ የጋራና አጠቃላይ በሆኑ የአደረጃጀትና የአመራር መርሆዎች ይገዛል ። ለምሳሌ የቡልጋሪያ ፣ የሀንጋሪና የቭዬትናም ከፍተኛ የመንግሥት አካሎች ብሔራዊ ሸንጎዎች (ናሽናል አሴምብሊ) ሲባሉ የኮሪያ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ‘ከፍተኛ ሕዝባዊ ሸንጎ’ (ሱፕሪም ፒፐልስ አሴምብሊ) ይባላል ። ይህ የቅርጽ ልዩነት ነው። ይዘታቸውን ስናይ ግን ሁሉም የሚመሠረቱት በምርጫ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ ውክልና ቁጥር የተሰጠው ለሠራተኛው መደብ ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አወቃቀር በማርክሳዊ ሌኒናዊ የመንግሥት አወቃቀር መርህዎች ላይ የሚመሠረት በመሆኑ የሶሻሊስት አገሮችን አጠቃላይ የመንግሥት አወቃቀር ባሕርያትን ይጋራል ። በመንግሥቱ አወቃቀር ሂደት ውስጥ በሁለንተናዊ የዕድገት ደረጃችን ፣ በአገራችንና በሕዝቡ ተጨባጭና ልዩ ፖለቲካዊ ባሕርይ ላይ ተገቢው ትኩረት የሚደረግበት ቢሆንም «በሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን አካል ብሔራዊ ሕዝባዊ ሸንጎ ሲሆን » በውስጡም በተለይ የሠራተኛው መደብ ልዕልና እያገኘ እንዲሄድና ብሔረሰቦችም ተገቢው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል።[28] የሸንጎው አመሠራረትም በሕዝብ ምርጫ ይሆናል ።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ሰፊው ሕዝብ በኢሠፓ አመራር ሰጭነት የራሱን መንግሥት ለመመሥረት ፣ የነፃነት አድማሱን የበለጠ ለማስፋትና ለማረጋገጥ

Digitized by Google

በሚጣደፍበት ወቅት የአድኅሮት ኃይላት በዝምታ እንደማይመለከቱ የታወቀ ነው።

አድኃርያን አጋጣሚውን ሁሉ በመጠቀም ሕዝቡ ለግንባታው እንዳይሰለፍ ለሚያደርጉት ሙከራ ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች አንዱ ሕዝቡ በዲሞክራሲ ጥያቄ ስም «ጭፍን ብሔረተኝነትን የሙጥኝ ብሎ ዓለምአቀፋዊ አጋር እንዲያጣና አብዮታችን ለጥቃት እንዲጋለጥ» [29] ማድረግ መሆኑ የታወቀ ነው። ለዚህም ጊዜና ሥፍራ እየለዩ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀማቸው በተደጋጋሚ ታይቷል። እስካሁንም እያንዳንዱን እርምጃ ለማሰናከል ያልተሳኩ ሙከራዎች ማድረጋቸው ይታወቃል ። ሆኖም አብዮቱ ሙከራዎችን በማከሸፍና ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከረ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማዋቀር ከተቃረበበት ታላቅ የድል እርከን ላይ ደርሷል ።

በዚሁ መሠረት በአገራችን አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት በማዋቀር ለሶሻሊዝም መሠረት ለመጣል ኢሠፓ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ይገኛል። ሌሎች የሥርዓቱ አካላት ከኢሠፓ በሚያገኙት አመራር ለሁለንተናዊው ግንባታ በየትግል መሥመራቸው የሚሰለፉ ሲሆን «የኢሠፓ ግንባር ቀደምትነት የሚገለጸው የፖለቲካ ሥርዓቱ እምብርት በመሆን በሚሰጠው አመራር ነው።» [30] የመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ኢሠፓ በሚቀይሳቸው አጠቃላይ ፖሊሲዎች መሠረት በመሆኑ በሂደት ውስጥ ሕዝቡንና ፓርቲውን የሚያገናኙ ድልድይ ይሆናሉ ።

ፓርቲ አመራር ሰጭ በመሆኑ የመንግሥት አካሉችን የየዕለትና ዝርዝር ሥራዎች ተክቶ አይሠራም። ፓርቲው የሥርዓቱ እንቅሳቃሽ ሞተር እንጂ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶችን የሚተካ አይደለም። ኢሠፓ አመራር በመስጠት የሁሉም መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሚና ከፍ እንዲል እንቅስቃሴያቸው ጤናማ እንዲሆንና ተደጋጋፊነት እንዲኖረው ያደርጋል ።

ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ለማጠናቀቅና ለሶሻሊዝም መሠረት ለመጣል ለሚደረገው ትግል የኢሠፓ አስተማማኝ ኃይል ሰፊው ሕዝብና የተደራጀባቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች መሆናቸው ግልጽ ነው ። ሕዝባዊ ድርጅቶች በዲሞክራሲ መድረክነታቸው እስካሁን ያስገኙት ልምድ እጅግ የላቀ ነው ። ሕዝቡ በየፈርጁ በተደራጀባቸው ድርጅቶች አማካይነት እራሱን በራሱ የመዳኘት ፣ ለአካባቢው ችግር መፍትሔ የመፈለግና በብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ጉዳዮች ንቁ ተሳትፎ የማድረግ ባህሉን እያዳበረ ነው ። ይህም ለሚመሠረተው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መሠረት ጥሏል ለማለት ያስደፍራል። በሪፐብሊኩ መንግሥት ምሥረታ ሂደት [illegible] የሕዝቡ ተሳትፎ በየደረጃው ስፋትና ጥልቀት እያገኘ እንዲሄድ አመቺ መድረኮችን መፍጠርና የሕዝባዊ ድርጅቶችም ሚና በየጊዜው እየጐለበተ እንዲሄድ ማድረግ የኢሠፓ ተግባር ይሆናል ።

ሰፊው ሕዝብ አብዮቱ ባስገኛቸው ታላላቅ ድሎች አማካይነት የዲሞክራሲያዊ መብቱን እድማስ ያሰፋው መሆኑ ይታወቃል ። የአሁኑ የዲሞክራሲያዊ መንግሥት ምሥረታም ይህንኑ መብት በይበልጥ የተሟላ የሚያደርግና ወደላቀ ደረጃ የሚያደርስ፣ ለሶሻሊዝም መመሥረት አመቺ ሁኔታዎች የሚፈጥር ነው።በፓርቲው አመራር የሚመሠረተው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና የሕዝቡ ፖለቲካዊ ተሳትፎ በይበልጥ የሚረጋገጥበት መድረክ እንደሚሆን ከወዲሁ መገንዘብ ይቻላል ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1- <u>የሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ምሥረታ ዝግጅት፡</u> ለኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበ፡ መጋቢት 1977፡ አዲስ አበባ፡ ገጽ 13 (ያልታተመ።)

2- የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ፕሮግራም፡ አዲስ አበባ፡ መስከረም 1977 ገጽ 41።

3. የኢሠፓ ፕሮግራም ገጽ 41-42

4- የሕዲሪኢ ምሥረታ ዝግጅት፡ ገጽ 42 (ያልታተመ።)

5. Constitution of the Union of Soviet Socialist Republics of 1978, Art. 30.

6. Constitution of German Democratic Republic, Art. 6 (ii), as quoted by A.Kh. Makhnenko, <u>*The State Law of the Socialist Countries*</u> (Moscow: Progress Publishers, 1976), p. 261.

7. Constitution of the Union of Soviet Socialist Republics, Art, 95.

8. A. Kh. Makhnenko, <u>*The State Law of the Socialist Countries*</u> (Moscow: Progress Publishers, 1976), p. 259.

9. V. Chirkin and Yudin, <u>*A Socialist Oriented State,*</u> (Moscow: Progress lishers, 1983), p. 65.

10. V.I. Lenin, <u>Collected Works,</u> Vol. 26, 1977, p. 256, as quoted by V. Chirkin and Yu. Yudin, pp. 62-43.

11. Constitution of the Union of Soviet Socialist Republics, Art. 48.

12. Makhnenko, pp. 252-257.

13. Ibid., pp. 65-66.

14. Ibid., p. 66.

15. Ibid.

16. Chikin and Yudin, pp. 66-67.

17. Makhnenko, pp. 66-67.

18. V. Chirkin and Yu. Yudin, p. 80.

19- የሕዲሪኢ ምሥረታ ዝግጅት፡ ገጽ 35። (ያልታተመ)

20. V. Chkikvadze, <u>*The State Democracy and Legality in the USSR*</u> (Moscow: Progress Publishers, 1972), p. 261.

21- የሕዲሪኢ ምሥረታ ዝግጅት፡ ገጽ 77

22. Makhnenko, op. cit., p. 239.

23. The Work of N. G. Alexandrov, as quoted by Makhnenko. op. cit., p. 266.

24- የሕዲሪኢ ምሥረታ ዝግጅት፤ ገጽ 79

25- የኢሠፓ ፕሮግራም፤ ገጽ 42።

26. Makhnenko op. cit., p. 271.

27. Ibid., p. 299.

28- የኢሠፓ ፕሮግራም፤ ገጽ 42።

29- ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ ለመሥራች ጉባኤ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ገጽ፡ 49።

30-የኢሠፓ ፕሮግራም፡ ገጽ 39።

Digitized by Google

ፕሮፓጋንዳ ለምንና እንዴት

—አጭር ቅኝት

ሰለሞን ለማ

20ኛው ምዕት ዓመት ከፍተኛ ማኅበራዊ ለውጦች የታዩበት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የመጠቁበት፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ለአብዮታዊ ትግል የተነሣሡበት፣ በቡርዧውና በሠራተኛው መካከል ያለው የመደብ ትግል እጅግ የተካረረበትና በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሠራተኛው መደብ ሶሻሊስት አብዮት አካሂዶ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን የበቃበት ነው። ይህ ወቅት ሶሻሊዝም ያበበበትና «ዘላለማዊ» ነው ተብሎ ይነገርለት የነበረው ካፒታሊዝም ውድቀቱ የማይቀር መሆኑ በተግባር የተረጋገጠበት ነው። በመሆኑም ይህ ዘመን ካለፉት ዘመናት ሁሉ አበይት ውጤት የታየበት ነው ማለት ይቻላል።

ክላይ ከተጠቀሱት ሌላ ያለንበት ዘመን የፕሮፓጋንዳ ዘመን ነው ማለትም ይቻላል። ዛሬ በመገናኛ ብዙኃን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለማቋረጥ የሚስተጋባው የፕሮፓጋንዳ መጠን ለገምት የሚያስቸግር ነው።

ፕሮፓጋንዳ በጥቅል ትርጉሙ ሐሳቦችን ፊት ለፊት፣ በማንባር ወይም በሌሎች ዘዴዎች አማካይነት ማሰራጨት ማለት ነው። ቡርዧው ተራማጅ መደብ ሆኖ በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ባለ ጊዜ ፊውዳሊዝምን ገርስሶ የበላይነቱን ለመጨበጥ ባደረገው ሰፊ የርዕዮተዓለምና የፖለቲካ ትግል፣የሰፊውን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ፕሮፓጋንዳን ዓይነተኛ መግሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል። ቡርዧው በወቅቱ ተራማጅ ሐሳቦችን ይዞ በመቅረብ የፊውዳሊዝምን የብዝበዛ ባህልና የዕድገት ማነቆነት በማጋለጥ ከፊውዳል ፊላጭ ቀራጮችና ለእነሱው ጥቅም ከቆሙ የእምነት ተቋሞች ጋር ጭምር ሰፊ ትግል አድርጓል። ቡርዧው ፕሮፓጋንዳ (ፕሮፓጌር) የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ የወሰደው ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነው። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በ17ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ ላይ የካቶሊክ እምነትን የማስፋፋትን ሥራ ወይም ስበካን ፕሮፓጋንዳ በሚል ስያሜ ትጠራ

Digitized by Google

ነበር ። ቡርዧውም የራሱን ሐሳብ ለማስራጨት የሚያካሂደውን የሐሳብ ጦርነት በዚሁ አጠራር ሰይሞታል ። ፊውዳሎች የነበራቸውን የበላይነት ላለማጣትና ሥርዓታቸውን ከመፍረስ ለማዳን ፣ ቡርዧው የሚያሰራጨውን ሐሳብ ለማንኳሰስ ፣ ታሪካዊውን እውነታ ሕዝቡ እንዳይቀበል ለማድረግ ያላደረጉት ሙከራ አልነበረም ። ይሁንና ፊውዳላዊ ፕሮፓጋንዳ ከቡርዧው ፕሮፓጋንዳ አንፃር ሲታይ ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ ሕዝቡን ከጐኑ ሊያሰልፍ አልቻለም ። ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ የማታለያ ዘዴው ውጤት ሊያስገኝለት አልቻለም ።

ቡርዧውም በበኩሉ ለጊዜው የድል ባለቤት ለመሆን ቢበቃም የተራማጅነት ባሕሪው ለብዙ ጊዜ ሊቆይ አልቻለም ። «እኩልነት ፣ ነፃነትና ወንድማማችነት» የሚለው መፈክሩ ምንነት በተግባር ሲፈተንና ባዶነቱ ሲታወቅ ፣ ማለትም ቡርዧው የተራማጅነት ታሪካዊ ተልዕኮው አክትሞ ወደአድኃሪ መደብነት ሲሸጋገር የእሱም ፕሮፓጋንዳ እንደፊውዳሉ ፕሮፓጋንዳ ዘመኑ ሊያከትምበት ችሏል ። ካፒታሊዝም በፈጠረው የወዝአደሩ መደብና በቡርዧው መደብ መካከል ያለው የመደብ ትግል እየተካረረና ስለ ሶሻሊዝም የሚካሄደው አስተምህሮ እየተስፋፋ ሲሄድ የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ከፀረ ፊውዳሊዝም ወደ ፀረ ወዛደርነት ተሸጋገረ ። የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ በይዘቱም ሆነ በቅርፁ የቡርዧው ሥርዓት እንደተካው እንደፊውዳሉ ሥርዓት ፕሮፓጋንዳ ሁሉ የሕዝቡን አስተሳሰብና ታሪካዊ እውነታ በማዛባት ላይ አተኮረ ። በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ያለውን የተራማጁን መደብ ሞራላዊና ርዕዮተዓለማዊ ፋይዳዎች ከታሪካዊ እውነታ አኳያ ያንፀባርቅ የነበረው የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ አይሎ ሲወጣ ታሪክን የሚያዛባ አዝታጭ መደብ ነፀብራቅ ለመሆን ተገደደ ። ዛሬ ቡርዧው የካፒታሊዝምን የፍትሕ መገኛ መሆን ለማሳመን አንዳችም ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ስለሌለው በግልጹ የሐሳብ ጦርነት ፊት ለፊት ከመግጠም ይልቅ በየጊዜው ታክቲክና ስትራቴጂውን በመቀየር ውሸትን እውነት ፣ እውነትን ውሸት ለማድረግና የታሪክን ዕድገት ለመገደብ እየሞከረ ነው ። የቡርዧውን ፕሮፓጋንዳ ዕድገት ደረጃ በደረጃ ብንመለከተው መጀመሪያ ፀረ ፊውዳል ፣ ከዚያም በማከታተል ፀረ ወዛደር ፣ ፀረ ሶሻሊዝምና ፀረ ሰላም ሆኖ እናገኘዋለን ። ይሁንና ይህ የቅርፅ ልዩነት እንጂ በየጊዜው የተከሰቱት የቡርዧው የፕሮፓጋንዳ ስትራቴጂዎች ግብ ዞሮ ዞሮ የቡርዧውን ጥቅም ማስጠበቅ ነው ። ቡርዧው ይህን ማድረጉም ለህልውናው ሲል የግድ ነው ።

ከፊውዳሊዝም ወደካፒታሊዝም፣ከዚያም ብዝበዛ አልባ ወደሆነው ሥርዓተ ማኅበር በሚደረገው ሽግግር ፕሮፓጋንዳ የተጫወተውና የሚጫወተው ማኅበራዊ ሚና እያደገ መጥቷል ። ይሁንና ያለንበት ዘመን ሁለቱ ተፃራሪ መደቦችና ሥርዓቶች የገጠሙት ትግል ከቀድሞዎቹ ሁሉ የተካረረ በመሆኑ በፕሮፓጋንዳውም መስክ የሚካሄደው ትግል እንዲሁ የተካረረ ሆኖአል ። «ከአንዱ ሥርዓተ ማኅበር ወደሌላው የሚደረገው ሽግግር ያለ ገጭትና ችግር ሊከናወን የሚችል አይደለም ። ምክንያቱም ይህ አንዱን ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት በሌላ የመተካት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ማኅበራዊና ኅሊናዊ አብዮትም ነው ። በመሆኑም በአዲሱና በአሮጌው ፣ በሟቹና በታዳጊው መካከል ፉክክር ይኖራል ። ይህም በበኩሉ የርዕዮተዓለም ትግሉን መካረርና ማለትም በተፃራሪዎቹ ንጽረተዓለሞች ፣ (World outlook) ፍልስፍናዎች . . . መካከል ያለውን ውድድር የሚወስን ይሆናል ። »[1]

ከ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ዕድገት በማርክሳዊ ሌኒናዊ ሳይንስ የሚያንፀባርቀው የሠራተኛው መደብ ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ ትምህርት በቡርዧው ላይ የበላይነትን ተቀዳጀ ። የሠራተኛው መደብ አብዮ

Digitized by Google

ታዊ ትግል ሳይንሳዊ በሆነና ጠንካራ ንድፈ ሐሳባዊ መሠረት ባለው ፕሮፓጋንዳ ሲታገዝ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሕዝቦች በማኅበረ ፖለቲካዊ ሂደት ውስጥ እየተሳተፉና የሠራተኛው መደብም «ዓለምን ለመለወጥ» የተነሣ መሆኑ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ መጣ።

የካርል ማርክስ፣ የፍሬደሪክ ኤንግልስና የሌኒን ሳይንሳዊ ጽሑፎች፣ ሠራተኛው መደብ ከቡርዧው ጋር ያደረገው የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ትግል፣ የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች ያካበቱት ሰፊ ልምድ ለዛሬው የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ሳይንሳዊ መሠረት የጣሉና የዕለት ተዕለት መመሪያዎችም ናቸው።

ዛሬ በዓለማችን ላይ በሚካሄደው የከረረ የርዕዮተ ዓለም ትግል የፕሮፓጋንዳ ሚና ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ጎልቶ ይታያል። ያለንበት ወቅት ለብሔራዊ አርነት፣ ለእኩልነት፣ ለሶሻሊዝምና ለዓለም ሰላም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች በየዕለቱ ትግል የሚያካሂዱበት፣ ማለትም በታሪካዊው ሂደት ውስጥ ሰፊው ሕዝብ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግበት ወቅት ነው። ይህ ሁኔታ ለዛሬው የፕሮፓጋንዳ ሚና ልቆ መገኘት ዋንኛው ነባራዊ ሁኔታ ነው።

ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድል አድርጎ፣ ለዘመናት ለጉልበቱና ለሀገሩ ባዕድ ተደርጎ የኖረው ወዛደርና ገበሬ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን ሲበቃና ለዓለም ተመዝባሪዎች አዲስና ብሩኅ የነፃነት ምዕራፍ ሲከፈት ዓለም በሁለት ተፃራሪ ጎራዎች ተከፈለች። እያደርም በዓለም የኃይሎች አሰላለፍ ላይ ሥር ነቀል ለውጥ ታየ። የሰላም፣ የእኩልነትና የሶሻሊዝም ኃይሎች በየጊዜው እየተጠናከሩና እየበዙ ብሎም አያሌ ተከታዮች እያገኙ በመሄዳቸው ካፒታሊዝም እንዲያፈገፍግ ተገደደ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የብዙ ሚሊዮን ሕዝቦች የሕይወት መመሪያ ሆነ። ለፕሮፓጋንዳ ሚና ማደግ ይህ ሌላው ነባራዊ ሁኔታ ነው።

ካፒታሊዝም ብቻውን ይዞት የነበረውን ዓለምአቀፍ መድረክ ቢቻል መልሶ ለመያዝ ካልሆነም ቀራቹን ላለማጣት ባለው ሰፊ የፕሮፓጋንዳ አውታር ኮሚኒዝምን፣ ለነፃነትና ለእኩልነት፣ ለዕድገትና ለዓለም ሰላም የሚካሄደውን ትግል እየተፈታተነ ነው። በአንፃሩ የዓለም አብዮታውያን ለፍትሕ መስፈን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር፣ በኢምፔሪያሊዝም፣ በጦረኝነትና በአድኅሮት ላይ ርዕዮተ ዓለማዊ የበላይነት ለመቀዳጀት፣ በሰላም አብሮ የመኖርን መርህ በስፋት ለማሳወቅ፣ የዓለም ሠራተኞችንና ሰላም ወዳድ ኃይሎችን ይበልጥ ለማቀራረብ፣ የካፒታሊዝምን የብዝበዛ፣ የዕብሪትና የወረራ ባሕርይ ለማጋለጥ፣ በአድርባይነት፣ በክላሽነትና በትምክህተኝነት ላይ የማያወላውል ትግል ለማካሄድ ወዘተ. ለኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ከፍተኛና ልዩ ትኩረት ይሰጣሉ። በየጊዜው ከልምድና ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር እየዳበረና በሳይንሳዊው ርዕዮተ ዓለም ላይ በተመሠረተ የፕሮፓጋንዳ አሠራር በሠለጠኑ ካድሬዎች (ፕሮፓጋንዲስቶች) እንዲካሄድ ያደርጋሉ።

ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ምንድን ነው?

ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ስለተፈጥሮና ኅብረተሰብ ዕድገት፣ ዕድገቱ ስለሚገዛባቸው ሕጎች፣ እነሱም የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት ለማርካት በሚያስችል መልክ ስለሚገሩበት ሁኔታ ሳይንሳዊ ዕውቀት ለሰፊው ሕዝብ ማስጨበጥ ነው። ይህ ሊከናወን የሚችለው ደግሞ ሳይንሳዊ በሆነና በተግባር በተፈተነ ንድፈሐሳብ ሲመራ ወይም በእውነታ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱም ትክክለኛና ሳይንሳዊ ንድፈሐሳብ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው። የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ መሠረትም ይህ ንድፈሐሳብ ነው። ፕሮፓጋንዳው የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለማዊ ተግባር ከፍተኛ ትኩረት የሚያደርግበትና የኅብረተሰቡን ስትራቴጂያዊ ግብ ለመምታት የሚያስችሉ «ጥቂት ስዎች (በአንፃራዊ አነጋገር) በአንድ ወቅት ሊገነዘቧቸው ስለ

Digitized by Google

ሚገቡ ብዙ . . . ሐሳቦች» 2 የሚያወሳ ነው ። ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ የሚመነጨው ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም የእውነታ አስተምህሮ (Doctrine) ነው ። እውነታ የተጨባጨ ማለትም የገሀዱ ዓለም ትክክለኛ ነፀብራቅ ነው ። ማንኛውም ሳይንሳዊ ንድፈ ሐሳብ ወይም ዕውቀት ከዚህ ትክክለኛ ነፀብራቅ የሚመነጭ ሲሆን እውነታነቱም ሆነ ተጨባጭነቱ የሚረጋገጠውም በዚሁ ነው። ያለን ፣ ተጨባጭ የሆነን ነገር የማያንፀባርቅ ንድፈሐሳብ ሳይንሳዊ ሳይሆን የማይዳሰስ ፈጠራና ማደናገሪያ ብቻ ነው ። የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ዓላማ በተግባር የተፈተነ ነባራዊ እውነታን ፣ ተጨባጭና ተአማኒ የሆነ ዕውቀትን ለሰፊው ሕዝብ ማስጨበጥ ነው። በመሆኑም የኮሚኒስትና የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ መሠረታዊ መለያ የሆነው ይህ እውነታን በትክክልና በተሳሳተ መንገድ የማንፀባረቅ ሁኔታ ነው ። እውነታን በትክክል አለማንፀባረቅ ደግሞ ማስተማር ሳይሆን ማሳሳትና ማደናገር ብቻ ነው ።

ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ የተፈተነ እውነታን ማሰራጨት ነው ብለናል ፤ ይሁንና ይህን እውነታ የማስጨበጡ ተግባር ቀዳሚ ተግባር እንጂ የመጨረሻ ግቡ አይደለም። ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ እውነታን በማስጨበጥና የመደብ ንቃተኅሊናን በመቅረፅ ሰፊው ሕዝብ የብዝበዛን ባሕርይና የሚወገድበትን ሳይንሳዊ ስልት ተገንዝቦ በጠላቶቹ ላይ እንዲነሣና የራሱን ፍላጎትና ጥቅም እንዲያስከብር ለማድረግ የሚያስችል መሣሪያ ነው ። በመሆኑም ለሠራተኛው መደብ ጎጂ የሆነውን አሮጌውንና አድኃሪውን ሁሉ የመናድ ፣ ለአዲሱና ለተራማጁ መንገዱን የማመቻቸት ፣ አሮጌውን የማፍረስና አዲሱን የመገንባት ተግባር ነው ። ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ሐሳብን ወደቁሳዊ ኃይል የመለወጥ ፣ በመደብ ትግሉ ውስጥ ንድፈሐሳብን ከተግባር ማዋሃጃ መሣሪያ ነው ።

ፕሮፓጋንዳ አእምሮአዊ (ኅሊናዊ) ግንኙነት ነው ። በዚህ ግንኙነት ሂደት ውስጥ በልዩ ልዩ የፕሮፓጋንዳ ዘዴዎች የተወሰኑ ሐሳቦች ከአንዱ ክፍል ወደሌላው ይተላለፋሉ ። ሐሳቦችን በማስተላለፍና በመግለጽ ብቻም አይወሰንም ፤ ስሜትን ይኮረኩራል ፤ ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ይገፋፋል ። የሚተላለፉት ሐሳቦች አንድም ማኅበራዊ ዕድገትን የሚያፋጥኑና ተራማጅ ይዘት ያላቸው ወይም ማኅበራዊ ዕድገትን የሚጎትቱና አድኃሪ ይዘት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ ። ስለዚህም ከመደብ በላይ ወይም ሁለንታዊ የሆነ ፕሮፓጋንዳ የለም ፤ ፕሮፓጋንዳ መደባዊ ነው ።

ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ የሠራተኛውን መደባዊ ንቃተኅሊና በማጐልበት ፍትሕና እኩልነት የሰፈነበት አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት ኅሊናዊ ሁኔታን በማመቻቸት ለተግባር ያነሣሣል ። እውነትን የሚያንፀባርቅ ፣ የሰፊውን ሕዝብ ብሶት ገሀድ የሚያደርግና ከዚህም ውስጥ የሚወጣበትን መንገድ የሚያመለክትና የሚመራ ነው ። በመሆኑም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ሕዝቦችን ስሜት ይስባል ።

ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ በሀቅ ላይ የተመሠረተና የሰፊውን ሕዝብ ነባራዊ ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ቢሆንም የታለመለትን ግብ ሊመታ የሚችለው ከዚህ መሠረታዊ ባሕርዩ በመነሣት ትክክለኛ ስልትና ዘዴ ሲከተል ብቻ ነው ። የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ፍሬያማነት መለኪያ የሰፊው ሕዝብ አስተሳሰብ ፣ ማለትም የመንፈሳዊ ባህሉ ዕድገትና ይህም የሚንፀባረቅበት ተግባራዊ እንቅስቃሴው ቢሆንም በሳይንሳዊ የማርክሲዝም ሌኒንዝም የፕሮፓጋንዳ መርህ ላይ መመሥረቱ ትድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ። እነዚህ መርሆዎች ምን ምን ናቸው ?

የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ መርሆዎች

1. ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ለሠራተኛው መደብ ፍላጎት ያለማወላወል የቆመ ፣ ማንኛውንም የአድርባይነትና የከላሽነት አዝማሚያ አጥብቆ የሚዋጋና ለእነዚህ አዝማሚያዎች አንዳችም ቀዳዳ የማይከ

Digitized by Google



የኢምፔሪያሊዝም «ነፃ መረጃ» የቡርዧው ጥቅም ጠባቂ ነው ።

ፍት ነው ። ማንኛውንም ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ጉዳይ ከሠራተኛው መደብ ፍላጎትና ከተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የሚገመግም በወገናዊነት ላይ የተመሠረተ ነው ። በመሆኑም የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ መሠረታዊ መርህ ወገናዊነት ነው።

የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ የሠራተኛውን መደብ እንቅስቃሴ ፣ በአጠቃላይ ኮሚኒዝምን በመፃረር ሰፊ ዘመቻ በያዘበት በአሁኑ ወቅት እያንዳንዱን የቡርዧ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከመደብ አንፃር የመተንተንና ቡርዧው «መረጃ» በሚል ሽፋን የሚረጨውን መርዝ ምንነት፣በአጠቃላይ መደባዊ ባሕርይ የሌለው ወይም ከመደብ ውጭ ነው ተብሎ የሚሠራጨውን የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ፀረ ሕዝብነት ማጋለጥ የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ አንዱ ትኩረት ነው ። በወቅቱ የተፋፋመ የመደብ ትግል ምርጫው የቡርዧ ወይም የሶሻሊስት ርዕዮተዓለም ብቻ ነው ። ሌላ ወይም የሁለቱ የጋራ የሆነ አማራጭ የለም ። ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ለሠራተኛው ወገናዊ በሆነ አቋም ላይ በመመርኮዝ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጥቅም ያስከብራል ፤ የሠራተኛውን መደባዊ ንቃተኅሊና ያጐለብታል ፤ የቡርዧውን መሰሪ ፕሮፓጋንዳ ያጋልጣል ። በመደባዊ ወገናዊነት ላይ ያልተመሠረተ ንቃት የመደብ መፍረክረክን ያስከትላል። ይህ ደግሞ ዞሮ ዞሮ የሚያመራው ወደ ሽንፈት ነው ። በመሆኑም ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ በጠንካራ ወገናዊነት ማንኛውንም ዓይነት አድርባይነት ፣ ከላሽነትና ከማርክሲዝም ሌኒንዝም የሚፈነገጥ አዝማሚያ ፣ በአጠቃላይ የሠራተኛውን የመደብ ጠላቶች ያለማወላወል መዋጋት ይኖርበታል ።

2. ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሐሳቦችን በማሰራጨት የርዕዮተዓለሙንና የፖለቲካውን ግንባር ቀደም ጥያቄዎች በማንሣት የመደብ ጠላትን በማጥቃት ላይ የተመሠረተ እንጂ ለጠላት የሚንበረከክ ወይም የጠላትን ጥቃት በመከላከል የተወሰነ መሆን የለበትም። የጠላትን ፕሮፓጋንዳ ይዘትና ባሕርይ በትድግሚያ ተገንዝቦ በአሳማኝ መረጃዎችና በሳይንሳዊ ትንታኔ ማጋለጥና ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል ። በመሆኑም ቀድሞ ወይም ፈጥና የሚያጠቃ እንጂ የጠላትን በትር የሚከላከል አይደለም ። ሠራተኛው መደብ በካፒታል የሚደርስበትን አጠቃላይ ብዝበዛ በማውሳት ወይም የሠራተኛው መደብ ጥቅም ከካፒታሊስቱ መደብ ጋር የሚፃረር መሆኑን በመግለጽ ብቻ የመደቡን ንቃተኅሊና ማጐልበት አይቻልም ። «ፈላጭ ቆራጩን አገዛዝ በሁሉም መልኩ በፖለቲካ ለማጋለጥ ካልቻልን የሠራተኛውን መደብ የፖለቲካ ንቃተኅሊና የማዳበሩን ተግባራችንን አላከናወንም ማለት ነው ። »[3]

3. ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ እንደቡርዧው ፕሮፓጋንዳ እውነትን የሚሸሽ ወይም የሚያደበዝዝ አይደለም ፤ ዋንኛ ባሕርዩ እውነታ ነው ። ይህ እውነታ ያሉ ድክመቶችን ማመንን ፣ የድክመቶቹን ባሕርይና መንሥኤ እንዲሁም የሚወገዱበትን መንገድ መጠቆምን ያጠቃልላል ። እውነታ የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ። እውነታ የሰዎችን ስሜት ለመሳብ የሚችል ፣ መተማመንን የሚፈጥርና ለነፃነት ፣ ለእኩልነትና ለፍትሕ ለሚታገሉ ሕዝቦች ድል ዋስትና የሚሰጥ ነው። የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ በእውነታ ላይ የተመሠረተ መሆን ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ሐቀኛና ሳይንሳዊ ከመሆኑ ባሕርይ የሚመነጭ ነው ። ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ የሚጠቀምበትን በተዋቡና ባሸበረቁ ቃላትና ዘዴዎች እውነታን አጣሞ የማቅረብን ስልት አጥብቆ ይቃወማል። የሁኔታን ይዘት በትክክል አለማመልከት ፣ ክስተታዊ ሁኔታን እንደቁም ነገር አጋኖ ማቅረብና የመሳሰሉት የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ባሕርያት አይደሉም ።

Digitized by Google

ስለኅብረተሰብና ተፈጥሮ ዕድገት ፣ ስለ
ማኅበራዊ ክፍሎችና መደቦች ሁኔታ
ትክክለኛ ግንዛቤ ሊገኝና በዚህም ላይ
ተመርኩዞ ዓለምን ለመለወጥ የሚቻ
ለው ነባራዊ ዕውቀት ሲጨበጥ ብቻ
ነው ። የሠራተኛው መደብ ፓርቲ በሚያ
ከናውነው ፕሮፓጋንዳ በሳይንሳዊው
ንድፈሐሳብና በተግባር የተረጋገጠውን
የሠርቶአደሩ ሕዝብ ይሁንታ ያለውን
እውነት ካላንፀባረቀ በፓርቲውና በሕ
ዝቡ መካከል ያለመተማመን ሊፈጠር ይች
ላል ። ሌኒን «ለፓርቲ አባላት» በተሰ
ኘው አነስተኛ ጽሑፉ የእውነትን መሠ
ረታዊነት በማውሳት «ነገሮችን ሸፋፍኖ
የማቅረብ ፍላጎት የለንም ። የወዛደሩ
ፓርቲ ፍላጎት እውነት ነው» [4] በማለት
ገልጿአል ።

4. ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ከሕዝቡ የየዕለት
ኑሮ ጋር የተጣጣመና የሕዝቡን መሠረ
ታዊ ፍላጎቶች በማንሣት መፍትሔ ጠቋ
ሚና ለዚህም ሕዝቡን የሚያነሣሣ መሆን
አለበት ። በወቅቱ ዓቢይ ጉዳይ ላይ በማ
ተኮር የሕዝቡን ስሜት ፣ እውነተኛ ፍላ
ጎትና አስተሳሰብ ተረድቶ ሕዝቡን የሚ
ያሳምንና ከአብዮታዊ እንቅስቃሴው ጐን
የሚያሰልፍ መሆን አለበት ። ኮሚኒስት
ፕሮፓጋንዳ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን
አስተምህሮና የኮሚኒስት ፓርቲውን
ፖሊሲ ለሠርቶአደሩ ሕዝብ በማሳወቅ
የሕዝቡን አብዮታዊ አስተሳሰብ ለማነ
ፅና ለተግባርም ማነሣሣት የሚችለው
እያንዳንዱን ታሪካዊ ክስተትና ሂደት
በሳይንሳዊ መንገድ በመተንተንና ለወ
ቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ተገቢውን ስልት
በመቀየስ ነው ። ለዚህም የተረጋገጡ
ማስረጃዎችንና ሐቆችን በማሰባሰብ፣የእ
ነዚህን ክስተቶች ዲያሌክቲካዊ ግንኙ
ነት ማብራራት አስፈላጊ ነው ።

5. ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ የልዩ ልዩዎቹን
የኅብረተሰብ ክፍሎች የባህልና የአጠቃ
ላይ ዕውቀት ደረጃ በመገምገምና የተቀ
ባዩን ሕዝብ (የተደራሲውን) ሥነልቦ
ናዊ ባሕርይ በመለየት እንደየባህሉ ፣ እን
ደየንቃት ደረጃውና ሥነ ልቦናዊ ባሕ
ርዩ በቀላሉ ሊገባና ስሜትን ሊስብ
የሚችል መሆን አለበት ። እንደሚያተ
ኩርበት የኅብረተሰብ ክፍል የፕሮፓ
ጋንዳውን ቅርፅና ይዘት ለመለዋ
ወጥ የማይችል የፕሮፓጋንዳ ሠራተኛ
የሚያገኘው ምላሽ አጥጋቢ ሊሆን አይ
ችልም ።

የፕሮፓጋንዳ ሳይንሳዊ መሠረት ማኅበ
ራዊ ሥነልቦና ነው ። ውጤታማ የሆነ ፕሮ
ፓጋንዳ ለማካሄድ የማኅበራዊ ሥነልቦናን
መሠረታዊ ሕጎች ጠንቅቆ ማወቅና በተግ
ባር መተርጐምም አስፈላጊ ነው ። የተደራ
ሲውን ማኅበራዊ ሥነ ልቦና ፣ ልማድ ፣ ባህል
የንቃተኅሊና ደረጃ ወዘተ. በሚገባ ሊገ
መግም የማይችል የፕሮፓጋንዳ ሠራተኛ
መልእክቱን ውጤታማ በሆነ መልክ ሊያስ
ተላልፍ አይችልም ።

ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ለማኅበራዊ ሥነ
ልቦና ጥናት ተገቢ ትኩረት ስለሚሰጥና
የሚነሣውም ከዚሁ በመሆኑ ለተለያዩ የኅ
ብረተሰብ ክፍሎች ተስማሚ የሆነውን የፕ
ሮፓጋንዳ ዘዴ አቀራረብና ይዘት በቅድ
ሚያ ለመወሰን ያስችላል ። ኮሚኒስት ፕሮ
ፓጋንዳ ምንጊዜም በመሠረታዊ የሰው
ልጅ ፍላጎት ላይ በማተኮር ፣ የሰው ልጅ
ፍላጎት የሚሟላበትን መንገድ የሚቀይስና
ወደዚያም የሚመራ ፣ የሰው ልጅን ችግር
ለመፍታት ትክክለኛ መፍትሔ የሚሻ ሳይ
ንሳዊ የሐሳብና የዕውቀት ማስተላለፊያ
ዘዴ ነው ።

ቡርዧው የሠራተኛውን ሕዝብ እንቅስ
ቃሴና ዓመፅ ስለሚፈራና ለማኅበራዊ ሥነ
ልቦና ያለው አመለካከትም ከዚሁ የሚመ
ነጭ በመሆኑ የሠራተኛውን ሕዝብ እንቅ
ስቃሴ ትጥየለሽ፣ ግብታዊና ልቅ አድርጎ
ይቆጥረዋል ። በመሆኑም ፕሮፓጋንዳ ለቡ
ርዧው ይህን «ልቅ» እንቅስቃሴ የመቆ
ጣጠሪያ ፣ የመግሪያና የሠራተኛውን ሕዝብ
ንቃተኅሊና በተወሰነ አቅጣጫ (የቡርዧ
ውን ፍላጎት በሚያረካ) እንዲያተኩር የማ

Digitized by Google

ድረጊያ መሣሪያ ነው ። የቡርዧ ፕሮፓጋንዳ ጠበብት ይህንን ሳይደብቁ ይናገራሉ ። የአሜሪካ የፕሮፓጋንዳ ንድፈሐሳብ ቀማሪዎች «ፕሮፓጋንዳ ከአንድ መደብ ጥቅም አኳያ ቀደም ሲል የታሰበ ዓላማን ለማሳካት ሆን ተብለው የተጣመሙ ሐሳቦችን እየተቆጣጠሩ ማሰራጨት»[5] ነው የሚል ትርጉም ሰጥተውታል ። በእርግጥም የቡርዧው ፕሮፓጋንዳ ዓላማ ይዘት ይኸው ነው።

የፕሮፓጋንዳ ሥራ በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን ዕውቀትና ልምድን የሚጠይቅ ጥበብ ነው ። የፕሮፓጋንዳ ሠራተኞች ዕውቀታቸውን ፣ ልምዳቸውንና ብቃታቸውን በየጊዜው ማሳደግ አለባቸው የሚባለውም ይህንኑ ጥበብ ተገንዝበው ከኅብረተሰቡ ዕድገት ጋር በተጣጣመ መልክ ውጤታማ ተግባር እንዲያከናውኑ ለማድረግ ነው ። ከላይ የተዘረዘሩት የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ መርሆዎች በሌኒን የተቀነባበሩ ሲሆን በተግባር ሂደት መጠናትና መዳበር ያለባቸው ናቸው ። የፓርቲ የዕለት ተዕለት መመሪያዎች ፣ የኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ መሠረቶች ናቸው ።

እዚህ ላይ ሌላው የርዕዮተ ዓለም ሥራ አንድ ዋነኛ ክፍል የሆነውን ማለትም የፖለቲካ ቅስቀሳን ምንነትና ከፕሮፓጋንዳ ጋር ያለውንም ተዛምዶ የሚመለከቱ አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦችን ማጤን ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳን ይበልጥ ለመረዳት ያስችላል ።

ቅስቀሳ በተራ ትርጉሙ «አንድን ሰው የተወሰነ ተግባር እንዲያከናውን መገፋፋት» ማለት ነው ። በማርክሳዊ ሌኒናዊ ጽንሰ ሐሳብነቱ ከአንድ አብዮታዊ ፓርቲ ፕሮግራም ፣ ፖሊሲ ፣ መመሪያና ውሳኔ ውስጥ የተወሰኑ ሐሳቦችን ለይቶ በማውጣትና በእነሱም ላይ በማተኮር የየዕለቱን ፖለቲካዊ ትግል በማጉላት ሰፊውን ሕዝብ ከፓርቲው ዙሪያ የማሰለፊያና ለተግባር ማነሣሻ መሣሪያ ነው ። በመሆኑም የቅስቀሳ ትኩረት ይበልጡኑ በፖለቲካው መስክ ሲሆን የፕሮፓጋንዳ ትኩረት ግን በርዕዮት ዓለሙ መስክ ነው ። ቅስቀሳ ከፕሮፓጋንዳ ይልቅ ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር የተቆራኘ የቅርብ ማስረጃዎችን የሚያነሣና «ጥቂቶች» ብቻ ሳይሆኑ ብዙኃኑ ሕዝብ ሊረዳው የሚችል ሐሳብን የሚያሰራጭ የታክቲክ መሣሪያ ነው ።

ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ አንድ የርዕዮተ ዓለም ፣ የፖለቲካና የመርህ መሠረት ያላቸው ቢሆኑም ይዘውት በሚነሡት ሐሳብ ስፋትና ጥልቀት ፣ በተደራሲያቸው (በተቀባዩ ሕዝብ) ዓይነትና ብዛት የየራሳቸው የሆነ ባሕርይ አላቸው ። የፕሮፓጋንዳ ሠራተኛውና ቀስቃሹ በአንድ ርእስ ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ ። ይሁንና አቀራረባቸው ይለያያል ።

ለምሳሌ በሴትኛ አዳሪነት ችግር ላይ ያተኩራሉ እንበል ። የፕሮፓጋንዳ ሠራተኛው በዚህ ርዕስ ላይ ሲያብራራ የካፒታሊዝምን መሠረታዊ ባሕርይ ፣ የተረፈ እሴትን ምንጭ ፣ የካፒታሊስት ክምችት ሂደትንና የሥራ አጡን ሠራዊት ሁኔታ ፣ የካፒታሊዝምን መሠረታዊ ቅራኔዎችና የሶሻሊስት አብዮትን አይቀሬነት ወዘተ. በስፋት ሊተነትን ይችላል ። እዚህ ላይ የፕሮፓጋንዳ ሠራተኛው ተደራሲዎች ምን ዓይነት መሆን እንደሚገባቸው መገመት ይቻላል ። እንዲህ ዓይነቱን ሰፊና ጥልቅ ትንተና ለመረዳት የተወሰነ የግንዛቤ ደረጃ ሊኖር ይገባል ። ለዚህም ነው ፕሮፓጋንዳ ብዙ ሐሳቦችን ሊገባቸው ለሚችል«ጥቂት» ሰዎች ማሰራጨት ነው የሚባለው ።

በተመሳሳይ ርዕስ ላይ የሚያተኩረው ቀስቃሽ ከላይ በተጠቀሱት ዝርዝር ርዕዮተ ዓለማዊ ወይም ጽንሰ ሐሳባዊ ጉዳዮችን አያነሣም ። ተደራሲዎቹ በሙሉ ወይም በአመዛኙ የሚያውቋትን አንዲት ሴተኛ አዳሪ በምሳሌነት በማቅረብ ፣ የትውልድ አካባቢዋን ፣ የቤተሰቦቿን ሁኔታ ፣ ወደሴተኛ አዳሪነት ሕይወት እንድትገባ ያስገደዳትን ሁኔታ በዚህ ሕይወት ውስጥ የደረሰባትን አስከፊ ሁኔታ በመዘርዘር አድማጩ ያንን ሕይወት ለመለወጥ እንዲነሣሣ ይገፋፋል ።

Digitized by Google

ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ እርስ በርስ ተደጋጋፊ ቢሆኑም እንደተጨባጩ ሁኔታ አንዱ ከሌላው የበለጠ ትኩረት ሊደረግበት ይችላል ። ፓርቲው ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በማንቃትና በማደራጀት የብዝበዛን ሥርዓት ለመገርሰስ በኅቡዕ በሚሠራበትና የፖለቲካ ሥልጣኑን በሚጨብጥበት ወቅት ሁለቱን በእኩልነት ደረጃ ላይጠቀምባቸው ይችላል ። አብዮታዊው ፓርቲ ገና ተመሥርቶ የሠራተኛውን መደብና የኅብረተሰቡን ሌሎች ተጨቋኝ ክፍሎች በርዕዮተ ዓለሙ ለማነፅ ትግል ሲያደርግ የፕሮፓጋንዳው ሚና ዓይነተኛውን ቦታ ይይዛል ። ይሁንና ፓርቲው ተጠናክሮ የፖለቲካ ፕሮግራሙን ቀይሶ ለአብዮታዊ እርምጃዎች ሲዘጋጅና የፖለቲካ ሥልጣኑን ለመያዝ ሲቃረብ ከፕሮፓጋንዳው ይልቅ የቅስቀሳ ሚና ጉልቶ ይወጣል ።

ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ የየራሳቸው የሆነ ባሕርይ ያላቸው ቢሆንም ፍጹም የተለያዩ ክስተቶች አይደሉም ። ሁለቱም ርዕዮተ ዓለምን ከፖለቲካ ፣ ዕውቀትን ከተግባር ፣ ሳይንሳዊ ኮሚኒዝምን ከሠራተኛው እንቅስቃሴ ጋር በማዋሐድ ከአንድ ታላቅ ግብ ላይ ለመድረስ አንዱ ሌላውን የሚያግዝበትና የሚያጠናክርበት እንጂ መስተጋብር የሌላቸው አይደሉም ።

ፕሮፓጋንዳ ሐሳቦች ፣ ትምህርቶች ፣ ንድፈ ሐሳቦች ፣ በአጠቃላይ መልእክቶች ከአንድ ሰው ወይም ቡድን ወደሌላው የሚተላለፉበት አእምሮአዊ (ኅሊናዊ) ግንኙነት ነው ብለናል ። ይህ ግንኙነት የሚከናወነው በሁለት ደረጃዎች ነው ። እነሱም ቀጥተኛ (ርቱዕ) እና ቀጥተኛ ያልሆነ (ኢርቱዕ) ግንኙነት በመባል ይታወቃሉ ። ርቱዕ ግንኙነት በስብሰባ ፣ በገለጻ ፣ በውይይት የሚደረግ ግንኙነት ሲሆን ፣ የተደራሲው ስፋት ከኢርቱዕ ግንኙነት ጠበብ ያለ ነው ። ይህ የግንኙነት ደረጃ ብዙውን ጊዜ «ዝቅተኛ ደረጃ ትርዕ» በመባል ቢታወቅም ፣ ውጤታማነቱ ከፍተኛ ነው ። የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት በቤተሰብ ፣ በጓደኛሞች ፣ በሥራ ባልደረቦች ፣ በት/ቤት ፣ በአጠቃላይ ቁጥሩ በአንፃራዊ ደረጃ አነስተኛ በሆነ ቡድን ውስጥ ዕለት በዕለት በግንባር የሚካሄድ ግንኙነት በመሆኑ የሰውን መንፈሳዊ ሕይወት በመገራት ረገድ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ። ግንባር ለግንባር ተገናኝቶ ሐሳብን መለዋወጥ ፣ መጠያየቅና መወያየት መልእክትን በትክክል የማስተላለፊያ ዓይነተኛ መንገድ ነው ። «ከግል ግንኙነትና ልብ ከልብ ተዋውቆ ከመወያየት የበለጠ የሰውን ስሜት ለመሳብ የሚያስችል አቋራጭ የለም ።» [6]

ሁለተኛው ደረጃ ማለትም ኢርቱዕ ግንኙነት ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው ሰዎች ፣ መደቦች ወይም ማኅበራዊ ክፍሎች መካከል የሚደረግ ኅሊናዊ ግንኙነት ነው ። የዚህ ዓይነቱን ግንኙነት በግንባር ማካሄድ ስለማይቻል አማካይ ዘዴዎች ወይም አገናኝ መገልገያዎች በግድ አስፈላጊ ይሆናሉ ። በመሆኑም መገናኛ ብዙኃን (ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ጋዜጣ ፣ መጽሔት ፣ መጻሕፍት ፣ ወዘተ .) ጥቅም ላይ ይውላሉ ። ይህ የግንኙነት ዘዴ እንደርቱዕ ግንኙነት የፕሮፓጋንዳውን ውጤታማነት ወዲያውኑ ለመገምገም የሚያስችል ባለመሆኑ የፕሮፓጋንዳ ሠራተኛውን ከፍተኛ ጥረትና ክትትል የሚጠይቅ ነው ። ለዚህ ዓይነቱ ግንኙነት የሚያገለግሉት መገልገያዎች በጥቅሉ የኢርቱዕ ግንኙነት ዘዴዎች ቢሆኑም በአንድ በተወሰነ ወቅትና ቦታ ሁሉም በእኩል ደረጃ ውጤት ሊያስገኙ አይችሉም ። እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ አንዱ የመገናኛ ዘዴ በአንድ ወቅት የበለጠ ውጤታማ የታሰበውን ግብ ለመምታት የሚያስችል ሊሆን ይችላል ። በመሆኑም መልእክት አስተላላፊው ክፍል የተለያዩ-የመገናኛ ዘዴዎችን ምርጭት ፣ ፕሮፓጋንዳው የሚያተኩርበትን የኅብረተሰብ ክፍል በሙሉ ወይም በአመዛኙ ለመድረስ የሚያስችለውን የመገናኛ ዘዴ ፣ የኅብረተሰቡን የንቃተ ኅሊና ደረጃ ፣ የማንበብና የመጻፍ

Digitized by Google

ባህል ወዘተ· በሚገባ ገምግሞ የፕሮፓጋንዳውን ይዘትና የሚተላለፍበትን ዘዴ መቀየስ፣ በየጊዜውም ፕሮፓጋንዳው የሚያተኩርበትን ክፍል አስተያየትና ስሜት በመከታተል (ብዙውን ጊዜ በሚደርሱ ደብዳቤዎች) የፕሮፓጋንዳውን ውጤታማነት መገምገም ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን የሚተላለፈው መልእክት በትክክል ደርሶ የተደራሲውን ስሜት መሳብ ወይም አለመሳቡን ማወቅ ስለማይቻል የፕሮፓጋንዳውን ቅርፅና አቀራረብ ለማሻሻልና የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ አይቻልም።

ከዚህ በመነሣት በዚህ የግንኙነት ሂደት ውስጥ እርስ በርስ የሚተሳሰሩ አምስት መሠረታዊ ክፍሎች እንዳሉ እንገነዘባለን። እነዚህም ፡—

1. የፕሮፓጋንዳውን ይዘት ፣ ቅርፅና አቀራረብ የሚወስነው መልእክት አስተላላፊ ክፍል ማለትም የፕሮፓጋንዳው ባለቤት (ፓርቲ ፣ መንግሥት ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች ፣ ወዘተ.)
2. በግንኙነቱ ሂደት ውስጥ መሠረት የሆነው ከፕሮፓጋንዳው ባለቤት ወደ ኅብረተሰቡ የሚተላለፈው መልእክት፣
3. መልእክቱን ለታሰበው ክፍል ለማድረስ የሚያስችለው ትክክለኛው የመገናኛ ዘዴ (ሬዲዮ ፣ ቴሌቪዥን ፣ ጋዜጣ ሲኒማ ፣ ወዘተ.)
4. መልእክቱ የሚተላለፍለት መደብ ወይም የኅብረተሰብ ክፍል ፣ (ሠራተኛ ፣ ገበሬ ፣ ወጣት ፣ ሴት . . .)
5. በግንኙነቱ ማ ለ ትም ከመልእክቱ የተ-ገኘው ውጤት ወይም ምላሽ ናቸው ።

እነዚህ አምስት ክፍሎች በፕሮፓጋንዳ ሥራ ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው ናቸው። በኢርቱዕ ግንኙነት መልእክት አስተላላፊው የተደራሲውን ስሜትና አስተያየት ማለትም የፕሮፓጋንዳውን ውጤታማነት በግንባር ለማየት ወይም ለመስማት ስለማይችል የመልእክቱን ውጤት ወይም የፕሮፓጋንዳውን ምላሽ መከታተል ከፍተኛና ተቀዳሚ ተግባሩ ነው ።

ፕሮፓጋንዳ ሐሳብን ወደቁሳዊ ኃይል መለወጫ ነው የሚባለው ፕሮፓጋንዳው ውጤታማ ሲሆን ብቻ ነው ። የፕሮፓጋንዳ ውጤትም የፕሮፓጋንዳ ሠራተኛው መልእክቱን ሲያስተላልፍ ሊያገኝ ያሰበው ውጤትና በተግባራዊ እንቅስቃሴ የተገኘው ውጤት መጣጣም ወይም ጥምረት ነው ። ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ውጤታማ ነው የምንለው የሠፊው አደፋን ሕዝብ ስሜት በመቀስቀስና የመደብ ንቃቱንና ርዕዮተ ዓለማዊ ብቃቱን በማጎልበት በአብዮታዊው ትግል ውስጥ በንቃት እንዲሳተፍ ሲያደርግ ነው ። እንዲህ ለማድረግ ደግሞ በሕዝቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት ማለትም በተጨባጩ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ሊጨበጥ የሚችለውን የኅብረተሰብ ዕድገት ሊያመለክት ይገባል ። ከተጨባጩ ሁኔታ የተፋታ ፣ በሕዝቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ ተመርኩዞ የነገውን ሊጨበጥ የሚችል ብሩህ ዓለም የማያመለክት ፕሮፓጋንዳ ውጤታማ ሊሆን አይችልም።

ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ሳይንሳዊ አመለካከትን የማስፈን ፣ እውነታን ለማዛባት የሚፈጸም ድርጊትን የመታገል ፣ በሕዝቡ አእምሮ ውስጥ ሳይንሳዊ ንጽረተ ዓለም የመቅረጽ ሂደት በመሆኑ ውስብስብና እጅግ አስቸጋሪ ተግባር ነው ። ይሁንና በሳይንሳዊ መርህ ላይ በመመርኮዝ የሚከናወን እስከሆነ ድረስ በሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነቱ የማያጠያይቅ ፣ ሊገደብ የማይችልና የተግባርን ፈተና እያለፈ የሚስፋፋ ነው ።

የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

1. V. Kortunov The Battle of Ideas in the Modern World, (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 16.
2. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 5, p. 409.
3. *Ibid.*, p. 401.
4. *Ibid.*, Vol. 1. p. 14.
5. Social Psychology And Propaganda, (Moscow: Progress Publishers, 1983). (ያልታተመ)
6. Party Construction Textbook, (Addis Ababa: Kuraz Publishing Agency, 1983), p. 191.

Digitized by Google

የሶሻሊስት ፔዳጎጂ ሚና

ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

ሰዎች መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን በዓይነትም ሆነ በመጠን አሟልተው ለማግኘት ፣ በተፈጥሮ ላይ የበላይነትን ለመጎናጸፍ መሥራትና ማምረት እንዳለባቸው የታወቀ ነው ። በማምረት ሂደትም አዳዲስ የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች እየተፈጠሩ ፣ የኋላቀር ሥርዓተ ማኅበር ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መሠረቶች ደግሞ እየከሰሙ ይሄዳሉ ። ዛሬ የሰው ልጅ ዕድገት ሂደት የሶሻሊዝም ሀልውና ለተረጋገጠበት ዘመን በቅቷል ። በዚህ መሠረት ሶሻሊዝም በተመሠረተባቸው አገሮች የሰው በሰው መበዝበዝ እየተወገደ የሠራተኛውን ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል ። ለዚህ ዓይነቱ ወደላቀ የኑሮ ደረጃ መሸጋገር ትምህርት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው ።

ትምህርት የሰው ልጅ ካለማወቅ ወደማወቅ ፣ ከኋላቀርነት ወደተሻለ ኑሮ እንዲሸጋገር አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሯል ። ትምህርት ማኅበራዊና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎችን በትክክል ለመገንዘብ ፣ ሥራን ለመውደድና በራስ ለመተማመን ያስችላል ። ዕውቀት ያለው የበለጠ ይጠቀማል ። ማወቅ በተሻለ የሕይወት ጉዳና ለመራመድ ያስችላል ። የተማረና አስተማማኝ ዕውቀት ያለው የሰው ኃይል ባለቤት የሆነች አገር የታደለች ናት ። የተማረ ሕዝብ ከሥራ የሚገኘውን ጥቅም ስለሚያውቅ ለሥራ ከበሬታ ይኖረዋል ። ሰው በአካባቢው የሚገኘውን ማንኛውንም ክስተት ማስተዋል ፣ መመርመር ፣ መረዳትና ሁኔታዎችም ለህልውናው እንዲመቹ ማድረግ የተፈጥሮ ግዴታው ነው ። ከዚሁ አኳያ በሚያደርገው እንቅስቃሴም ዕውቀት ያገኛል ። በዚህ ዓይነት ዘዴና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተካበተው ልምድና የተገኘው ዕውቀት የበለጠ እየዳበረ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል ። በዚህ ዓይነት ጠቃሚ ልምዶችን የማካበቱና የማስተላለፉ ተግባር እንደኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ የሚከናወን ሲሆን ከቃል እስከ ሥነ ጽሑፍ ቅንብር

Digitized by Google

ድረስ ያሉትን የማስተላለፊያ ዘዴዎች ያጠቃልላል ። ይህ የዕውቀትና የልምድ ግኝቶችን (ትምህርትን) የማስተላለፉ ተግባር ወይም ማስተማር ፣ አስተላላፊውን መምህርና የሚተላለፈውን ተቀባይ የሆነውን ተማሪ ያጠቃልላል ።

የማስተማር መማር ክንውን በዳበረ መልኩ የሚካሄደው በትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው ። ይሁን እንጂ የትምህርት ምንጭ ትምህርት ቤት ብቻ እንደሆነ አድርጎ መውሰድ ስሕተት ነው ። ትምህርት ከቤተሰብና ከኅብረተሰብም ይገኛልና ። ከቤተሰብና ከኅብረተሰብ የሚገኘው ትምህርት ከትምህርት ቤት ከሚገኘው ትምህርት ተነጥሎ የሚታይ ሳይሆን ጐን ለጐን አብረው የሚሄዱና በሥርዓት መዋሐድ ያለባቸው ናቸው ። የአንድ ግለሰብ ትምህርት ማግኛ ሥፍራ መጀመሪያ ቤተሰቡ ሲሆን በአካሉና በአእምሮው እየጐለመሰ ከሄደ በኋላ ከኅብረተሰቡና ከትምህርት ቤትም ነው ።

ኅብረተሰቡ ወጐቹና ልማዶቹ በያንዳንዱ የኅብረተሰቡ አባል አእምሮ ው ስ ጥ እንዲሠርጹና እንዲጠበቁለት ይሻል ። ተቀባዩም ትውልድ ለአያሌ ዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረውን ወግና ልማድ ለራሱ እንደሚያመች አድርጎ ይጠቀምባቸዋል ። ከዚህ አንጻር ሁለት የማይነጣጠሉ ሂደቶች ይከናወናሉ ። አንደኛው የግለሰቡ በአካልና በአእምሮ ማደግ ሲሆን ሌላው ግለሰቡ በአካባቢው ወግና ልማድ መሠረት ራሱን ማስተካከሉ ነው ። እነዚህ በማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነት ዕድገት ወቅት የማይነጣጠሉ ሂደቶች ናቸው ። የተጣጣሙ እንዲሆኑና የማስተማር ተግባር የሚፈለገውን ውጤት እንዲያስገኝ ለማድረግም ፔዳጐጂ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ።

ፔዳጐጂ ምንድነው ?

ፔዳጐጂ « ፔዳጐገስ » (Paedagogus) ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ነው ። ትርጉሙም በጥንት ግሪክና ሮም የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ለትምህርት የደረሱ የገዥ መደብ አባላት ልጆችን በመንከባከብ ወደ ትምህርት መስጫ ሥፍራ አድርሰው የሚመልሱ ባሮች ማለት ነበር ።[1] በመካከለኛው ዘመን ይህ ትርጉም ተለውጦ «ፔዳጐገም» (Paedagogium) በመባል ለሚታወቀው የትምህርት መስጫ ተቋም መጠሪያ ሆነ ። በዚሁ ዘመን ፔዳጐገም በትምህርት መስጫ ተቋምነቱ በግሪክና በሮም የአእምሮ እነፃ (መገንቢያ) ማዕከል በመሆን አገልግሏል ። በነዚህ አገሮች ትምህርት የሚሰጠው በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች ላይ ብቻ ሲሆን ፣ የትኩረት መስኮችም ሰዋስው ፣ ሎጂክ ፣ ንግግር ፣ ሒሳብ ጂኦሜትሪ፣ሙዚቃና ሥነ ከዋክብት ነበሩ ።[2] እነዚህን የትምህርት ዓይነቶች ለመማር የሚችሉትም የገዥ መደብ አባላት ነበሩ ።

ፔዳጐገም እያደር የተለያዩ ትርጉሞችን በመያዝ በመካከለኛው ዘመን ማብቂያ አካባቢ በምዕራባዊና ማዕከላዊ አውሮፓ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ማዘጋጃ ትምህርት ቤት ፣ በኋላም ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ማዘጋጃ እንዲሁም በአንዳንድ አገሮች የሰዋስው ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን የሚሠለጥኑበትን ተቋም የሚመለከት ሆነ ።[3]

ዛሬ ፔዳጐጂ የሰውን ልጅ በተቀነባበረ ግብና ሥርዓት ባለው ሁኔታ የማነጽ ሳይንስ ነው ። ዘርዘር ብሎም ሲታይ «ፔዳጐጂ የሰውን ልጅ ትንብር ፣ ዓላማና ሥርዓት ባለው መንገድ የማነጽ ሳይንስ ነው ። ፔዳጐጂ ወጣቶችን የመኰትኰት ፣ የማስተማርና የማሠልጠን ይዘት ፣ ስልትና ዘዴ ሳይንስ ነው ። »[4]

በተለይ ሶሻሊስት ፔዳጐጂ ደግሞ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ንጽረተዓለም (world outlook) ላይ የተመሠረተ ፣ ግብ ያለውና በዕቅድ የሚመራ የማስተማርና የማሠልጠን ሳይንስ ነው ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ፔዳጐጂ ሲባል ይህንን ሳይንስ ለማመልከት ነው ።

Digitized by Google

የፔዳጐጂ ሳይንስ ዓላማዎች ፣ መርሆዎች፣ ደንቦችና ንድፈሐሳቦች እንደየሥርዓተ ማኅበሩ የሚለያዩና በየሥርዓተ ማኅበሩ ነባራዊ ሁኔታዎች የሚወሰኑ ናቸው ። ፔዳጐጂ ሙሉ ሰብእና ያለውን የዳበረ አምራች ሰው ለመፍጠር መቻሉ የሚረጋገጠው በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ነው ። ዓላማውና ተግባሩም ለወዛደሩ መደብ የበላይ ገዥነት መስፈን ብሎም ለመደብ የለሽ ኅብረተሰብ ምሥረታ ማገዝ ነው ። ስለሆነም የፔዳጐጂ ማኅበራዊ አገልግሎት ወይም ተግባር ፣ ይዘቱና ባሕርዩ ከታሪካዊ የኅብረተሰብ ዕድገት ጋር የሚለዋወጥ ፣ በቁሳዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች ፣ በመደቦችና ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል ሕግጋት የሚገዛ ነው።ለብዙ ዘመናት በዝባዥ የገዥ መደብ አባላት በትምህርት ላይ የበላይነትን በመያዝ የፔዳጐጂ ፖሊሲያቸውን በጥቅማቸው አንጻር በመቀየስ ፣ ለተበዝባዥ መደቦች ዝቅተኛ ትምህርት በመስጠት ማኅበራዊ ዕድገትን አጓተዋል ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ የፔዳጐጂ ፖሊሲ መደባዊ ባሕርይ ስላለው በአንድ አገር የፖለቲካ ሥልጣን የያዘው የገዥ መደብ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መሠረት አቋም እንዲያንፀባርቅ ተደርጎ ይነደፋል ። የፔዳጐጂ ፖሊሲ የሥርዓተ ማኅበሩ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ነፀብራቅ በመሆኑ ይዘቱ ካለው የገዥ መደብ ርዕዮተዓለም ጋር የግድ መጣጣም አለበት ።

ፔዳጐጂን ከተገዥው መደብ ፍላጎት አኳያ ማካሄድ የተጀመረው በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ነው ። የዓላማው ፣ የይዘቱና የመከትከቱ ዘዴው ተጠቃሚ የባሪያ አሳዳሪው መደብ አባላት ነበሩ ። የዚያ ሥርዓተ ማኅበር ፈላስፎች ፣ ገጣሚዎችና የሥነ ጽሑፍ ምሁራን የግሪክ ከተማ ነፃ ነዋሪዎች (ዜጎች) በአካልና በአእምሮ እንዲጐለምሱ አጥብቀው ጥረዋል ። የግሪክ ነፃ ዜጋ ጠንካራና ደፋር ጦረኛ ፣ በአካሉ የዳበረና የተማረ መሆን ነበረበት ። ይህም በወቅቱ ሙሉ ሰብእና ያለውን ሰው መፍጠር ማለት ነበር ። የባሪያ አሳዳሪው መደብ የራሱ መደብ ትውልድ ጠንካራ ምሁር እንዲሆን ፣ በአእምሮው እንዲዳብር ባደረገው ጥረት ፔዳጐጂ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ትምህርቱን መማር የሚችሉት የገዥው መደብ አባላት ብቻ እንጂ ባሮች አልተፈቀደላቸውም ። በባሪያ አሳዳሪው ፖለቲካ አራማጅ ፈላስፎችና ገጣሚዎች ባሮች ሙሉ ሰብእና እንደሌላቸው ተደርገው ስለሚታዩ «ተናጋሪ ዕቃ» የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል ። በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ፔዳጐጂ ባሮች ከባርነት ለመውጣት የማይችሉና በባርነት መገዛት፣ተጨቁነውና ተበዝብዘው መኖር «ዕጣቸው» ነው የሚል ትምህርት አስፋፍቷል ። በዚህ ሥርዓት ፔዳጐጂ እንጭጭ የነበረ ቢሆንም ለባሪያ አሳዳሪው መደብ ጥቅም መጠበቅ ጠንካራ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

በፊውዳሉ ሥርዓተ ማኅበርም የሃይማኖት ማስፋፊያ ድርጅቶች ጭቁኖች በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የመደብ ቅራኔ ወይም ግጭት እንዳይረዱና ለነፃነታቸው እንዳይታገሉ ፣ የሚደርስባቸውን ማንኛውንም መከራና ሥቃይ እንደ «ጸጋ» እንዲቀበሉ በማድረግ አመለካከታቸውን በማስተማር ስም አዛብተውባቸዋል ።

በመካከለኛው ዘመን በአውሮፓ ፔዳጐጂ በእምነት ተከታዮች ቁጥጥር ሥር በመሆን ለፊውዳል ገዥ መደብ ማገልገልና የሰውን አስተሳሰብና ምግባር በሃይማኖት ተጽዕኖ ሥር ማድረጊያ መሣሪያ ሆነ ። እያደርም በሌሎች የዓለም ክፍሎች ለነበሩ (እንደ እስልምናና ቡድሃ) እምነቶች ማስፋፊያ መሣሪያ በመሆን አገልግሏል ።

የፊውዳሊዝም ሥርዓት እየፈራረሰና የቡርዧው ሥርዓት እየተስፋፋ ሲመጣ ስለ ፔዳጐጂ የነበረው አመለካከት እየተለወጠ መጣ ። በ17ኛው ምዕት ዓመት የተሻለ አስተሳሰብ የነበራቸው ምሁራን የተሟላ ሰብ

Digitized by Google

እና ያለውን ሰው ለመፍጠር ያስችላል የሚሉትን የትምህርት ዘዴ መቀየስ ጀመሩ ። ከተጨባጩ ሁኔታ ከራቀውና ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ከማይጥረው ከፊውዳላዊ ትምህርት ይልቅ ማኅበራዊ ችግሮችን የሚያብራራና መፍትሔ የሚጠቁም ትምህርት እንዲሰጥ ግፊት አድርገዋል ።

ከዚህም አንፃር ሁለት መሠረታዊ የፔዳጐጂ አስተሳሰብ አዝማሚያዎች ሊከሰቱ ችለዋል ። አንደኛው አዝማሚያ በሃይማኖታዊ ተጽዕኖ የተገነባው የፊውዳሉ ፔዳጐጂ የራሱን ዕድሜ ለማራዘም የሚያካሂደው ትግል ሲሆን ፣ ሁለተኛው አዲስና ከፊውዳሉ የተሻለ ሆኖ የተገኘው የቡርዧ ፔዳጐጂ አስተሳሰብ ነበር ።

የቡርዧ ፔዳጐጂ የተሟላ ሰብእና ያለውን ሰው ሳይሆን የቡርዧ ሰብእና ያለውን ዜጋ በማነጽ ላይ የሚያተኩር ፣ እውነትን በተሟላ መልክ የማያስጨብጥና ከኋላቀር አመለካከት ያልጸዳ ነው ። የቡርዧ ፔዳጐጂ ንድፈሐሳቦች የትክክለኛውን ፔዳጐጂ ሳይንሳዊ መርህ በማጣመም ለቡርዧ ሥርዓት ታማኝና አገልጋይ ግለሰቦችን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ የርዕዮተዓለም መግሪያዎች ናቸው ። በይዘታቸውም የቡርዧውን የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና ማኅበራዊ ቀውስ መሠረታዊ መንሥኤ በማድበስበስና የሠራተኛውን መደብ ትግል ትክክለኛ አቅጣጫ በማጣመም ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ባለንበት ዘመን የቡርዧው ፔዳጐጂ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የትምህርት ፖሊሲን ፣ በሶሻሊስት አገሮች የሚሰጠውን ሶሻሊስት ፔዳጐጂን የሚቃረንና የሞኖፖል ካፒታሊዝምን የፔዳጐጂ ፖሊሲ የሚያስፋፋ ነው ። የሶሻሊስት አገሮች የትምህርት ፖሊሲ ማኅበራዊ ተቀባይነትን ማግኘትና ሙሉ ሰብእና ያለው ዜጋ ለመፍጠር መቻል የቡርዧውን ፔዳጐጂ መሠረት አናግቶታል ። ዛሬ የቡርዧ ፔዳጐጂ በቀውስ የተወጠረውን የካፒታሊስት ሥርዓት ዕድሜ ለማራዘም በሚያካሂደው ትግል ወጣቶች በካፒታሊስት ማኅበራዊ ሥርዓት እምነት እንዲኖራቸው ፣ ለሥርዓቱ ታማኝ እንዲሆኑና ሶሻሊዝምን እንዲጠሉ ለማድረግ ይጥራል ። የካፒታሊስቱ ሥርዓት የሚመራበት ፔዳጐጂ ወጣቱን ትውልድ ለእውነተኛ ነፃነት ከሚካሄድ የመደብ ትግል እንዲገለል ፣ ራሱን ወዳድ እንዲሆንና በግላዊ ችግር ላይ ብቻ እንዲያተኩር የሚያደርግ ነው ።

ሌላው የቡርዧ ፔዳጐጂ ተግባር ሶሻሊዝምን ለመዋጋት አዳዲስ ስልቶችን በመቀየስ የሰውን አመለካከት ማዛባትና ውዥንብር ውስጥ መክተት ነው ። ዛሬ የቡርዧ ፔዳጐጂ አራማጆች ከነደፏቸው ንድፈሐሳባዊ ስልቶች መካከል «የውሕደት» ንድፈሐሳብ Convergence theory የሚባለው በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው ። «የውሕደት ንድፈሐሳብ» ካፒታሊዝምና ሶሻሊዝም ማንኛውም ማኅበራዊ መሠረት ሳይለያቸው እያደር የጋራ ባሕርያት ይኖራቸዋል የሚለውን የቡርዧውን ዓላማ የሚያስተጋባ ነው ። በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል ያሉት ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ልዩነቶች ለወደፊቱ ቀስ በቀስ የሚወገዱ ናቸው በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው ። ይህ «ንድፈሐሳብ» ትምህርት ከማናቸውም «መደቦችና የመደቦች ትግል በላይ ነው ፤» «ነፃ ትምህርት ለዓለም ሕፃናት ከተሰጠ ከካፒታሊዝምና ከሶሻሊዝም በላይ የሆነ» «የተዋሐደ የዓለም ማኅበረሰብ»(Unitary world Community) እንዲፈጠር ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ምሁራንን ያስገኛል [5] የሚሉና መሰል የተሳሳቱ አመለካከቶችን ያስፋፋል ።

የቡርዧ ፔዳጐጂ አራማጆች ኢሳይንሳዊ አስተሳሰብ ካፒታሊዝም በቅርዕ ብቻ ተለውጦ በዘለዓለማዊነት እንዲቀጥል ያላቸውን ምኞት ይጠቁማል ። «የውሕደት ንድፈሐሳብ» በዩናይትድ ስቴትስና በምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊስት መንግሥታት አግካይነት በመስፋፋት ላይ ሲሆን መሠረታዊ ተልዕኮውም ውዥንብር መፍጠርና ሙሉ ሰብእናን ለመቅረጽ በሳይንሳዊ አመራር

Digitized by Google

የተደራጀውን የሶሻሊስቱን ፔዳጎጂያዊ አሠራር ማጥላላት ነው ።

በካፒታሊስት ሀገሮች የቡርዧውን መደብ ጥቅም የሚጠብቁ ትላልቅ የትምህርት ተቋ ሞች በቡርዧ ፔዳጎጂ ላይ የሚሠማሩ ግለ ሰቦችን በብዛት ያሠለጥናሉ ። ስትራተጂያዊ ዓላማቸውም ወጣቱ ትውልድ ለሞና ፖል ቡርዧው ተገዥ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን ፣ ከነዚህ ተቋሞች መካከል ዛሬ በፌዴራል ጀርመን የዋልተር ሬይሞንድ ድርጅት (Walter Raymond Foundation) በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው ።[6]

ሶሻሊስት ፔዳጎጂ

የሶሻሊስት ፔዳጎጂ ጽንሰ ሐሳብ የሰውን አስተዳደግ ከሶሻሊስት ሰብእና መፈጠር ጋር የሚያዋሕድ ፣ ምርምራዊ አስተሳሰቡ የዳበረ ዜጋን በመፍጠር ላይ ያተከረ ነው። በትምህርት ሂደትም ውስጥ አስተያየትን ፣ ሞራልንና ባሕርያትን የሚያንጽ ነው ።

ሶሻሊስት ፔዳጎጂ በማርክሳዊ ሌኒናዊ መርህ ላይ የተመሠረተ ፣ በዓላማው ፣ በይዘቱም ሆነ በማስተማር ዘዴው በአስገዳጅነት ተጽዕኖ (ሥነ ልቦናዊ ተጽዕኖ) የማይፈጥር ፣ በዘር ፣ በጾታ ፣ በሃይማኖትና በቀለም ልዩነት የማያምን ሥርተአደርችን ሁሉ በእኩልነት የሚያገለግል ነው ። ሶሻሊስት ፔዳጎጂ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብን መመሪያው ያደረገ ፣ ግልጽ በሆነ ዕቅድ ላይ በመመሥረት የማስተማርና የማሠልጠን ተልዕኮን የሚያራምድ ነው ። ዓላማውም በአዲስ የኅብረተሰብ ግንባታ መስክ በፖለቲካዊ ፣ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ብቁና ሁለንተናዊ ሰብእናቸው የተሟላ ዜጎችን መፍጠር ነው ።

ሶሻሊስት ፔዳጎጂ ጽንሰሐሳቦችን ፣ ደንቦችን ፣ ሕግጋትን ፣ የትምህርት ዓላማና ይዘቶችን ፣ የመማር ዘዴዎችን ፣ የቁጥጥርን፣የግምገማንና የመሳሰሉትን ተግባራት ያካትታል።በተግባራዊነቱ በማስተማር ሥራ ላይ የተሠማራው መምህር የሙያ ግዴታውን በብቃት እንዲወጣውና አጥጋቢ ው ጤ ት እንዲያገኝ ይረዳዋል ። ሶሻሊስት ፔዳጎጂ መምህራን የትምህርት ዓላማዎችና ይዘቶች እንዳደፍን ፣ የመማር ዘዴና የትምህርት መረጃ መግሪያዎች አዘገጃጀትንና አጠቃቀምን ፣ የቁጥጥርና የግምገማ ዘዴዎች አመራረጥንና አቀነባበርን እንዲያገናዝቡና እንዲጨብጡ ይረዳቸዋል ። በአጠቃላይ መምህራን በሙያቸው የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲችሉ መመሪያ በመሆን ያገለግላቸዋል ።

ሶሻሊስት ፔዳጎጂን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አራት ዋና ዋና የጥናት ዘርፎች አሉ ። እነርሱም 1/ የሶሻሊስት ፔዳጎጂ መሠረቶች ፣ 2/ የመማር ንድፈሐሳብ ፣ 3/ የትምህርት ታሪክ ፣ 4/ የሶሻሊስት ትምህርት ንድፈሐሳብ [7] ናቸው ።

የሶሻሊስት ፔዳጎጂ መሠረቶች የተሰኘው የጥናት ዘርፍ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና ላይ በመመሥረት በፔዳጎጂ ዘርፎች በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰቱ የንድፈ ሐሳብና የዘዴዎችን ችግር ይመረምራል ፤ ይተነትናል ። ይህ የጥናት መስክ ለአጠቃላይ የፔዳጎጂ ትምህርትና ሥልጠናዎች መሠረት ነው ።

የመማር ንድፈሐሳብ በተለይ በመምህርነት ሙያ ላይ ማለትም በትምህርት ዓላማዎች ፣ ይዘቶች ፣ የመማር ዘዴዎች ፣ የትምህርት መረጃ መግሪያዎች ፣ የቁጥጥርና የግምገማ ዘዴዎች በአመራረጣቸው ፣ በአቀራረባቸው ፣ በዝግጅታቸውና በአጠቃቀማቸው ላይ አስፈላጊውን ሥልጠናና ትምህርት የሚሰጥ ወይም የሚተነትን የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ነው ። [8]

የትምህርት ታሪክ በሶሻሊስት ፔዳጎጂ ዘርፍነቱ በትምህርት መስክ የተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች ያሳዩትን ንፈድሐሳባዊ ዕድገትና ይህንኑ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ያሳዩትንና የሚያሳዩትን ባሕርይ ይመረምራል ። ይህ የትምህርት መስክ ከጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር እንሥቶ በባሪያ አሳዳሪ ፣ በፊውዳል ፣ በካፒታሊስቱና በኮሚ

Digitized by Google

ኒስቱ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የትምህርትን ቅርጽና ይዘት ይተነትናል ።[9]

ሶሻሊስት የትምህርት ንድፈሐሳብ የትምህርት ሂደትን በተከታታይነት የሚተነትን ፣ ከሶሻሊስት ዓላማዎች ፣ ይዘቶችና የመማር ዘዴዎች አንፃር የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ዝንባሌያቸውንና አጠቃላይ ባሕርያቸውን ለማጉልበት የሚያስችላቸውን ትንታኔ የሚያደርግ ነው ። ይህ የትምህርት መስክ አምስት ዋና አካሎች አሉት ። እነርሱም ፡—

ሀ. የርዕዮተ ዓለም ትምህርት
ለ. የቀለም ትምህርት
ሐ. የፖሊቴክኒክ ትምህርት
መ. የሥነውበት ትምህርት
ሠ. የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት
ናቸው ።

የወዝ አደሮችም ሆነ በአጠቃላይ የዓለም ሠርቶአደሮች ፍላጎቶች የሚሟሉትና ድላቸውም ዋስትና ያሚኖረው ዓለም የሠራተኞች ሆና የሰው ልጆች በሳይንሳዊ አስተሳሰብ የተካኑ ፣ በሥራ የዳበሩ ፣ በዕውቀት የበሰሉ ፣ በስፖርት የጐለመሱ፣ኪነ ጥበብን የሚያጣጥሙና በፈጠራውም የሚሳተፉ ፣ ሳይንሳዊ ርዕዮተዓለምን የተግባር መመሪያ በማድረግ ከግል ጥቅም ይልቅ የኅብረተሰብን ጥቅም የሚያስቀድሙና የሚንከባከቡ ሆነው ሲገኙ ነው ። ሶሻሊስት የትምህርት ይዘትም ሙሉ ሰብእና ያላቸውን ዜጎች በመፍጠር በኩል ከፍተኛ ድርሻ አለው ። የሶሻሊስት ፔዳጐጂ የተለያዩ መስኮች ለተሟላ ሰው እነፃ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ በበለጠ ለመረዳት ዝርዝር አድርገን እንመልከት ።

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ ሂደት ውስጥ የርዕዮተዓለም ትምህርት ለተሟላ ሰብእና ግንባታ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ። ይህ ትምህርት በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የአዲሱን ትውልድም ሆነ በትምህርት ዓለም የሚገኘውን ግለሰብ ወይም ቡድን ጠቅላላ ሰብእና ግለትም የአእምሮ ፣ የአካል፣የሞራል ፣ የርዕዮተ ዓለም እንቅስቃሴውንና ዕድገቱን እንደኅብረተሰቡ ነባራዊ የዕድገት ደረጃ መገንዘብን የሚጠይቅ ነው ።

የርዕዮተዓለም ትምህርት በትምህርት ቤቶችና በትምህርት ተቋሞች እንዲሰጥ የሚደረግበት መሠረታዊ ምክንያት አዲሱ ትውልድ በሶሻሊስት አመለካከት እንዲታነጽ ፣ ንቁና ብቁ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ዜጋ እንዲሆን ፣ በፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሚጠበቅበትን ተግባራዊ ተሳትፎ እንዲያደርግ ለማዘጋጀት ነው ። ዛሬ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ይህ ትምህርት የሚሰጥበት ምክንያት ወጣቱ ትውልድ በሶሻሊስት አመለካከት ታንጾ በማደግ የሚጠበቅበትን ታሪካዊ ድርሻ ሁሉ እንዲያበረክት ለማብቃትነው ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ የማርክሲዝም ሌኒንዝምን ንድፈሐሳብ የታጠቁ ፣ ለመደብ አልባው ሥርዓት በግንባር ቀደምትነት የሚታገሉ ፣ ለሠርቶአደሩ ሕዝብና ከዚያም ለሠራተኛው መደብ የበላይነት የሚቆሙ ዜጎች መሠረታዊ ምንጫቸው ትምህርት ቤቶች መሆናቸውን በመገንዘብ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ትምህርት በሰፊው እንዲሰጥ ልዩ ትኩረት ታደርጋለች ። ይህም ለምንገነባው አዲስ ኅብረተሰብ አመቺና አስተማማኝ መሠረት ይጥላል ። ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓ መሥራች ጉባኤ ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት የትምህርትን ዓላማና የወደፊት አቅጣጫ በሚመለከት እንደሚከተለው ገልጸውታል ።

የሶሻሊስተ ሥርዓተ ግንባታ ተልማችን እውን የሚሆነው በየመስኩ የሚፈለገውን ለውጥ ለማስገኘተ የሚችል ኃይል ሲኖር ብቻ ነው። ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ከአሮጌው ሥርዓተ መንፈሳዊ ተጽዕኖ በማላቀቅ በሳይንሳዊና አብዮታዊ ርዕዮተዓለም ለማነፅ የምናካሂደው የባህል አብዮተ ዓላማም ይህንኑ ኃይል መፍጠር ነው። በዚህ አኳያ የትምህርተ ተቋሞች ሊጫ

Digitized by Google

ወቱ የሚችሉት ሚና ከፍተኛ መሆኑ ገልጽ ነው።

ዛሬ የአገራችን መሠረታዊ ዓላማ ወጣቱን ትውልድ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለም ለማነፅ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ የአዲስ ባህልና የሥነ ጥበብ ዕውቀቶችን ለማዳበር፣ ትምህርትን፣ ምርምርና ምርትን በማቀናጀትና ብማዋሃድ አብዮቱን ለማራመድና አምራች የሆኑ ዜጎችን ለማፍራት ነው ። [10]

የርዕዮተዓለም ትምህርት ወይም በዚህ ውስጥ የሚጠቃለለው የፖለቲካ ትምህርት ወደሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ በሚያመራ አብዮት አኳያ ሰፊው ሕዝብ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሐሳብን በመቅሰም የመደብ ትግሉ ግቡን የሚመታበትን ፣ ርዕዮተዓለሙን ከአብዮቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የሚደራጅበትን ፣ ለሰላምና ለአርነት ትግል በበለጠ የሚዘጋጅበትን አመቺ መድረክ የሚፈጥር ነው ። በሌላ አገላለጽ አብዮታዊ ንቃተ ኅሊና የሚዳብርበት ፣ ሶሻሊስት አርበኝነትና ወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነት የሚጠናከርበት ፣ አዲስና ተራማጅ ኅብረተሰብ የሚገነባበት ነው ።

የርዕዮተዓለም ትምህርት የሠራተኛውን ማኅበራዊ አብዮት ባሕርይና ሂደት በትክክል ለመረዳትና ለመጠናከሩም አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚረዳ ነው ። ይህ ትምህርት የእናት አገር ነፃነትና አንድነት የሚከበርበት ፣ ምርት የሚዳብርበት ፣ አብዮቱን የሚመራው ግንባር ቀደም ፓርቲ ፖሊሲና ለኅብረተሰብ ግንባታ የሚያወጣቸው መርሐ ግብሮች በተግባር የሚተረጐሙበት ፣ ሠራተኛው መደብ ወዳጁንና ጠላቱን የሚለይበትና የአብዮታዊ ት ግ ል ስትራቴጂና ታክቲክ የሚቀይስበት ፣ ፖለቲካዊ አመለካከት የሚሰፍንበትና ሶሻሊስት ወገናዊነት የሚጠናከርበት ነው ።

የፖለቲካ ትምህርት ለሠራተኛው መደብና ለሶሻሊዝም ድል አድራጊነት ግንባር ቀደም አመራር ለሚሰጠው ፓርቲ ዓላማ መሳካት ኅብረተሰቡ የሚያደርገውን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚያስችል ነው ። ከዚህም ሌላ እያንዳንዱ ዜጋ መብትና ግዴታውን ተረድቶ አብዮታዊ ንድፈሐሳብንና ተጨባጭ ሁኔታን በሚገባ እያገናዘበ አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችል ይረዳዋል።

የፖለቲካ ትምህርት በትምህርት ቤቶች እንዲሰጥ ማድረግ ሶሻሊስት ኅብረተሰብን ለመገንባት ወሳኝ ነው ። ይህም ትምህርት ለረጅም ዘመናት በመደበኛነት ሲሰጡ ከነበሩት የትምህርት ዓይነቶች የሚለይና በዓላማውም ለአብዮት ግብ መምታት አዲሱን ትውልድ የተግባር መመሪያ ለማስጨበጥ የሚረዳ አስፈላጊ የትግል መማሪያ ነው ። በአጠቃላይ ለማኅበራዊ አብዮት ግብ መምታትና ለሠራተኛው መደብ የበላይነት ሳይንሳዊ አመለካከትና አስተሳሰብን ይቀርጻል ፤ ያጠናክራልም ። አዲሱ ትውልድ የወደፊት ኃላፊነቱን እንዳይዘነጋ ፣ የእርሱም ሆነ የመጭዎቹ ትውልዶች የተሟላ መብት መጐናፀፍ በአብዮቱ መጠናከርና ግብ መምታት የሚወሰን መሆኑን እንዲገነዘብ ይረዳዋል ።

የፖለቲካ ትምህርት ፣ ተማሪዎች በአገራቸው የሚካሄደውን ፖለቲካዊ ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንባታ በትክክል እንዲገነዘቡ የሚረዳቸው ከመሆኑም ሌላ የሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደም መሪ ፓርቲ የሚሰጠውን መመሪያ እንዲያጤኑና በተግባር እንዲተረጉሙ ሰፊ መስክ ይከፍትላቸዋል ። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ከአገራቸው ማኅበራዊ አብዮት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማስተዋል ያስችላቸዋል ። በአገራቸው ውስጥና ከአገራቸው ውጭ የሚካሄዱት ማኅበራዊ አብዮቶች ወደሶሻሊስት ዲሞክራሲ የሚያመሩና የማይቀሩ የታሪክ ክንውኖች መሆናቸውን ለማወቅ ያስችላቸዋል ። የአብዮቶችን ሂደት ከመገንዘብ ሌላ በኅብረተሰብ ውስጥ የሚታዩትን ክስተቶች፣ ድርጊቶች ፣ ግንኙነቶችና ሂደቶች ከሠራት

Digitized by Google

ኛው መደብ ርዕዮተዓለምና ከአገራቸው
ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር ድርጊቶ
ችን ከቦታ ፣ ከጊዜና ከሁኔታ አንፃር ለመ
ለየት ይረዳቸዋል ። በአጠቃላይ ሶሻሊዝም
ከአሮጌው ሥርዓት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ
መሆኑን ፣ ኢምፔሪያሊዝም መሸነፉና ሶሻ
ሊዝም በድል አድራጊነት መውጣቱ የማይ
ቀር ታሪካዊና ሳይንሳዊ እውነታ መሆኑን ፣
በመገንዘብ ትክክለኛ አቋም እንዲይዙ
ያዘጋጃቸዋል ።

የሶሻሊዝምን የዕድገት ፈር ለመከተል
በመረጡ አገሮች ትምህርት ቤቶች በመን
ግሥትና በሕዝብ ቁጥጥር ሥር ሆነው ከኋላ
ቀር እምነት ማስፋፊያነት እንዲጸዱ ማድ
ረግ አንድ ዓቢይ አብዮታዊ እርምጃ ነው።
በኢሳይንሳዊ አስተሳሰብ የሚመሩ ፣ በራቸ
ውን ለብዙኃኑ ልጆች ዝግ ያደረጉና ከሶ
ሻሊስት ፔዳጎጂ መርህ ውጭ የሚሠሩ
ፀረ ኮሚኒስት ዓላማ ያላቸው ትምህርት
ቤቶች በመንግሥት አመራር ሥር ሳይውሉ
ወጣቱ ትውልድ አንድ ወጥ የትምህርት ዓይ
ነት ይቀስማል ማለት አይቻልም ። ይህን
ሐቅ በመገንዘብ ነው ኢሠፓ በፕሮግራሙ
ውስጥ የሚከተለውን ያሠፈረው ።

ትምህርት አሮጌውንና አድኀሪውን ሥርዓት
በማፈራረስና አዲሱን ሶሻሊስት ሥርዓት
በመገንባት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ እውነተኛ
ነፃነት ማስገኛ አንድ ዋንኛ መሣሪያ እንዲሆን
በኀብረተሰቡ ውስጥ ለዘመናት ሰፍነው ከነ
በሩት ኢሳይንሳዊ አስተሳሰቦችና ከበዝባዥ
መደቦች ርዕዮተዓለማዊ ተጽዕኖ ነፃ ሆኖ ለሁ
ሉም በእኩልነት እንዲዳረስ ትምህርት ቤቶች
ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር
እንዲውሉ ይደረጋል ።[11]

ለዚህ እርምጃ ተግባራዊነት የአብዮታ
ዊት ኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች በአንድ
ወጥ አመራር ሥር በመሆን አዲሱን ትው
ልድ ለማነጽ የሚችሉበት ሁኔታ መሟላቱ
አስፈላጊ ነው ።

ትምህርት ቤቶች በውስጣቸው ከተሠ
ማሩት መምህራን ተለይተው የሚታዩ ካለ
መሆናቸው ሌላ ይልቁንም የመምህራኑ
ሁኔታ ወሳኝነት አለው ። አዲሱን ትው
ልድ ለአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ የሚያዘ
ጋጅ መምህር አጠቃላይ የማስተማር ዘዴው
በሚገባ የተቀነባበረና በራሱ ችሎታ የሚ
ተማመን ፣ በሚያስተምረው ትምህርትሙሉ
እምነት ያለው ፣ ንድፈሐሳብን ከተግባር
ጋር ለማዋሐድ የበቃ መሆን አለበት ። ለማ
ርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ ተግባራዊነት
ግድ የሌለውን መምህር በፖለቲካ መምህ
ርነት ማሠማራት ተማሪውን በማርክሳዊ
ሌኒናዊ ንድፈሐሳብ ላይ ዝቅተኛ ግምት
እንዲኖረው የሚያደርግ ነው ። አዲሱ ትው
ልድ ለወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነት አስተ
ዋጽኦ የሚያደርግ ፣ በአእምሮው የበለፀገና
በአካል የዳበረ ሆኖ ለኮሚኒስት ሥርዓተ
ማኅበር ግንባታ ቁሳዊና ኅሊናዊ ዕድገት
አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚችል እንዲሆን
በቅድሚያ መምህሩ ለዚሁ ዓላማ የቆመ
መሆኑ የማይታለፍ ግዴታ ነው ።

የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ትምህርት ብቻ
ውን የሚቆም ሳይሆን ከሌሎችም የትምህ
ርት ዓይነቶች ጋር የተሳሰረ በመሆኑ አቀ
ራረቡም ከዚሁ በመነሣት መሆን ይኖርበ
ታል ። ትምህርት ቤትም የኅብረተሰቡ የዕ
ድገት ደረጃ የደረሰበትን የማኅበራዊ ፣ የኢ
ኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የባህል ዕድገት አቅ
ጣጫ መሠረት አድርጎ ተማሪውን ከዚሁ
አኳያ የሚያሠለጥን መሆን አለበት ። በአ
ጠቃላይ ትምህርት ለምርምር ፣ ለምርት ፣
ለንቃተ ኅሊና መጐልበት መሠረት እንደ
መሆኑ ልዩ ትኩረት ያሻዋል ። የተግባር
መመሪያነቱንም ለማረጋገጥ የሥራ ትምህ
ርትን (Labour Education) ተግባራዊ
ማድረግ ፣ ንድፈሐሳብንና ተግባርን ማቀ
ናጀት አንደኛው ተልዕኮው መሆን አለ

Digitized by Google

በት ። ንድፈሐሳብ መምህሩ ከሚሰጠው የትምህርት ይዘት የሚገኝ ሲሆን ተግባር ደግሞ ተማሪው ከሚያደርገው እንቅስቃሴ የሚገኝ ነው ። 12

የሥራ ትምህርት ተማሪው ንድፈሐሳብን በተግባር ለማስፈን የሚረዳው ከመሆኑም ሌላ ስለሥራ ወሳኝ ሚና የበለጠ ለመገንዘብ እንዲችል የሚረዳው ነው።ሶሻሊስት የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች አዲሱ ትውልድ ስለሥራ ምንነት በሚገባ እንዲገነዘብ የፖሊቴክኒክ ትምህርት ከመደበኛ ትምህርት ጋር ተጣምሮ እንዲሰጥ ያደርጋሉ ። ይህም የፖሊቴክኒክ ትምህርት አዲሱ ትውልድ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር ተዋውቆ ችሎታውን አዳብሮ ተግባራዊ እንዲያደርግ ይረዳዋል ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት መሠረታዊ ዓላማ ወጣቱን ትውልድ ለውጤታማ ሥራ ለማሠልጠን የሥራን ባህልና ልምድ ለማዳበር ፣ ተማሪውን ከሙያ (ከተግባረ እድ ሙያ) ጋር ማስተዋወቅ ነው ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ጽንሰ ሐሳብ መሠረት የተጣለው በካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ነው ። እነርሱም በትምህርት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የፖሊቴክኒክ ትምህርትን ከምርታማ ተግባር ጋር ማዋሐድ ግለሰቡ በተፈጥሮ ላይ የበላይነትን እንዲጐናፀፍ ፣ ይህም ድል ሙሉ ሰብእና ፣ በአካልና በአእምሮ የዳበረውን ሶሻሊስት ሰው ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን አስገንዝበዋል ። 13

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሥልጠና ትኩረት አንድን ግለሰብ በተወሰነ የሙያ ዘለላ ብቻ አሠልጥኖ የሥርዓቱ ጠበቃ እንዲሆን ማድረግ በመሆኑ ለፖሊቴክኒክ ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው ። ይህም ሲባል አንድን ግለሰብ በተወሰነ ሙያ ማሠልጠን የሶሻሊዝም ዓላማ አይደለም ለማለት አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። በሶሻሊስት ኅብረተሰብ አንድ ግለሰብ ከፍተኛ የሙያ ሥልጠና ከማግኘቱ በፊት የፖሊቴክኒክ ዕውቀትን እንዲማር ይጠበቅበታል ። ለአጠቃላይ ግንባታ ጠቅላላ ዕውቀት መሠረት ነውና ።

ከማርክስና ከኤንግልስ በኋላም ሌኒን የፖሊቴክኒክ ትምህርት በሶቭዬት ኅብረት እንዲዳብር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል። ሌኒን ወጣቱን ትውልድ የኮሚኒዝምን ንድፈሐሳብ ለማስተማርም ሆነ የኮሙኒስት ዜጋን ለመፍጠር የፖሊቴክኒክ ትምህርት ቤቶች ዋንኛ ማዕከላት መሆናቸውን ፣ ከአካልና ከአእምሮ ሥልጠና ጋር በመያያዛቸው ለአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታና ለሠራተኛው መደብ የበላይ ገዥነት መሠረት የሚጥሉ መሆናቸውን አስገንዝቧል ።

ወዛደሩ በበላይ ገዢነት ዘመኑ ትምህርት ቤቶች መደብ አልባውን ሥርዓተ ማኅበር ለመመሥረት የሚችሉ ዜጎችን በማሠልጠንና የኮሚኒስት መርሆዎችን በማስጨበጥ ረገድ ዋንኛ መሣሪያዎች ናቸው ። ሌኒን በሶቭዬት ኅብረት ትምህርትን ለኅብረተሰቡ ከማዳረስ አኳያና የየይዘቱንም ሁኔታ በተመለከተ በአጣዳፊ ተግባርነት አንድ መርሐ ግብር ቀይሶ ነበር ። በዚሁ መርሐ ግብር ውስጥ 1/ ጠቅላላና ፖሊቴክኒካዊ ትምህርት (ንድፈሐሳብን ከተግባር ጋር የሚያጣምሩ) ዕድሚያቸው እስከ 16 ለሆኑ ወንዶችና ሴቶች እንዲሰጥ ፣ 2/ በትምህርትና በምርታማ—ማኅበራዊ ሥራ መካከል የተቀራረበ ግንኙነት እንዲኖር ፣ 3/ በትምህርት ቤት መምህራን መካከል ጠንካራ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ሥራ እንዲካሔድ ፣ 4/ አዳዲስ መምህራንን በኮሚኒስት ዲስፕሊን ማሠልጠን ፣ የቡርዧውን ርዕዮተዓለም በወጣቱ መካከል እንዲሠርፅ የሚፈልጉ መምህራንን መድረክ መንሣት 14 የሚሉ መመሪያዎች ይገኙበታል ።

የፖሊቴክኒክ ትምህርት ከሳይንስና ቴክኒክ ጋር የተሳሰረ ሲሆን ፣ ማኅበራዊ ለውጥን ለማካሄድ በሚደረገው ሁለገብ ግንባታ ውስጥ የፓርቲውን ፖሊሲ በማስፈ

Digitized by Google



ትምህርት ለምርታማ ሥራ ።

Digitized by Google

ጸም የኅብረተሰቡን ቁሳዊ ፍላጎት ለማሟ
ላት የተነደፈውን መርሐ ግብር በተግባር
ለመተርጐም ያስችላል ።

የአንድን ዜጋ ብቁነት ለማረጋገጥ በአእ
ምር ማጐልመስ ብቻ ሳይሆን በአካልም
የዳበረ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል ።
የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት ዓላማው
የሕፃናትንና የወጣቱን በአጠቃላይም የሠ
ራተኛውን ሕዝብ አካል አዳብሮ ለሥራና
ለማናቸውም አስፈላጊ ግዳጅ ብቁ እንዲ
ሆን ማድረግ ነው ። የሰውነት ማጐልመሻ
ለባህል ዕድገት ፣ ለወዳጅነት ፣ ለአገር ግንባ
ታና መከላከል ፣ ለመሳሰሉት እንቅስቃሴ
ዎች ጭምር ያገለግላል ። በስፖርት ውድ
ድሮች አማካይነት ሕፃናት ፣ ወጣቱና ሠራ
ተኛው ደፋር ፣ ጠንካራና ታታሪ እንዲሆኑ ፣
የስፖርት ቴክኒክ ዕውቀትና የዳበረ ባህል
እንዲቀስሙና አእምሯቸውን እንዲያበለ
ጽጉ ያግዛቸዋል ።

የሶሻሊዝምን የዕድገት ጐዳና የተከተሉ
መንግሥታት የሰውነት ማጐልመሻ ትም
ህርት በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት
እንዲያገኝ ማድረግን እንደአንዱ ዓቢይ
ተግባራቸው አድርገውታል ። በዚህም መሠ
ረት አዲሱን ሥርዓት ገንቢ የሆነው ወጣት
አእምሮውን ከሚያደነዝዙ ፣ ሞራሉን ከሚ
ያላሽቁ ፣ ጤንነቱን ከሚያቃውሱ ጎጂ ልማ
ዶች ተጠብቆ እንደየፍላጎቱ የሚመርጠ
ውን የስፖርት ዓይነት እንዲያዘወትር ያደ
ርጋሉ ።

በአብዮታዊት ኢትዮጵያም የሰፊውን
ሕዝብ አካል ማጐልመሻ ሁኔታዎች በየቦ
ታው ለማመቻቸት ልዩ ትኩረት ተሰጥ
ቷል ። በፓርቲያችን ፕሮግራም እንደተገለ
ጸው ፦—

አዲሱ ሶሻሊስት ሰው በመንፈስ ብቻ ሳይሆን
በአካላዊ ጥንካሬውም ብቃት ያለው መሆን
ይጠበቅበታል። . . . የአካላዊውን ባህል ዕድ
ገት የበለጠ ለማስፋፋት በከተማና በገጠር
መላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ማሳተፍያሻል ።
ምርጥ ስፖርተኞችንም በብዛትና በጥራት
ማፍራት የሚቻለው ስፖርትና አካል ማሠል
ጠኛን.. ሕዝባዊ መሠመር በማስያዝ ነው። [15]

ፕሮግራሙን ተግባራዊ ከሚያደርጉት ተቋ
ሞች መካከል ትምህርት ቤቶችም ይገኙበ
ታል ። በዚሁ መሠረት የሀገሪቱ ወጣቶች
በስፖርት በመታነጽ ጠንካራ ፣ ቀልጣፋና
ንቁ ዜጋ እንዲሆኑ ለማድረግ የአብዮታዊት
ኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ኃላ
ፊነት እንዳለባቸው ግልጽ ነው ።

ከርዕዮተዓለም ፣ ከፖሊቴክኒክና ከአካል
ማጐልመሻ ትምህርቶች በተጨማሪ የቀለ
ምና የሥነውበት ትምህርትም የተሟላ ስብ
እና ያለው ሰው ለመቅረጽ ከፍተኛ ድርሻ
አላቸው ። የቀለም ትምህርት አንድ ግለሰብ
ሁሉንም የሳይንስ ዓይነቶችና የባህል መስ
ኮች የሚመለከት አጠቃላይ ዕውቀትን ፣
የምርምርንና ነገሮችን ሳይንሳዊ በሆነ መን
ገድ የማመዛዘንን ፣ የማነፃፀርንና በዝርዝር
የማጥናት ችሎታን ፣ በአጠቃላይም የአእ
ምሯዊ ሥራ ክንውን ዘዴዎችን እንዲሁም
የመማር ጽኑ ፍላጎትን ያጐናጽፋል ።

ሥነ ውበት የውበትን ምንነት ፣ አመጣጥ ፣
እድገትና ሚና የሚያጠና የዕውቀት ዘርፍ
ነው ። ሥነ ውበት የደስታን ፣ የኀዘንን ፣ የን
ዴትንና የመሳሰሉትን የሰውን ስሜቶች
በመቀስቀስ ፣ ሰዎችን ለአንድ ዓይነት ማኅ
በራዊ ግብ ያነሣሣል ፤ ያስልፋል ፤ ያዝና
ናል ፤ ወዘተ . ። የሥነ ውበት ትምህርት
ዋንኛ ማስተላለፊያ ኪነጥበብ (ለምሳሌ ፣
ሥነ ጽሑፍ ፣ ሙዚቃ ፣ ቴያትር ፣ ሲኒማ ፣
ሥዕል ፣ ቅርፃቅርፅ) ነው ። ኪነጥበብ በአቀ
ራረቡ ውበታዊ ስለሆነ የሰውን ስሜት ያነ
ሣሣል ። የሥነ ውበት ትምህርት ሲባልም
የሰውን የኪነጥበብ ስሜትና ፍላጎት ማዳ
በር ማለት ነው ። በሥነውበት ትምህርት
የታነፀ አእምሮ ውበትን የማጣጣምና በፈ
ጠራም የመሳተፍ ችሎታ ይኖረዋል። በሳ
ይንሳዊ ርዕዮተዓለም ላይ ተመሥርቶ የሚ
ሰጥ የሥነ ውበት ትምህርት የወጣቶችን

Digitized by Google

እእምሮ ያዳብራል ፤ ሕይወት አስደሳችና ዓላማ ያለው መሆኑን ለመረዳት ያስችላቸዋል ።

ማጠቃለያ

አዲስ ሰው የመፍጠሩ ሥራ ሥርዓተ ማኅበርን ከመቀየርና ቴክኖሎጂን ከማዳበር አኳያ ሲታይ የሚከብድና ውስብስብ ተግባር ነው ። ለሶሻሊዝም ግንባታ የሚጣሉት ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረቶች የሰዎችን አመለካከት ከመለወጥ ጋር የሚከናወኑ ተግባሮች ናቸው ። የሰዎች አመለካከት የሚወሰነው በሚገኙበት ቁሳዊ ሁኔታ ቢሆንም የነዚህ ሁኔታዎች መቀየር አመለካከትን ከመለወጡ አንፃር ፈጣንና ውጤቱም በግልጽ የሚታይ ነው ። የሰዎች ቁሳዊ ሁኔታ ቢቀየር እንኳ የቀድሞዎቹ አመለካከቶችና ልምዶች እምብዛም ሳይለወጡ ለብዙ ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ ። ምንም እንኳ ሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ተመሥርቶ ቴክኒካዊ መሠረት ቢጣልም የምርቱንና የቴክኒኩን ሥራ የሚመሩት የሰዎች አመለካከት እስካልተቀየረ ድረስ የግንባታው ሥራ ፈር ይዟል ለማለት አይቻልም ። የሰዎችን ንቃተ ኅሊና የመለወጡና የማዳበሩ ሥራ ጊዜና ትዕግሥት የሚጠይቅ ፤ በሳይንሳዊ ጥናቶችና ዘዴዎች ላይ የተመሠረተ ሥራ ነው ። ለዚህ ውስብስብ ሥራ ዓይነተኛ መሣሪያ ትምህርት ሲሆን እሱን የማስተላለፉና በሚገባው ወገን በሚገባ እንዲዉብጥ ማድረግም ውስብስብና ከባድ ነው ።

ለአገር ዕድገት ዋስትና ለማስገኘት ተተኪውን ትውልድ የማዘጋጀቱ ኃላፊነት የያንዳንዱ ዜጋ ቢሆንም ለትምህርቱ ተጠሪ የሆኑ መምህራን የበለጠ ኃላፊነት አለባቸው ። በሶሻሊስት ፔዳጎጂ መሠረት ወጣቶች ስብእናቸው የተሟላ ሆነው እንዲያድጉ መምህራን ወሳኝ ሚና አላቸው ። መምህራን አዲሱን ትውልድ በሶሻሊስት ሥነ ምግባር ኮትኩተው የሚያዘጋጁ በመሆናቸው ለኅብረተሰብ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ። መምህራን የፓርቲውንና የመንግሥትን ፖሊሲ ተከትለው አዲሱን ሰው በመፍጠሩ ሥራና ጠቅላላውን የትምህርት ዕቅዳችንን ተግባራዊ ለማድረግ ከኅብረተሰቡ እጅግ ከባድ አደራ የተቀበሉ ናቸው ።

መምህራን ተማሪዎች ለጋራ ብልጽግና እንዲሰለፉ፥የሥራን ወሳኝነትና ክቡርነት እንዲገነዘቡ፥ብቁና አምራች ዜጋ፥የሕዝብና የመንግሥት ንብረት ተንከባካቢ እንዲሆኑ ፤ ለሶሻሊዝም ዓላማዎች ተግባራዊነት በቆራጥነት እንዲታገሉና በወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነት እንዲያምኑ ፤ በሶሻሊስት አርበኝነት እንዲታነጹ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው ። በዚህ ዓይነት ኃላፊነታቸውን የሚወጡ መምህራን ሲኖሩ ነው ሶሻሊስት ፔዳጎጂ የተሟላ ሰው ለመፍጠር የሚያስችለውና የሀገር ግንባታን የሚያፋጥነው ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Webster's Third New International Dictionary — Unabridged, (USA: G and Merriam, Co.) 1976, p. 1663.
2. The New Encyclopedia Britannica in 30 volumes, 15th Edition, Vol. 13, York: Encyclopedia, Britanica, Inc. 1983), p. 1099.
3. Great Soviet Encyclopedia Third Edition, Vol. 19, (New York: MacMillan Inc., 1978), p. 136.
4. *Ibid.*, p. 380.
5. Pedagogy: Study material for the Training and Further Qualification of

Digitized by Google

Cadres of Public Education, (Berlin: Verlag "Volk und wissen", 1983, p. 24.

6. *Ibid.*, pp. 26-27.

7. መስታወት ፣ በየ2 ወራት በትምህርት ሚኒስቴር ሕዝብ ግንኙነትና የትምህርት ዜና አገልግሎት የሚታተም ፣ ቅጽ 4 ፣ ቁጥር 3 ፣ ሚያዝያ—ግንቦት 1979 ፣ ገጽ 5 ።

8. ከላይ የተጠቀሰው ።

9. ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 6 ።

10. ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለኢሠፓ መሥራች ጉባኤ ያቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ፣ ጳጉሜ 1976 ፣ ገጽ 129—130 ።

11. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ፕሮግራም ፣ 1977 ፣ ገጽ 126—127 ።

12. Kim Il Sung, On Socialist Pedagogy, (Pyongyang: Foreign Languages Publishing House,.1939), pp. 328-29.

13. Great Soviet Encyclopedia, 3rd Edition, Vol. 20, (New York: MacMillan, Inc. 1979), p. 388.

14. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 29, (Moscow: Progress Publishers, 1965), p. 111, 132.

15. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ፕሮግራም ገጽ 136 ።

Digitized by Google

Hoover Institution Library
3 6105 070 925 586

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

BSPP

Digitized by Google